# ቅዱስ ቁርባን

## መግቢያ

**በስመ አብ፣ ወወልድ፣ ወመንፈስ ቅዱስ፣ አሐዱ አምላክ፣ አሜን።**

ከሰባቱ ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ የሆነው ቁርባን የሚለው ቃል የሱርስት ቃል ሲሆን በቁሙ ለእግዚአብሔር የሚቀርብ መንፈሳዊ አምኃ፣ መሰዋት፣ መባዕ ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን ይቀርብ የነበረው የመስዋዕት ቁርባን፤ ከበግ፣ ከላምና ከተለያዩ የእንስሳት ነበር። በሐዲስ ኪዳን ግን እንስሳት በቤተ መቅደስ ውስጥ ቁርባን(መስዋዕት) ሆነው አይቀርብም፤ መስዋዕት ሁሉ በክርስቶስ ሥጋና ደም ተጠቅሏልና።

ቅዱስ ቁርባን ሕይወት ነው። ቅዱስ ቁርባን የዘላለማዊነት ማኅተም ነው። ቅዱስ ቁርባን የክርስቲያን ኃይል ነው። የጸጋው ምንጭ ነው። የቃልኪዳን ስጦታው ነው። ምርኩዝ ዋሱ ነው። ያለ ቅዱስ ቁርባን ክርስትና ዜሮ ፋርሽ ነው። ክርስትና ክርስቶስነት ነውና። ክርስቶስነት እንኪያስ ሥጋና ደሙን በመቀበል ውስጥ ክርስቶስን መልበስ ነው። ያለ ቅዱስ ቁርባን ሰማያተ መንግሥትን መውረስ አይቻልም። የክርስቶስ በጎች የሚገቡበት የበረቱ በር ቅዱስ ቁርባን ነው። ቅዱስ ቁርባን የትንሣኤ ማጽደቂያው ነው። ያለ ሥጋና ደሙ ሕይወት ማግኘት አይቻልም።

(የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 6)

54፤ *ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።*

56፤ *ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ።*

### ቅዱስ ቁርባን ለመውሰድ ምን ያስፈልጋል ?

ንስሐ ያስፈልጋል። የቅዱስ ቁርባን መሠረታዊ መስፈርት ሰውነትንና ውስጣዊ ሕይወትን ከኃጢአት ማንጻት ነው። ምክንያቱም አዲሱ ወይን የሚሞላው በአዲሱ አቁማዳ ነው። ቅዱስ ቁርባን የሚወሰደው ከኃጢአት በታጠበ ሰውነት ነው። የቃናው ሠርግ ቤት ጋኖች ውኃ ተሞልተው ወይን ከመሆናቸው በፊት የሚቀረው ቅራሪያቸው መደፋት ነበረበት። እነሆ ወይኑ በሕይወታችሁ ውስጥ እንዲሞላ የኃጢአት አተላ ሁሉ መደፋት ያስፈልገዋል።

ከዚህ በዘለለ የዕድሜ ክልል፣ የኑሮ ሁኔታ እና ማኅበራዊ ነገራት ቅዱስ ቁርባንን ከመውሰድ አያግድም። ንስሐ ተቀብሎ ቀኖናውን የጨረሰ ሰው ሁሉ መቁረብ ውዴታው ሳይሆን ግዴታው ነው። ምክንያቱም ያለ ቅዱስ ቁርባን ክርስቲያንነት ሊጸና አይችልም። ክርስቶስ የሌለበት ሕይወትና ኑሮ የክርስቲያን አይደለም። ክርስቶስን ያልተከተለ ጉዞ የክርስትና መንገድ አይደለም። ስለሆነም ያለ ቅዱስ ቁርባን ክርስትና የለም።

ዛሬ ዛሬ በሚያሳዝን አኳኃን የቤተክርስቲያን አገልጋይ የሆኑ የሚሰጥረ መለኮትን ስጦታና የመናፍስትን አሠራር ያልተገነዘቡት ሁሉ ምዕመኑን ከቅዱስ ቁርባን አርቀውታል። "ቀይ ዕድሜህ ገና ነው፣ ትንሽ ሰከን በል ልትሳሳት ትችላለህ፣ ወጣት ለቁርባን ዝግጁ አይደለም" እያሉ በተለይ ወጣቱን ማኅበረሰብ ከክርስቶስ ሥጋና ደም በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የሚያርቁ ሰዎች አሉ። በዚህ ምክንያት ትውልዱ ቁርባንን ይፈራል። ሥጋና ደሙን ይሸሻል። በዚህ ሽሽት ውስጥ ታዲያ ዲያቢሎስ የራሱን ወጥመድና መረብ ዘርግቶ የሰው ልጆችን በመጠላለፍ ገና ከማለዳው ጀምሮ ትውልዱን በመያዝ ብዙ ውድመቶችን እንደ ተናጠልም እንደጋራም አድርሶ በብዙ አቅጣጫዎች ላይ አክስሮን ቁጭ አለ።

ስለሆነም ይህን ንባበ ጥራዝ የተዘጋጀበት መሠረታዊ ዓላማ፤ የቅዱስ ቁርባንን ሰማያዊ እውነት በመግለጡ በኩል ያለውን መረጃ በማካፈል ለሥጋና ደሙ ክብር የበቃን ማድረግ ነው።

ከመምህር ግርማ ተማሪ ናትናኤል

# ክፍል - 1

## የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት

የመጀመሪያዎቹ የሰው ልጆች አዳምና ሔዋን ዲያቢሎስ ወደ ሕይወታቸው ከመጣ በኋላ **አስበው የማያውቁትን ማሰብ** ጀመሩ። አምላክ ስለመሆን አሰቡ። ከመሠረታዊ የዲያቢሎስ የጥፋት ስልቶችና አካሄዶች ውስጥ አንደኛው ክፍል አስቀድሞ ያላሰብነውን እንድናስብ ነገሮችን በራሱ ድብቅ አጀንዳ ተርጉሞ የማሳየት አሠራሩ ነው። ሔዋን የሞትን ዛፍ ከዲያቢሎስ ጋር ከተነጋገረች በኋላ የሕይወት ዛፍ እንደሆነ አድርጋ አየቺው። ያልታየው ታያት፣ ያልሆነው መሰላት፣ የሌለው እንዳለ ተተረጎመላት ማለት ነው።

ዛሬም ይሄው የዲያብሎስ አካሄድ ቅርጹንና ሁኔታውን እንደዘመኑና እንደ ትውልዱ በመቀያየር ይዘቱን ግን ከመሠረቱ በተነሣበት ልክ አድርጎ ያልታየውን ያሳየናል፣ ያልተነገረውን ያሰማናል፣ ያልተሰማውን ያናግረናል። በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ሦስት ቁጥር ስድስት ላይ እንደዚህ የሚል ቃል ታገኛላችሁ። << ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደ ሆነ፥ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ፥ ለጥበብም መልካም እንደ ሆነ አየች፤ ከፍሬውም ወሰደችና በላች፤ ለባልዋም ደግሞ ሰጠችው እርሱም ከእርስዋ ጋር በላ። >>

ዲያቢሎስ አትብሉ የሚባለውን ብሉ ወደሚለው ለውጦ የሰበካት ሔዋን፤ በለሱን ከዚህ አስቀድሞ ባላየቺው መልኩ ማየት ጀመረች። ይኸውልህ እንደዚህ ነው የሚሆነው። ጠላት ወደ ሕይወትህ መጥቶ ነገሮችን መለወጥ ከጀመረ በኋላ የሕይወትህን አሳቦች፣ ዓላማዎች፣ እቅዶች፣ ፕሮግራሞች እና የኑሮህን አሰላለፍ እንደቀድመው አታየውም።

ዛሬ ላይ ብዙዎቻችን ትናንት በመልካም ስንመለከታቸው የነበሩትን ነገሮች በተለየ አቅጣጫ ማየት ከጀመርን መቆየታችንን ጭምር ለመረዳት እንዳንችል ዘመኑ፣ ጊዜው እና ትውልዱ መናፍስታዊ ዳፍንት በሆነ የዘልማድ ኑሮ ውስጥ የቆየ በመሆኑ ስለ ክፉ ጠላቶች ያለን ግንዛቤና አመለካከት በጣም አናሳና ደካማ ስለሆነ ተሰውሮ ለሚያጠቃውና የጥፋት ሥራዎችን በረቀቀ ዘዴ ለሚፈጽመው የእርግማን ኃይል ጥሩ መሣሪያ እንሆን ዘንድ ተገደናል። ብዙዎቻችን እንደ ማኅበረሰብ አስቀድሞ የጨዋነት ልኬት አድርገን የወሰድናቸው እሴቶቻችን ዛሬ ዛሬ ሳይታወቀን ባህላዊነትና ኋላ ቀርነት አድርገናቸው ንቀናቸዋል። በፊት በከበሬታና በመውደድ የምንመለከተውን የሕይወታችንን አንዳች መልካም ክፍል ዛሬ ከአኗኗራችን ውስጥ ብንፈልገው አይገኝም። ባሳለፍነው የታሪካችን ዳራ ውስጥ በጥሩ መዝገብ ያሰፈርነው ማንነት፣ እውቀትና ጥበብን ዛሬ ላይ ሳናውቀው የተቃረንናቸው፣ የሸሸናቸው እና ለመሆን የምንፈራቸው እውነታዎቻችን ናቸው። በአንፃሩ ቀደም ሲል እንደ አመፃ፣ ነውር፣ ግፍ፣ ዝባዝንኬ፣ ርኩስ፣ አስፈሪና አስጨናቂ አድርገን የምናያቸውን ነገሮች በዛሬው የሕይወታችን ምዕራፍ ተገኝተንባቸው አልፎም ተርፎ ስላልተነገረው ዘመናዊ ጥቅማቸው ስንከራከርላቸው የምንገኝ ጥቂቶች አይደለንም። የምንጠየፋቸው ነገሮች አውቀነውም ሆነ ሳናውቀውም የተጠልፍንባቸው ነገሮች ሆነዋል። የምንፈራቸው ጉዳዮችን በድፍረት ምክረናቸዋል። የምንሸሻቸውን ነገሮች ዞረን እየሄድንባቸው ነው። ይሄን ከምለብስ አንገቴ ላይ ካራ ይቀመጥ የሚሉ እህት ወንድሞቻችን ዛሬ ያንን ልብስ ለብሰውታል። እዚህ ቦታ ከምገኝ አምላክ ከምድረ ገጽ ያጥፋን ያልን ሰዎች አሁን ላይ ምናልባት ቀንደኛ የቦታው ተሰያሚ ሆነን ይሆናል። ከባህሪያችን፣ ከልማዳችን፣ ከልቦናችን ያልገጠመውን እንደገጠመ አድርገን በፈረሰበት በኩል የቆምን ሰዎች ብዙዎች እንደሆንን የማንናገረው ሕይወታችን እንደሚናገር እናውቃለን። እንዴት ነው ነገሩ? ምንድነው ይሄ ጉዳይ? ለምንድነው እንደዚህ የሚሆነው?

ይሄ  ለምን ሆነ ስንል ዲያቢሎስ ወደ ሕይወትና ወደግዜ መጥቷላ። ቦታህ ውስጥ ቦታ ይዟል። ኑሮህ ውስጥ ስፍራ አግኝቷል። እቅድህ ውስጥ ቀድሟል። ስለዚህ የቀደመው ክፉ ነገርን መልካም አድርጎ ያሳይሃል። አሊያም የቀደመው መልካም ነገርን ክፉ አድርጎ ያሳያሃል።

ስለሆነም አዳምና ሔዋን << የሞትን ፍሬ የሕይወት ፍሬ >> ይሆንልናል ብለው በሉ። በመብላታቸውም የእግዚአብሔርን ቃል፣ ጥበቃ፣ ሞገስና ጸጋ አልበቃንም ተጨማሪ እንፈልጋለን ብለው ነውና ሕጉን የተላለፉት የሞት ኃጢአት ወደ ሰው ልጆች ገባ።

አዳም አምላክ ትሆናለህ የተባለውን የዲያቢሎስ ድምፅን መሆን ፈልጎ በለስ ቢበላ፤ ሕያው አምላክ ግን አምላክነቴን ልትነጥቅ ተመኘህ ብሎ አልተከፋም። ይልቅስ ከአዳም ልጆች እንደ አንዱ ሆነና በገር ቋንቋው እንደዚህ አለ << " እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል" (የዮሐንስ ወንጌል 14፥12) >>

እኔ በአምላክነት ኃይሌ የማደረገውን ታደርጉ ዘንድ ከእኔ ጋር ሁኑ ያለ አባት እንደምን ቸር ነው? እኔ በሥልጣኔ የምፈጽመውን ታከናውኑ ዘንድ ወደኔ ኑ የሚል ንጹሕ ጌታ እንዴት ርኅሩኅ ነው? አሳልፎ እኔ ከምሠራው የሚበልጥ ታደርጋላችሁ የሚል የዋህ አምላክ እንደምን ፍቅር አለው?

እነሆ፥ አዳም የተመኘውን አገኘ። አምላክ የሚሠራውን ሊሠራ፣ የሚያየውን ሊያይ፣ የሚሰማውን ሊሰማ ተመኝቶ ሕጉን ቢጥስ፤ እንግዲያው ኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ሲሆን ሰውን አንድ ጊዜ ወድዶታልና የተመኘውን ሰጠው። ሰው አምላክ፥ አምላክ ሰው ሆኖ አንድነቱን ሰጠ በቃ። ለሔዋን "ከእግዚአብሔር የበለጠ ትሠራላችሁ" ብሎ ሳያስብ ትንቢት የተናገረው እባብ ዲያቢሎስ፤ ለክፋት ያሰበው ቃሉን ክርስቶስ ሥጋ ሆነና በአንድነቱ አማኑኤል ተብሎበት በፍቅር አጸደቀው። ከኔ የበለጠውን ታደርጋላችሁ ብሎም ኃያል ድምፁን ለዓለም አሰማ። ስለዚህ ያቺ የዛፍ ፍሬን እግዚአብሔር ሲተክላት፤ ከእርሱ ለጊዜው ልንርቅባት ሲሆን ግን ለዘላለም ይበልጥ ወደርሱ ልንቀርብባት ምክንያት የምትሆን መሆኗንም ያውቃል። እኛን የሚያርቀን አንዳች ነገር አልፈጠረም የሰማዩ አባት። አዳምና ሔዋን ያንን ዛፍ ባይበሉ፤ ክርስቶስና ድንግል ማርያምን አናገኛቸውም ነበረ። አዳምና ሔዋን የተከለከለውን ፍሬ በልተው ከገነት ባይወጡ፤ ገነትን የፈጠረውን ጌታ ሥጋና ደም በልተን እኛ በእርሱ አንኖርም፤ እርሱ በእኛ አይኖርም ነበረ። አባቶች ይህንን የእግዚአብሔር ፍቅርና ጥበብ በእውነት ተመለከቱና እንዲህ አሉ << እግዚአብሔርን ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ ይልቅ ዓለምን ያዳነበት ጥበቡ መንክር ነው። >>

ስለዚህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣበት አንደኛው ታላቅ ዓላማ ሞተ ኃጢአትን ለማስወገድና ሕያውነትን ለኛ ለመመለስ አምላክነቱን ይሰጠን ዘንድ ነው። ካጣነው ጸጋና ሞገስ በላይ እርሱነቱን ይሰጠን ዘንድ ነው። እግዚአብሔር ቃል ሥጋ ሆነ። ጸጋንና እውነትን ተመልቶ በኛ አደረ። ይህንን መለኮታዊ ስጦታውን ደግሞ በምን በኩል አሳልፎ ሰጠን? በሥጋና ደሙ በኩል ባርኮ ሰጠን። የሞትን ፍሬ በልተን ከእርሱ እንደተለየን፤ የእርሱን ሥጋና ደም በልተን ወደርሱ ቀረብን። በልተን የወጣን ስንሆን፤ በልተን እንመለሳለን።

(የዮሐንስ ወንጌል ምዕ. 6)

48፤ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ።

49፤ አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ ሞቱም፤

50፤ ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት ከሰማይ አሁን የወረደ እንጀራ ይህ ነው።

51፤ ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፤ እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው።

ቅዱስ ቁርባን ምድር ላይ ሳለን ሰማያዊ የምንሆንበት ቁልፍ መሻገሪያ ነው። እመቤታችን ድንግል ማርያም ሰማይንና ምድርን እንደምትፈትለው ሐርና ወርቅ አስማምታ ፈተለች ስንል፤ የሚሞተውን ሥጋና ደም በማይሞተው መለኮት አግባብታ አምላክን ወለደች ማለት ነው። ይሄ የአምላክ የባሕሪይ ልጅ የሰው ልጅ የተባለበት የአንድነት ሚስጢር ለሁላችን የተሰጠን ታዲያ በቅዱስ ሥጋና ደሙ በኩል ነው። ቃል ሥጋ ሆነ አንደኛው ነው። ጸጋንና እውነትን ተመልቶ በኛ አደረ ሁለተኛው ነው። እግዚአብሔር ቃል ከመለኮቱ ሳይወሰን በሰው አካል ተወስኖ ከእመቤታችን ተወልዶ ሰው ሆነ። ከእመቤታችን የነሣውን ሥጋና ደም ደግሞ በመለኮቱ ባረከውና ለኛ ሲሰጠን ጸጋንና እውነትን ተመልቶ በኛ አደረ እንላለን። በቅዱስ ቁርባኑ በኩል ነው << በኛ አደረ >> የሚለው ቃል የሚተረጎመው። ቃሉን ተመልከቱ።

" ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ።" (የዮሐንስ ወንጌል 6፥56)

ኢየሱስ ክርስቶስ ምድር ላይ የሰው ልጆችን ውደቀት ተመልክቶ፣ የዘር እርግማንን ሊያጠፋ፣ በፍጹም ፍቅሩ ሊባርክን ወገናችን ከምትሆን እመቤታችን መጥቶ ሲጎበኘን፤ እርሱ ከኛ ሰውነትን ይካፈል፥ እኛ ደግሞ ከእርሱ አምላክነትን እንካፈል ዘንድ ነው። ሰው አምላክ፤ አምላክ ሰው የመሆኛው መተሳሰሪያው ገመድ ቅዱስ ቁርባን ነው። ክርስቲያን የመሆኛው ማጽደቂያ ቅዱስ ቁርባን ነው። ሐዋሪያው እኔን ክርስቶስን እንደምመስል ብሎ አምላክን የመምሰሉን ቋንቋ በፍጹም ድፍረት ያሰማው አስቀድሞ ከራሱ ከሊቀ ካህኑ ከኢየሱስ ክርስቶስ እጅ በመቁረቡም ጭምር ነው። ስለዚህ መለኮታዊ ስጦታዎቹን ማግኘት የምንችለው በሥጋና ደሙ መባረክ በኩል ነው።

ጌታችን << ክርስቶስ >> የመባሉ ኃያሉ ስጦታ አንደኛው ቅዱስ ሥጋና ደሙ መሆኑን ብዙም አላስተዋልነውም። ኢየሱስ ማለት፥ መድሃኒት ማለት ነው። ክርስቶስ ማለት ሥጋ የለበሰ የተቀባ ንጉሥ ማለት ነው። እንግዲያው ኢየሱስ ክርስቶስ ማለት፤ መድሃኒት ሊሆን የተቀባ ንጉሥ ማለት ነው። ቀደመ ዓለም ያለ እናት ከአብ የተወለደ ሲሆን ድኅረ ዓለም ያለ አባት ከድንግል ማርያም የተወለደው ወልድ እግዚአብሔር፤ የመወለዱ ሚስጢር በሥጋ ትስብእት ይገኝ ዘንድ ነው። መለኮቱ በሁሉ የመላ ነው። ሥጋ ግን የተወሰነ ነው። እነሆም በመለኮቱ ምሉዕነት ሳለ የእመቤታችንን ሥጋ በተዋሐደ ግዜ፤ የተወሰነ ሥጋን በመለኮቱ በሁሉ የመላ መድሃኒት አደረገው። የእግዚአብሔር ስሙ የተመሰገነ ይሁን። ኢየሱስ መባሉ፥ ሥጋ መድሃኒት እንዲሆን በመለኮቱ ኃይል እንደባረከው ሲነግረን ነው። ክርስቶስ መባሉ፥ ያልታየው መለኮተ ሕላዌ በሚታይ ሥጋ ተገኝቶ ቢባርከን ጊዜ እኛነትን መምሰሉ ሲያመለክት ነው። ይሄ የስሙ ኃይል ግን በልባችን የለም። በእምነታችን የለም። በአኗኗራችን የለም። ሃይማኖት ማድመቂያ ነው ያደረግነው። ጎራ መለያ ነው ያደረግነው። በስሙ ላይ የተኛነው። ነገር ራእይ ባለው የእውነት አምልኮት ውስጥ ዕለት ዕለት በቅድስናው መስመር የምንከተለው ስሙ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰሞች በላይ ለሰው ልጆች ገኖ የመዳናችን ማኅተም ነው። ቅዱስ ሐዋሪያውም ስለዚህ ነገር በእውነት አለ። ቃሉን እስኪ ተመልከቱ። " መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።" (የሐዋርያት ሥራ 4፥12)

መዳን በሌላ የለም ማለቱ የባሕሩ መንፈስ እንደሚፈታው የቅዱሳን ተራዳኢነትን ማሸሸ ሳይሆን፤ በሥጋና ደሙ ለሁላችን መድሃኒትነቱን የሰጠን አባት ክርስቶስ ብቻ ስለመሆኑ ያበከረ ቃል ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ የሚለው ስሙ ብቻ አይደለም። <<አማኑኤል>> የመባሉ አንደኛው ኃያል ክፍል ቅዱስ ቁርባን ነበረ። አማኑኤል ማለት እግዚአብሔር ከኛ ጋር ሆነ ማለት ነው። አንድ ሆነ ማለት ነው። የአንድነቱ ማሰሪያ አሪቡት ደግሞ ቅዱስ ሥጋና ደሙ ነው። ወንጌለ ዮሐንስ 6፥56'ን ተመልከቱ። " ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ።" ይላል ቃሉ ሲነበብ። አሁን ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ

በእኔ ምን ይላል አለ? በእኔ ይኖራል አለ። እኔም በእርሱ ምን እላለሁ አለ? በእርሱ እኖራለሁ አለ። ታዲያ ይሄ አንድነቱ አይደለም? እርሱ በእኛ፥ እኛ በእርሱ ማለት አማኑኤልነቱ እውን ሲሆን ነው። የእግዚአብሔር ቤት እንሆን ዘንድ ክርስቶስ በሥጋ ተገልጦ በውስጣችን አማኑኤልነት ታትሞ እንዲኖር ወደራሱ የሳበን በቅዱስ ቁርባኑ በኩል ነው።

## ክፍል - 2

## በር የጠፋው ትውልድ

## ወደ አብ የሚወስደው ሰማያዊ በር የትኛው ነው ?

እስኪ የዮሐንስ ወንጌል ምዕ. 10'ን ከ7 ቁጥር ጀምረን ምን ይላል የሚለውን እንመልከት።

(የዮሐንስ ወንጌል ምዕ. 10)

7፤ ኢየሱስም ደግሞ አላቸው። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ እኔ የበጎች በር ነኝ።

8፤ ከእኔ በፊት የመጡ ሁሉ ሌቦችና ወንበዴዎች ናቸው፤ ዳሩ ግን በጎቹ አልሰሙአቸውም።

9፤ በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፥ ይገባልም ይወጣልም መሰማሪያም ያገኛል።

እኔ ምንድነኝ አለ ጌታ? የበጎች በር ነኝ ይላል። ወደ ቅዱስ ሥላሴ መግቢያ በር ያገኘነውና የተሰጠን በወልድ ዋህድ በኩል ነው። ቃል ሥጋ ሊሆን በምድር ሲወለድ ሰማያዊነቱን ይዞ ወደኛ መጣ። በዚህ በመምጣቱ ውስጥ አንደኛው ያሰማው የደኅነት ድምፅ << እኔ የበጎች በር ነኝ >> የሚለው የነፍስ ድምፅ ነው። ክርስቲያኖች ዛሬ የነፍስ በር የለንም። የእውነትንና የሕይወትን በር አጥተን አጥር ዳር የቆምንና መሄጃ የጠፋን ብዙዎች ነን። ከትናንት ዛሬ እንዴት እንደመጣን ማወቅ ተስኖን፤ ወደፊት ለመጓዝ ቀድሞ የሚመራ የኑሮ ብርሃንን አጥተን፤ ወደማዳን የሚያስገባ የነፍስ በር አጥተን፤ ዙሪያው ሁሉ አንድ አይነት ሲሆን ዝም ብለን እግራችን በመራን በር ውስጥ ከፍተን እየገባን ወዴት እንደምንሄድ፣ የት እንደምንሄድ፣ ምን እንደሚጠብቀን ስለማናውቅ ግራ ግብት ብሎን፤ ውስጣችን መሪ አጥቶ ውጪያችን በዘፈቀደ እየነጎደ፤ ባለቤት ያጣ ኑሮ፣ ሰብሳቢ ያጣ ትውልድ፣ እርስ በእርሱ የተመሳከረ ዘመንና ዓመት ላይ ተገኝተን እየዳከርን የመኖር ፍንጭና ትርጉም የተሰወረው የዛለ አኗኗርን እንኖራለን። የሕይወት በር ከሌለን ራእይ የለንም። ተስፋ የለንም። የብርሃን ምሪት የለንም። ስለዚህ ክርስትናችን ወዴት እንደሚሄድ፣ ኑሮአችን ምን እያሳለፈ እንደሆነ፣ ጊዜያችን በምንና እንዴት እንደሚነጉድ የሚጠቁመን ምንም ነገር አይኖረንም።

ውስጣችን የእፎይታና የሰላም በር ማግኘት አቅቶት የዘመንና የጊዜ ማዕበል አምጥቶ ገፍቶ ባስገባን የጊዜ በር፣ የዘመን በር፣ የክፉዎች በር ላይ ተገኝተን ለገዛ ኑሮአችን መሪ የመሆን ሥልጣኑን ተነፍገን ስንሰደድ እንኖራለን። መሰደድ ነው በቃ። ምን የማያሳድደን አለ? ኑሮ ያሳድደናል። እንጀራ ያሳድደናል። ድህነት ያሳድደናል። ሰላም ማጣት ያሳድደናል። ክፉዎች ያሳድዱናል። ተሰደንም ርቀን የኋላ ችግሮቻችንና ድክርቶቻችን ተከትለውን እየተሰደዱ በየሄድንበት ቦታ ስንማስን፣ ስንማስን፤ ጭንቅ እያለን፣ 'አሁንስ ወዴት ልሂድ' ብለን የምናማርር መነሻና መድረሻው የተቀላቀለብን ምስኪን ዜጎች ከሆንን ቆየን። መግቢያ በር የሌለው መሄጃ የለውም። እኛም መሄጃ የለንም። ስለዚህ ወዳገኘነው እንነጉዳለን። አገር ውስጥም ሆነን በአንክርት አሳብ ዘወትር እንሰደዳለን። ልቦናችን

ከሕሊናችን መስማማት አቅቶት አንድ ሆነን እንደ ሁለት ሰዎች በተጣረሰ አሳብ መካከል እየዋተትን፤ ተረጋግቶ መኖር ተስኖን ዘመናችንን እንደጥላ እንዲሁ የምናሳልፍ በየቤቱ የምንቀጠር እንኖራለን። በር ማጣት አየህ?

እግዚአብሔር ቃል በዓለም ፊት ገጹን አስነበበና እንዲህ አለን። << እኔ የበጎች በር ነኝ። በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፥ ይገባልም ይወጣልም መሰማሪያም ያገኛል። >>

በኔ የሚገባ ቢኖር ምን ይላል? ይድናል። የነፍሰ መዳን፣ የሥጋ መዳን፣ የኑሮ መዳን፣ የበረከት መዳን፣ የጊዜዎች መዳን። የምሕረት ዘመን፣ የምሕረት ዓመት፣ የምሕረት ጊዜ ብለን ቆጥረን ስናበቃ ዛሬ ግን ሁሉም በሽተኛ ነው። አልጋ ላይ የታመመ አለ፣ ሰላም አጥቶ የታመመ አለ፣ ፍቅር ተነፍጎ የታመመ አለ፣ ብቸኝነት ያሳመመው አለ፣ ሰው ያሳመመው አለ። ታሞ በበሽታ ላይ በሽታ የሚጨምር እንዲሁ ብዙ ነው። እናትም ታማለች። አባትም ታሟል። ሕዝብም በሽተኛ። አገርም በሽተኛ። ስንናገር፥ ስናወራ ክርስቲያኖች ነን እንላለን። ቀንጆ ቀንጆ መስቀልም እናስራለን። ዝክር እንዘክራለን። ሲመቸን እናስቀድሳለን። ሲመቸንም ቤተክርስቲያንም፥ ገዳምም እንሳለማለን። እንግዲያው ታዲያ የክርስትናችን ውጤት ለራሳችንም ሲሆን ለሌሎችም መድሃኒት መሆን ሲገባው፤ በሽታችን ስለምን ጸንቶ ቀየ? ሕመማችን ከዘመን ዘመን ለምን በፍጥነት እየጨመረ ሄደ? ምንድነው ያጎደልነው? ምንድነው የሌለን? አያችሁ እዚህኛው ጥያቄ ላይ ቆም ብለን ስናስተውለው በክርስትናችን ጉዞ ውስጥ በእውነትም አንድ የዘለልነው የሕይወት ጉዳይ አለ። በዮሐንስ ወንጌል 15፥5 ላይ " እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ። ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፥ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል።" ይላል። ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም እኮ ነው። ማን እንደዚህ አለ? ኢየሱስ ክርስቶስ። ኢየሱስ ማለት ከዕብራይስጡ ወደ አማርኛ አተረጓጎም ሲመለስ መድሃኒት ማለት ነው። ዛሬ የሕይወትን መድሃኒትን ከውስጥ በኩል ስላጣን፤ ከውጪ በሮጥንባቸው የሕይወት መስኮች በሙሉ ከዳር መድረስ ያቃተን በሽተኞች ሆነን እንገኛለን። ያለ እግዚአብሔር መገኘት የያዝነው ክርስትናችን ነጠላችን ላይ ተንጠልጥሎ ቀረ። አስቀዳሽ እንጂ ተቀዳሽ መሆንን አላወቅንበትምና ከቤተክርስቲያን ስንወጣ ክርስትናም ተከትሎን በዛው ይወጣል። ስለሆነ ጌታ እንደተናገረው ምንም ልናደርግ አልቻልንም። ያለ እኔ ምንም አታደርጉም ነው በቃ። ታዲያ እኮ ይኸው አየነው። በቀለም ትምህርት መፍትሔነት ኑሮአችንን እንለውጠው እስኪ አልንና ተማርን ከ100 ዓመት በላይ። እሺ ዛሬ የት ደረስን? ምን አተረፍን? ምን አገኘን? በተንኮል በኩል የተሰለፉና የእግዚአብሔርን ሕልውና በማጥፋት ረገዱ በኩል የዲያቢሎስ ቀኝ እጆች የሆኑት የሥልጡን አገራት ሰዎች ከፊት ፊት እየቀደሙ፥ የርዮተ ዓለም የመደንግግ ፍልስፍናዎችን እና ክዶ አስከጂ ትምህርቶችን በፖሊሲና ፍኖተ ካርታ ቀርጸው፤ በቴክኖሎጂ እያነሆለሉ ሲፈልጉም በኢኮኖሚ ጫና እያስገደዱ፤ የሴራ ምኞታቸውን እየቀነሱ ብቻ ጣል ጣል እያደረጉ ወደሚፈልጉት አቅጣጫ ሲጎትቱን አልገባንም። እንዲገባንም ፍቃደኞች አይደለንም። ጌታ ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም ነው ያለን። አይ ገንዘብ ገንዘብ አልንና ደሞ በግልም በጋራም አንድ ጊዜ የሥጋ ምቾት ዓላማው የሆነ ኑሮ ፍለጋ ወደ ገንዘብ ሮጥን። ሩጫውን እየተሰደድንም ሞከርነው። ግን ተሰደንም ሰውም አገር ሆነን እንቅልፍ አጣን። ውስጠኛ ሰላም አጣን። እውነተኛ ደስታ አጣን። ከ18 ሰዓታት በላይ እየሠራንም የእጆቻችን ፍሬዎች እየደረቁ፤ በረከትና ረድኤት ሸሽቶን፤ ለፍተን ለፍተን የምናገኘው ሩቅ የማያስኬድ የድካም ትርፍ ሆነና ቁጭ አለ። ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም ነው። እንዳለውም ምንም ፍሬያማ ነገር ጸንተን ልናደርግ ሳንችል እንገኛለን።

ቃሉን ስናስታውስ "በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፥ ይገባልም ይወጣልም መሰማሪያም ያገኛል" ነው የሚለው። መግቢያ መውጫያ ያለው በር ነው ደግሞ። ይገባልም ይወጣልም ነው የሚለው። አሁን እኛ በሩን ስላላገኘነው መግቢያም መውጫያም የለንም። ነፍስ አወቅን ከሚባልበት ጊዜ አንስቶ፤ በኑሮአችንም፣ በአሳባችንም፣ በምግባራችንም፣ በእቅዶቻችንም፣ በጊዜያችንም፣ በመሻታችንም እንደተገኘንበት አከባቢ ብቻ የመኖር ጠባይና ልማድ ስላለን፤ የመዳኛውና የማሰማሪያው በር ላይ ልንደርስ አልቻልንምና ዛሬ ላይ ለደረስንበት የተጣመመ የእምነት ጎዳና፣ የደበዘዘ የሃይማኖት ጉዞ፣ የተናቀ የቃልኪዳን ኃይል፣ የተረሳ የእውነት ታሪክ፣ የተዛነፈ የምሪት መንገድ በሙሉ የክፉ ዘመን ትውልድ መግለጫ ሆነን፤ በዘመኑ ቅዱስ ሰው መነሣት እርግማን እስኪመስል ድረስ

አንድ ጊዜ ተሰብስበን ከቅድስና አምባ ተለየን። የዛሬ ፍቅር ጊዜያዊ ሲሆን በሁኔታዎች ቅርጽ ላይ ያረፈ ነው። የዛሬ አንድነት ጎራ በመለየት ስሜት የራስን ፍቃድ ለማስፈጸም ነው። የዛሬ መተዛዘን የሆነ አንዳች ነገር ከጀርባ ለመቃረም ካለ ፍላጎት ጋር የተያያዘ ነው። እንደ ትውልድ ምን ያህል በግራ ዘመም አካሄድ ውስጥ ተዘፍቀን እንደተገኘን ለማረጋገጥ የጋራ አኗኗራችን በራሱ በቂ ምስክር ነው። ነውር የሚባለው ጉዳይ ዛሬ በዘመናችን ክብር ሲሆን፤ አባቶች በትላልቅ የረድኤትና የሞገስ ኃይል ውስጥ ያለፉበትን ጸጋና በረከት መናቅ የዘመናዊው ትውልድ ሥልጣኔ መነሻ ሆኗል። ከሁሉም በላይ አደጋው ደግሞ አንድ ላይ ተንሻፈን ስንገኝ፤ በቀጥተኛው መስመር የሚሄዱትን ማንጋደዱ ላይ ሁሉም የድርሻውን ያዋጣል። ስለዚህ ደጋጎች ደግ መሆን ይፈራሉ። ትሑታን ታዣዥ መሆን ያፍራሉ። ለምንድነው ይሄ የሚሆነው? ምንድነው ችግራችን? ምንድነው የጎደለን? ምንድነው ነው ያጣነው? ያጣነው የመዳንን በር ነው። መግቢያ መውጪያ ያለውን የመዳን በር። በመግባት የሚያድን፥ በመውጣት የሚያሰማራውን በር አጣነው።

## በሩ ምንድነው ?

ወደ ሥላሴ የሚወስደው በር የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ነው። " ኢየሱስም። እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።" (ዮሐንስ 14፥6)

በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም ነው። አስቀድሞ እኔ የበጎች በር ነኝ ብሏል። በ14፥6 ላይ ደግሞ "መንገድና እውነት ሕይወት ነኝ" አለ። ይሄ የሕይወት መንገድ ወዴት ነው የሚወስደው? ወደ አብ ነው የሚወስደው። በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም በማለት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የመግቢያው በር ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ገልጾልናል። ይኸውም በሥጋና ደሙ በኩል ነው። ቅልብጭ ባለ አገላለጽ "ሥጋዬን ሳትበሉ ደሜን ሳትጠጡ ወደ አብ መንግሥት አትሄዱም" ነው ያለን እግዚአብሔር ወልድ። የክርስቶስን ሥጋና ደም ካልወሰድን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አንወጣም። የክርስቶስን አርአያነት ካልተከተልን ወደ መንግሥቱ አንሄድም። የክርስቶስን ትንሣኤ ካላመንን በትንሣኤው አናርግም። ስለዚህ ከጌታችን በቀር ወደ አብ ልንሄድ አይቻለንም። ወደ አብ የሚመጣ ማለት፤ ወደ ሰማይ የሚወጣ የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚያይ ጻድቅ ነፍስ ማለት ነው። ምክንያቱም አብ ከሰማይ ሆኖ ወልድ በተጠመቀ ጊዜ ራሱን ገልጦዋልና። የአብ በሰማይ መገለጥ ምሳሌው፤ አብ በሰማይ ብቻ የተወሰነ ነው ለማለት ሳይሆን፤ የእግዚአብሔር መንግሥት በአርያም ሰማይ እንዳለ ለሰው ልጆች ሰማያዊ ተስፋ ይሆን ዘንድ ያለው ምሳሌ ነው። ይሄን ሰማያዊ ጉዞ ልንይዝ የምንችለው የእውነተኛውን መንገድ አቅጣጫ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋና ደም በመቀበል ነው።

በዚህ በዮሐንስ ወንጌል መጀመሪያው ላይ ቁጥር 12 ምንድነው የሚለው? << ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤ >> የሚል ቃል ተጽፎ እናገኛለን። ለተቀበሉት ሁሉ ግን ምን ማለት ነው? ምንድነው የምንቀበለው? የምንቀበለው ሥጋና ደሙን ነው። ስሙን ብቻ በመቀበል አይደለም የዘላለም ሕይወት የሚመጣው። ሥጋና ደሙን መቀበል የግድ ነው። " ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።" (የዮሐንስ ወንጌል 6፥54)

አሁንም በዮሐንስ 6፥27 ላይ " ለሚጠፋ መብል አትሥሩ፤ ነገር ግን ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር መብል የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ሥሩ፤ እርሱን እግዚአብሔር አብ አትሞታልና።" ይላል። ለሚጠፋ መብል አትሥሩ ተብለን እኛ ግን ለዕለት እንጀራ ብቻ ስንባዝን ዕድሜያችን ሄደ። እንጀራ ብቻ ስናሳድድ ግዜና ኑሮአችንም በዛው ተሰደደ። ስለዚህ በየቀኑ ለእንጀራ ኑሮ ብቻ የምንወጣ የምንገባ ፍጡሮች ሆነን፤ ሌሎች የሕይወት እውነታዎችና ሰማያዊ ሚስጢሮች ከጉያችንም ሆነው እየተሸሸጉብን ያዝን ስንል እያመለጥን፣ ልናድግ ነው ስል እየደከምን፣ ልናርፍ ነው ስንል ተጨማሪ እየሮጥን፣ ተረጋጋን ስንል ሌላ ችግር እያስጨነቀን አልባረክ ባለ ጊዜ ውስጥ አልበረክት ያለ የሕይወት ዘመንን ተሸክመን ተቸገረን፤ አልፎም ተርፎ የመኖር ጣዕሙ እስከሚደበዝዘን ድረስ ተፈተንን። ኢያችሁ

ለምድር እንጀራ ብቻ መሮጥ? የምድር እንጀራ፣ የምድር መብል፣ የምድር ሥጋ ፍለጋ ስትሮጥ መንገዱ ማለቂያ የለውም። አጋመስኩት ብትል ዞረህ ከተነሣህበት ጅማሮ ላይ ትመለሳለህ። ደረስኩበት ብትል የሚቀርህን አስበህ በአእምሮም በአካልም አንድ ጊዜ ትዝላለህ። እንደዚህ ነዋ የሚለው በቃ፤ << ለሚጠፋ መብል አትሥሩ! >። እሺ ታዲያ ለምን እንሥራ? ቃሉን መለስ ስናነበው እንደዚህ ይላል። << ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር መብል የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ሥሩ! >> ለምን የሚኖር? ለዘላለም የሚኖር። ዛሬ ተብልቶ ነገ የሚርብ መብል አይደለም። ወሩን ሙሉ ተደክሞበት፣ ከክፉዎች ጋር በመታገል፣ ብዙ በመውጣትና በመድከም የሚመጣ መብል አይደለም ይሄ። የዘላለም መብል ነው። እርሱም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደሙ ነው።

ይዘን የተነሣነው ቃል ላይ << እኔ የበጎች በር ነኝ፤ በዚህ በር የሚገባም ቢኖር ይድናል፥ ይገባልም ይወጣልም መሰማሪያም ያገኛል >> ሲል እንሰማዋለን የሠራዊት ጌታ። በእኔ የሚገባ ቢኖር ምን ማለት ነው? እንዴት ነው ወደ ጌታችን መግባት የምንችለው?

ወደ ክርስቶስ መግባት የምንችለው በሰጠን ሥጋውና ደሙ በኩል ነው። ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ እርሱ በእኔ ይኖራል ብሎ ወደርሱ የመግቢያ መንገዱን ነግሮናል። ግን ዛሬ ላይ ይሄንን የሚያስተውሉ ሰዎች ብዙም የሉንም። መግቢያ በሩ የጠፋን ትውልዶች ነን እኛ ማለት። ባገኘነው በር ስንገባ ስንወጣ፣ ስንገባ ስንወጣ፣ ስንገባ ስንወጣ ሁለንተናዊ መዛልና መድቀቅ በስነልቦናም በአካልም ደርሶብን ወደሌላ በር ለመሄድ ትንሽ አቅምና ፍላጎት ሰላጣን፤ ተነሥ መፍትሔው ተገኝቷል ብንባል እንኳ ከተሳሰርንበት አልጋ ወርደን ለመራመድ ጉልበቱ ከድቶናል። ወደ አብ የሚወስደውን በር ለማግኘት ብዙ ጊዜ የምናሳየው ፍቃድና የውስጥ ስሜት በጣም የተደበተ ስለሆነ፤ ከበር በር ስንከራተት፣ ከሃይማኖት ሃይማኖት ስንለዋውጥ፣ ከሰው ሰው ስንገለባበጥ ቀኑ እየመሸብን መጣ። ምንድነው የሚሻለው? ለምን ወደ አብ የሚወስደውን በር ለማግኘት አልቻልንም? እንደተንከራተትን እስከመቼ ነው እስኪ አስቡት?

ቃሉ እንዲህ ይላል። "እኔ የበጎች በር ነኝ። በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፥ ይገባልም ይወጣልም መሰማሪያም ያገኛል።"

**ክፍል - 3**

## ማስቀደስ እንጂ መቀ'ደስ ያቃተው ክርስትናችን

## ቅዱስ ቁርባን ይቀሰፋል ?

በተወደደች ቅድስት ቤተክርስቲያን ከሚከናወኑ መሠረታዊ ሥርአተ አምልኮ የእምነት ምግባሮች መካከል ቅዳሴ ትልቁን ድርሻ ይወስዳል። ቅዳሴ የቤተክርስቲያን ማገር ነው። ያለ ቅዳሴ ጊዜና እውነት ቤተክርስቲያን ቤተእግዚአብሔር ትሆን ዘንድ አይቻላትም። የሰማይ ሥርአት በምድር ላይ የመሆኑ የመገለጫው ገጽታ አንደኛው ክፍል ቅዳሴ ነው። ጌታችንም ጸሎት አስተምረን ባሉት ጊዜ << ፍቃድህ በሰማይ እንደሆነች ሁሉ በምድርም ትሁን >> የሚለውን የምስጋና ጸሎት ሲያስተምራቸው፤ በሰማይ እንደምትመሰግን ሁሉ፣ በሰማይ እንደምትመለክ ሁሉ፣ በሰማይ እንደምትቀደስ ሁሉ በምድርም እኛ እንቀድስህ ዘንድ ፍቀድ ማለትን አሰለጠነን። ስለዚህ በሰማይ ቅዱሳን መላእክት በሚያመሰግኑበት ምስጋና በአንድነት በምድር የምናመሰግንበት አንደኛው የሐዲስ ኪዳን የአማኑኤልነት ስጦታችን ቅዳሴ ነው። ቅዳሴ እግዚአብሔር በምሕረቱ ዘመን ከመላእክቱ ጋር ብቻ ሳይሆን ከኛም ጋር ሆነ ብለን ስሙን የምንይዝበት የሃይማኖት ተግባራችን ነው። በሰማይ መላእክት ዘወትር ይቀድሳሉ፤ በምድር

ቅድስት ቤተክርስቲያናት ዘወትር ይቀድሳሉ። ስለዚህ በዘወትር ጸሎት የምንለው << ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች ሁሉ እንዲሁም በምድርም ትሁን >> ማለታችን ጸድቀልን በክርስትናችን ጉዞ ውስጥ በቅዳሴውም በኩል ይነበባል።

የሰማይ ቅዳሴ እና የምድር ቅዳሴ በምን ይለያያሉ? ከሚለያዩባቸው ነገራት መካከል አንደኛው << ቅዱስ ቁርባን >> ነው። "በሰማይ የምትኖር አባታችን ሆይ፥" ስንል ልዑል አምላክ በጸጋውና በፍቃዱ መኖሪያ ይሆን ዘንድ የወደደው ሰማይን እንደሆነ እንጠቅሳለን። በምድር እግዚአብሔር አይኖርም ለማለት ሳይሆን፤ ይገለጥበት ዘንድ የፈቀደው ስፍራ ሰማይ ነው ለማለት ነው። እነሆ በሰማይ ተገልጦ በሃያ አራቱ ካህናት ሰማይ ሱራፌል፣ በጸዘወርተ መንበር ኪሩቤል እና በቅዱሳን መላእክትና ጻድቃን ሁሉ ሲመለክ፤ በምድር ደግሞ ለመለገጫው ይሆን ሥጋ ሕብሥቱና ደመ ወይኑ በቅዳሴ በኩል ይፈተታል። ምክንያቱም በሐዲስ ኪዳን እግዚአብሔር ምን ሆኗል? ከኛ ጋር ሆኗል። አማኑኤል ሆኗል። ስለዚህ በሰማይ ያለው አምላክ በምድርም ከኛ ጋር ይሆን ዘንድ ሕብሥተ ሥጋው ተቀድሶ ሥጋ መለኮት፤ የወይኑ ጽዋ ተለውጦ ደመ መለኮት ሆኖ ለኛ ይዘጋጃል። በመሆኑም በሰማይ በቅዱሳኑ የሚመለከው አባት በምድር እኛ ውስጥ ቅዱስነቱን ይዞ ያድር ዘንድ ሥርአተ ቁርባን የቅዳሴ ትልቁ አካል ሆኖ ዘወትር ሥጋና ደሙ ይዘጋጃል።

ዛሬ ክርስትናችን ውስጥ ቅዳሴ እንጂ መቀ'ደስ የለም። ነጠላ ለብሰን፣ የጸሎት መጽሐፍ ይዘን፣ ሰዓትና ጊዜውን ጠብቀን ለቅዳሴ ቀመን አስቀድሰን እንመጣለን እንጂ ተቀድሰን አንመጣም። በቅዳሴው ዜማ ውስጥ በእያንዳንዱ ክፍል ስሙ የተወደሰው ሕያው አምላክን ከውስጣችን ይዘን አንመለስም። ስለዚህ አሁን አሁን ለቅዳሴ መቆምም እያቃተን፤ እንደምንም ሞልቶልንም ስንሄድ በቅዳሴው ሰዓት ገሚሱን በዓለም አሳብ ጭው ብለን እየጠፋንበት፣ ገሚሱን ፍዝዝ ብለንበት፣ የተቀረውን ትንሽዬ ደቂቃ ከካህናትና ዲያቆናት ጋር አብረን አዚመን እንመለሳለን። ቤተክርስቲያን ገብተን የሌሎች ምዕመናን አቋምና ገጽታ አጥንተን እንመለሳለን። ቤተክርስቲያን ገብተን ስንወጣ አሊያ ቅዳሴው ሲጠናቀቅ ቤተክርስቲያን እንደነበርን የምናስታውስ ጥቂቶች አይደለንም። አየህ መቀ'ደስ የሌለው ልቦና? መቀ'ደስ ያጣ ማስተዋል? መቀ'ደስ ያጣ ጽናት? መቀ'ደስ ያጣ የሃይማኖት ጉዞ? እንዳይቀር ያህል የሚከናወን ውስጡ ግን የፍላጎትና የተስፋ ፍቅር የሌለበት ሌጣ ይሆናል በቃ።

በዚህ በመጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ ምዕራፍ 3፥5 ላይ ስናነብ እንዲህ ነው የሚለው። " ኢያሱም ሕዝቡን። ነገ እግዚአብሔር በመካከላችሁ ድንቅ ነገር ያደርጋልና ተቀደሱ አለ።" ነገ እግዚአብሔር በመካከላችሁ ድንቅ ነገር ያደርጋልና ምን በሉ? ተቀደሱ። እሺ ታዲያ መቼ ነው የምንቀደሰው? መቼ ነው ወደ ውስጣችን ቅዱሱን አምላክ የምናስገባው? መቼ ነው ከሥጋና ደሙ ቅድስና የምንካፈለው?

መቀ'ደስ ከትውልድ መካከል ሲጠፋ ለነገ የሚቀየው የእግዚአብሔር ድንቅ ነገር አይደለም። የሰይጣን ክፉ ነገር ነው። ይኸው እኮ መቀ'ደስ ያቃታቸው ዘመን፣ ጊዜ፣ ቤት፣ ኑሮ፣ ገንዘብ፣ ዕድል፣ ጤና፣ ሰላምና በረከት መልሰው እያስጨነቁን፤ እንዲሁ ስንዋትት ስንዋትት፣ ስናስብ ስናስብ፣ ወዴት እንደምንወጣ ወዴት እንደምንወርድ ግራ እየተጋባን፣ መፍትሔ ከችግር ጋር እየተሳሰረብን ወደፊትም ወደኋላም መሄድ ሳንችል ቀርተን በሕይወት አዙሪት ተዳክመን ዕድሚያችን ያስጠላን ክርስቲያኖች በየቤቱ መከራ እያየን ነው። ለምንድነው ይሄ ሁሉ? ምክንያቱም ለቅዳሴ መቆም እንጂ በቅዳሴ ተቀድሶ የተዘጋጀውን ቅዱስ ቁርባን ለመውሰድ ስላልቀረብን በአጥፊ መናፍስታዊ ስውር አሠራር የመጣው የሕይወት የእርግማን ፍሬ በመገለጡ ነው።

በተለይ በኛ ዘመን ውስጥ መነሻው ከየት እንደመጣ የማይታወቅ አረማዊ ትምህርት በቤተእግዚአብሔር ሰዎች ጭምር ሲነገር ይሰማል። ቅዱስ ቁርባንን ሊወስዱ የተገቡት << ሕፃናት እና አዛውንታን >> ናቸው ሌሎቻችሁ ያለ ዕድሚያችሁ ስትቀርቡ ትቀሰፋላችሁ የሚል የሰይጣንን ጠባይና አሠራር የሚያግዙ ድምፆች በብዙ ቦታዎች ውስጥ በማኅበረሰቡ አኗኗር መካከል ዘልቀው ገብተው ይሰማሉ። አንዱ እንግዲህ በክፉ ሠራዊት ለመያዛችን ሁነኛ ማስረጃ ሆኖ የሚቀመጠው ማስረጃ ይሄ ነው። በተለይ በወጣቱ የትውልድ ክፍል ቅዱስ ቁርባን እንደ ትልቅ

ሽክምና አስፈሪ ጉዳይ ምናቡ ውስጥ ተስሎ ስለተቀመጠ፤ እንኳን ሊቀርብ ቀርቶ አሳቡም በጭራሽ ከሕሊናው አይመጣም። እጅግ ደግሞ አሳዛኙና አስከፊው እውነታ ደግሞ ንስሐ ለመቀበል በየቤቱ የሚመጡት ካህናት ትውልዱን ከንስሐ በኋላ ወደ ቅዱስ ቁርባን ከመውሰድ ይልቅ እያራቁት፤ ቀይ ገና ነህ ታጠፋለህ ሲሉት፤ ቁርባን ለትልቅ ሰው ነው ሲሉት፤ ወጣት ይሳሳታልና አይቆርብም ሲሉት፤ ከመቀ'ደስ ሕይወት የራቀው ትውልድ ቀልብ ጠፋው። ፍቅር ጠፋው። እፎይታ ጠፋው። ግራ ቀኝ ማጤን ጠፋው። ረድኤትና ጸጋ ጠፋው። ያልተቀደሰች ነፍስ ነዋ በቃ። የጌታዋን ሥጋና ደም መኖሪያ ያላደረገች የሰውነት ቤት የመቅደስ ሰላም የላትም። ይሄው የውስጠኛ ሕይወታችን ሰላም የማጣቱ ተጋቦት ወደቤትና ቤተሰባችን የተሻገረ ሲሆን ቤታችንም መቀ'ደስ አቅቶት ለብቻው ተሰቃየ።

ዛሬ ቤቶች ተሰርተው፥ በቀንጆ መልክና ግንባታ ታይተው፥ ግን የታሰሩ ቤቶች ብዙዎች ናቸው። ቤቶች በሚታሰሩበት ጊዜ ውስጣቸው የሚያድሩትም ሰዎች የታሰሩ ይሆናሉ። ተኝተው ይባንናሉ፣ ሰላም ያጣሉ፣ ሲጨነቁ ውለው ያድራሉ፣ ፍቅርና ደስታ ይርቃቸዋል፣ በረከትና ሞገስ ይሸሻቸዋል። የብዙዎችን ቤት ዛሬ ላይ ብንመለከት ፍቅርና አንድነት አልባ የሆነበትን ገጽታ እናስተውላለን። አባትም በፊናው ይሮጣል። እናትም በራሷ ትሮጣለች። ልጆችም ይሯሯጣሉ። ግን በረከት የለም። ከወር እስከ ወር የተለፋበት ነገር፤ የት እንደገባ ግራ ይጋቡና መልሰው ደሞ እርስ በእርስ ይጣላሉ። "እኔ ለቤቴ እየለፋሁ፣ ቀንና ሌት እየዳከርኩ፣ አቅሜን አሟጦጩ እየደከምሁ፣ ለምን አታግዙኝም? ለምን የኔን ድካም አትረዱም?" እየተባባሉ ይጣላሉ። የአንዱን ድካምና ውጣ ውረድ አንዱ እየናቀ እየቃለለ፤ ሌላውንም ተጠያቂ እያደረገ የሚጨቃጨቁ ቤተሰቦች ለቁጥር የሚያታክቱ ቤተሰቦች ገመና ነው። ከጀርባቸው ተሰውሮ የሕይወታቸውንና የኑሮአቸውን ሩጫ ግን ገለባ የሚያደርገው ጠላት ቤቱን አስሮታል። በዘመናችን ሰዎች ወህኒ ሳይወርዱ ቤት ውስጥ እያሉ ነጻነትና ሰላም፣ ደስታና እፎይታ አጥተው የታሰሩበት ጊዜ በኛ ትውልድ ተባብሶ ይገኛል። ቤት ውስጥ ጨሌ ይዘው ለዘመናት የቀየ ቤተሰቦች ልጆች ወልድው ዘር በሚተኩበት ጊዜ፤ የባዕድ አምልኮዋቸው ውጤት በዛው የትውልድ ሐረግ ውስጥ አቀራርጦ ስለሚመጣ፤ የሚወለዱት ልጆች ያንኑ የኃጢአት እርግማን የሚገልጡ፣ ምስጋና የማይወዱ፣ ለመንፈሳዊ ሕይወትና ጉዞ ምንም ደንታ የሌላቸው ወይንም እምነትን የሚያናንቁ፣ ቋንቋቸው የተደበላለቀና ሁለንተናዊ መቀዛቀዝ የሚታይባቸው ይሆናል። መቀ'ደስ እኮ ስለተለየን ነው ኅበዝ። መቀ'ደስ ሲጠፋ በመጀመሪያው ሰላም ይጠፋል። ሰላም ሲጠፋ፥ ጭቅጭቅ፣ ንትርክ፣ ኩርፊያ፣ ጸብ፣ ብቸኝነት በቤቱ ይነግሳል። እንደቤተሰብ ሳይሆን እንደ ባላንጣ ለመኖር ሰዎች ይገደዳሉ። ቤት ገብቶ ሰላም ባጣ ሁኔታ ከመቀየት ውጪ በየመጠጥ ቤቱ ማምሸት አማራጭ ያደርጋሉ። ጌታችን ለሐዋሪያቱ እንደዚህ የሚል ቃል እንዳስተላለፈላቸው በሉቃስ 10፥5 ላይ እናገኛለን። " ወደምትገቡበት ቤት ሁሉ አስቀድማችሁ። ሰላም ለዚህ ቤት ይሁን በሉ።" ምን በሉ አላቸው? ሰላም ለዚህ ቤት በሉ አላቸው። የሰላም አምላክ የሰላምን ዋጋ ያውቃል። የመንፈስ ቅዱስ ሰላምና እረፍት ያጠረው ቤት፤ በፍጹም ሰላማዊ መሆን አይችልም። ለብርጭቀና ለሲኒ የተመቸ ቦታ ሰጥተን ስናበቃ፤ ለእግዚአብሔር የሚሆንን ቦታ ለቤታችንም ስላጣን በመቀ'ደስ ጊዜና ኑሮ ውስጥ የሚመጣውን በረከትና ሐሴት ለማጣጣም እንዳንታደል መናፍስት የዘመናችንን መንፈሳዊ መስመር አቅጥነውብናል። እንደዚህ በሚሆንበት ጊዜ ቤቱ በራሱ ነገር ተሸካሚ ይሆናል። አንዳንድ ጊዜ ቤተሰቦች ሰላም ለመባባል የሚንቀራፈፍ አንደበታቸው፤ በትንሽ ነገር ለመጋጨት በጣም ቅርብ ይሆናሉ። ስለዚህ ልጆች በየጫትና ሺሻ ቤቱ ለመዋል ፍቃዳቸውን ስለሚሰጡ፤ በዛ ቦታ ላይ በሚያገኙት በሱስ የናወዘ ጊዜያዊ ደስታና ሰላም የቤታቸውን ትኩሳት ያበርዳሉ። የክርስቶስ ሥጋና ደም በረከት ከቤቶች ሲርቅ፤ በአንፃሩ ሊኖር የሚችለው የርኩሳን መናፍስት ወረራና የምቀኞች የክፋት ሴራ የተተበተበበት የእርግማን ፍሬ ለመሆኑ ምንም አያጠራጥርም። አያችሁ? ለካ በሐዲስ ኪዳንም ቤቶች ይጨነቃሉ። ቤት ስንገባ የምንቃዥ፣ የሚከብደን፣ የሚጫጫነን፤ ቤት ውስጥ ስንቀመጥ የሚደብተን፣ የምንታመም፣ የምንፈዝ፤ በቤት ውስጥ ቤተሰቡ እሳት ጎመራ የሆነበት፤ እናት ከአባት የሚነታረኩበት ቤት፣ ልጅ ከእናት አባት የሚጣላበት ቤት፣ መደማመጥ የራቀበት ከሆነ ጌታውን ያጣ ቤት ነው ማለት ነው። ቅዱስ ቁርባን የማይቀበሉ ቤተሰቦች ያሉበት ቤት የጌታ ቤት አይደለምና።

## ቅዱስ ቁርባን ይቀስፋል ?

በዘመናችን በተለይ ከታዳጊው እስከ መካከለኛው የዕድሜ እርከን ያለው የሕብረተሰብ ክፍል ከቅዱስ ቁርባን የሸሸበትና ሥጋና ደሙን ከመውሰድ ተራራ መሸከም፣ መከራ መሸከም፣ ስቃይ መሸከም የሚቀለው ትውልድ የተፈጠረበትን ምክንያቶች ስንመለከት የሚከተሉት ይሆናሉ። አንደኛ የመናፍስቱን ዓለም ሚስጢራዊ አካሄድና የረቀቀ ስልት ካለመረዳት የሚመጣ የጎደለ አመለካከት፤ ሁለተኛ አገልጋዮች በእውነት መንፈስ የተተረጎመና በምግባረ ክርስትና የተቃኘ ጠባይና ልምድ ከአገልግሎታቸው ስለጠፋ የዘልማድ ስብከትን ብቻ ደጋግመው እየጮኹ አጥፍቶ ጠፊ በመሆናቸው እና በሦስተኛው በአረማውያንና በድብቅ አጀንዳ አጠንጣኝ የዲያቢሎስ እጆች በሆኑ ሰዎች የተነሣ የተሰራጨው የተዛባና ፈጽሞ ከእውነት የራቀ ትምህርት በፈጠረው የጠራና የተስተካከለ አለመረዳት ምክንያት ነው።

ይኸውም ትምህርት ምንድነው ሰዎች በወጣትነት ዕድሜያቸው ቅዱስ ቁርባን ከወሰዱ፤ ቅዱስ ቁርባን ከወሰዱ በኋላ ፍጹም የሆነ ኑሮን መምራት ተስናቸው ኃጢአት ከሠሩ፤ ለቅዱስ ቁርባን የሚያስፈልግ አልባስ ሳያዘጋጁ ቢቀርቡ፤ በድፍረት ሥጋና ደሙን በመውሰዳቸው እንደሚቀሰፉ የሚያትት ውስጠ ሰይጣን ትምህርት ነው።

ወገኖቼ ክርስቶስ የሚያፈቅር እንጂ የሚቀስፍ፣ የሚያከብር እንጂ የሚያዋርድ፣ የሚያነሣ እንጂ የሚጥል፣ የሚሰበስብ እንጂ የሚገፋ አባት አይደለም። እንኳን ሰዎችን ሊያጠፋ፤ የጠፉ ሰዎችን ሲያይ የሚያለቅስ የዋህ አባታችን እንደሆነ ኢየሩሳሌምን ባየ ጊዜ እንባው ሲፈስ ገርነቱ ተገልጧል። ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች አትቁረቡ ትቀሰፋላችሁና የሚል ማንኛውም አስተምህሮ የዲያብሎስና የዲያቢሎስ ብቻ ነው። በእርግጥ የጌታን ሥጋና ደም ሳይ'ገባን መውሰድ አይፈቅድም። መጽሐፍ ቅዱስም " ስለዚህ ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት።" (1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 11፥27) ይላል። ይሄ ቃል የተገረው ግን በክርስቶስ ስም ላላመኑ፣ አምነውም ላልተጠመቁ፣ የጌታን ክብርና ኃይል ላቃለሉ፣ ስሙንና ፍቅሩን ለገፉ፣ የቅዱስ ቁርባንን ኃይልና በረከት ለመፈታተን የሚቀበሉ፣ ለሌላ ተልዕኮና ዓላማ ለቀረቡ፣ ለማንጓጠጥና ለማሾፍ ብለው ሊወስዱት ላሰቡ እንጂ በዐርባ በሰማንያ ቀን ተጠምቀን በስሙ ማኅተብ አስረን ንስሐ ለተቀበልን ክርስቲያኖች ፈጽሞ አይደለም። ይሄንን በአንክሮ መረዳትና በአጽንዖት ማጤን ያስፈልጋል።

ቅዱስ ቁርባን ለመውሰድ የዕድሜ ገደብ ፈጽሞ የለውም። በምንም መንገድ በዚህ ዕድሜ የተገኘ ሰው አይቁረብ የሚል ትምህርት ቤተክርስቲያን አታስተምርም። ወጣት ከሆንክ ስለምታጠፋ አትቁረብ የሚሉት የምግባረ ክርስትና ሕይወትና አቋም በአኗኗራቸው የማይገኝባቸው፤ ስለ አምልኮት ሕይወትና ስግደት የማያውቁ፤ የጸሎትና የመንፈሳዊ ልምምድ በቤታቸው የሌላቸው፤ ስለ መንፈሳዊ ጥፋቶችና ጉዳቶች ጥልቅ ግንዛቤ የሌላቸው የዘልማድ የቤተክርስቲያን አገልጋዮችና ሰዎች እንጂ ቅድስት ቤተክርስቲያን አይደለችም። ቅድስት ቤተክርስቲያንማ ዘወትር ቅዳሴ ቀድሳ ሥጋና ደሙን አዘጋጅታ ምዕመናኖቿን ከበጉ ማዕድ ታቋድሳለች እንጂ "አትቁረብ" የምትለው ወጣት የለም።

ሌላው አንድ ግለሰብ ቅዱስ ቁርባን ከተቀበለበት ጊዜ ጀምሮ የቅድስና ሕይወት ከሌለው ይቀሰፋል የሚባለው ሙሉ በሙሉ ሐሰት ነው። እንዲህ ቢሆንማ ስንት ሰው እስከአሁን ተቀስፎ አልቆ ነበረ። ትናንት ቀርበው ዛሬ ሃይማኖት የካዱ፣ ትናንት ቀርበው ዛሬ ክር የበጠሱ፣ ትናንት ቀርበው ዛሬ በዝሙት የወደቁ፣ ትናንት ቀርበው ዛሬ የሚዘርፉና የሚያዘርፉ፣ ትናንት ቀርበው ዛሬ የሚዋሹና ሲያሙ የሚውሉ፣ ትናንት ቀርበው ዛሬ በሱስ በአደንዛዥ ዕፅና መጠጥ የተወረሱ፣ ትናንት ቀርበው ዛሬ ሲሰዳደቡና ሲጣሉ የሚገኙ፣ ትናንት ቀርበው ዛሬ በየስርቻውና አደባባዩ ሰው የሚያጠፉና የሚያስጠፉ እልፍ አገልጋዮችና ምዕመናን አሉ። ታዲያ ይሄ መቅሰፍት ከቅዱስ ቁርባን በኋላ ለሚያጠፉት የታዘዘ ቢሆን እነዚህ ሰዎች እንዴት ከመቀሰፍ ይልቅ በክፋት ላይ ክፋት፣ በኃጢአት ላይ ኃጢአት፣ በበደል ላይ በደል እየፈጸሙ ሊቀዩ ይችላሉ? እሺ ሕፃናትንስ ኃጢአትን አገናዝበው ለመሥራት ስላልበቁ

ከመቅሰፍቱ አመለጡ ብንል ቀርበው አሁንም ግን በየሰፈሩና መንደሩ በቀደመ ግፍና ክፉ ባሕሪያቶቻቸው የተገኙ አዛውንታንና ትልልቅ ሰዎች የሉንምን? ልብ ሰጥታችሁ ልታስታወሉ ይገባል።

እንዲሁ ቅዱስ ቁርባን ለመውሰድ የተለየ ልብስ ካላዘጋጃችሁ አይቻልም የሚል የኑፋቄ ትምህርት የሚያሰሙ አሉ። ይሄም የመናፍስት ተንኮልና ሕዝበ ክርስቲያኑን ከሥጋና ደሙ ለማራቅ ዲያቢሎስ የተጠቀመበት ድብቅ ሴራ እንጂ እውነት አይደም። ክርስቶስ በልብስ መጽዳትና መቀሸሽ ልክ ሰውን የሚያቅፍ የሚዛን አምላክ አይደለም። የእርሱ ሚዛን ልብህና ውስጣዊ እውነትህ እንጂ ልብስህ አይደለም። ቢኖርህና ቢሆን ሙሽራ መስለህ ሥጋና ደሙን ብትወስድ እሰየው። ካልተቻለ ግን ያለውን አጽድተህ ለብሰህ መቁረብ እንጂ ለብቻ የተለየ ልብስ ከሌለኝ አልቀርብም ማለት ሰይጣንን ለማገዝና ለማጽደቅ በጣም ሰፊ አጋጣሚ የሚሰጥ የመናፍስት ግፊት ነው።

እንግዲህ በቅዱስ ቁርባን መቀ'ደስ ባለመቻላችን ምን መጣ? የሚለውን ለመለየት ኑሮአችንን መመልከት ነው። በተለይ እጅጉን ከአምልኮትና ከሥጋና ደሙ በረከት የራቀው የወጣቱ ትውልድ በሁሉም መንገድ የታሰረ ተንቀሳቃሽ እስረኛ ሆኖ አረፈው። በሱስ የታሰረ፣ በአመል የታሰረ፣ በድካም የታሰረ፣ በፌዝ የታሰረ ሆነ። ዛሬ የወሲብ ፊልም እንደሚበላው የሚጠጣው የዕለት ልማዱ ሱስ የሆነበት ወጣት በየቤቱ እጅግ ለቁጥር የታከተ ነው። በመናፍስት ወጥመድ ወድቀ በአጥፊ አደንዣዥ ዕፆች ጥገኝነት ላይ ታስሮ ያለው ወጣት እጅግ ብዙ ነው። እስኪ ማን ነው ለትውልዱ እውነተኛ ስጦታ ሰጠ የምንለው በዚህ ጊዜ? ብዙ በጣም ትልልቅ ሰዎች ትልልቅ ቤቶች ሠሩ ለልጆቻችን ብለው፥ ብዙ ገንዘብ ውጪ አገር ለፍተው ሁሉ ሳይቀር አከማቹና አጠራቀሙ። እነዛ ልጆች በመንፈሳዊ ሕይወት በምንም በመንገድ ያልተባረኩ ስለሆኑ፤ የአባቶችም እጅ ያንን ሲገነባ ከክፉ መንፈስና ኃጢአት ጋር ስለሆነ፤ ልጆቹ ያንን ሊበሉ አልታደሉም። ቢበሉም እንኳን ከአመልና ከሱስ ጋር ስለሆነ ከአንድ ማኅፀን የወጡት ልጆች፥ ዘመዳሞች እርስ በእርሳቸው ይጋደላሉ፤ እርሰ በእርሳቸው ይጣላሉ፤ አርስ በእርሳቸው ይካከሳሉ። አሁን እኮ እንዴት ነው መታሰራችንን በአንድ ጊዜ እንደጋራ የመጣብን ፍዳ ስለሆነ፤ የተለየ ትኩረት ሰጥተነው የሚገርመን ከእስራት የተላቀቀ ሰው ስናይ ነው። መታሰራችን አይገርመንም። በፍጹም አይገርመንም። ይህ ሁሉ ታድያ መንፈሳዊ በረከትን ለወጣቶች ላለመስጠት ያደረግነው ጉዞ ከራሳችን የሥጋ አሳብ ጋር የተራመድነው እርምጃ ሰማያዊ አምላክን ሳንጨምርበት የሄድነው ሕይወት ያስከተለው ውጤት ነው።

## ክፍል - 4

## ልጆቻችን ምን ሆኑብን?

### ሰው ሰይጣን ሰይጣን ሰው ሆነ

ከአዳምና ሔዋን መተላለፍ በኋላ የመጀመሪያው የኃጢአት እርግማን በቃየን ሕይወት ሲገለጥ፤ የርኩሳን መናፍስትና የሰው ልጆች በግፍ ሥራዎችና በአመፃ ኑሮዎች የመተሣሠር አካሄድ ከዘመን ዘመን እየጨመረና በስልት በአሠራር እየረቀቀ ዛሬ የምንገኝበት ሁኔታ ላይ እንዲህ ለመገኘት እነሆ ተገድደናል። በቃየን ሕይወት የተገለጠቺው አጋንንትም የኃጢአት ክስ መነሻ ሆና ትውልዱን ገና ከማለዳው ጀምሮ ከማኅፀን አንስቶ በመዋረስና አብሮ በመወለድ፤ የሰውን ልጅ የትውልድ ዘር ውስጣዊ ማንነት ላይ የራሷን ጊዜ፣ ቦታና ስፍራ በማበጀትና በማመቻቸት ከእግዚአብሔር አምላክ ሰማያዊ የሕይወት ጉዞ እያስወጣች፤ የቅድስና አምባዎችንና የበረከት ጎዳናዎችን ከሰው ልጆች ኑሮ እያራቀች፤ በጠመመው መንገድ ላይ ረጅም ርቀትን እንዲጓዝ እያደረገች ገና ከንጭጩ የተኮላሸ ዘር እንዲኖር ለረጅም ዘመናት ያለማቋረጥ ሠርታለች። " *መልካም ብታደርግ ፊትህ የሚበራ አይደለምን? መልካም ባታደርግ ግን ኃጢአት በደጅ ታደባለች፤ ፈቃድዋም ወደ አንተ ነው፥ አንተ ግን በእርስዋ ንገሥባት።*" (ኦሪት ዘፍጥረት 4፥7)

በቃየን የፊት ማጥቆርና ማጨለም ገጽታ የተነበበው የመናፍስት ውስጣዊ ሕይወትን የመቆጣጠር አሠራር በትውልድ ሐረግ ውስጥ  ዘልቆ እንዲገባ መናፍስታዊ የዘር ውርርስን በማከናወን በሚወለዱ ልጆች ላይ ልክፍት እየሆነ፤ ቁራኛ እየሆነ፤ አብሮ አድጎ እየተማረ፣ እየሠራ እና ኑሮን እየተከተለ ባሕሪይን ሙሉ በሙሉ በመዋረስ ሰው ሰይጣን፤ ሰይጣን ሰው የሆነበትን የርኩሰት አንድነት በከፍተኛ ግፊትና ፍጥነት ዘመኑን በሚመስል ጥበብ ድብቅ መናፍስታዊ አጀንዳዎችንና መሬት የረገጡ ጥፋቶችን በማስፋፋት፤ ከአድማስ ጫፍ እስከ ሌላኛው ጫፍ ሥር ነቀል ትውልድን የመያዝና የመላመድ ሂደትን ወደ ምድር የተጣሉት ጽልመተ መላእክት ለዘመናት አረጋግጠው በመሥራታቸው ሳቢያ ይኸው ዛሬ በእግዚአብሔር አምላክ ሰማያዊ ኃይልና በጽድቅ የሚመራ ትውልድ እንዲጠፋ ሆኗል። የዛሬው ደግሞ የኛ የነፈዘውና በዘመኑ የዓለም መዘውር ብቻ የአኗኗሩን መሠረት የገነባው፤ ውስጣዊ ማንነቱ ከታሪኩ ጋራ የጠፋው ትውልድ መናፍስት በሰው ልጆች ዘር እንደሚወራረሱ ከነ አካቴውም ባለመገንዘቡ እንደገና እንደ አዲስ በግብ ግብ እየተማረ መሆኑን ያለበት ሁኔታን ስንመዝን፤ ምን ያህል ከአባቶች መንፈሳዊ አቋምና ገጽታ ሸሽተን የተገኘንበት የትናንት ቀይታዎቻችን ለዛሬ ዘርፈ ብዙ ድቀትን እና ማኅበረሰባዊ ኪሣራን እንዳስከተለ ለመረዳት እንችላለን።

## የመናፍስት በዘር ትውልድ ውስጥ የመተላለፍ እውነታ እንዴት ነው?

አንድ ቤተሰብ አንደኛ፥ ባዕድ አምልኮት እንደ ጨሌ፣ አቴቴ፣ አዳል ሞቲ፣ ወሰን ገፊ፣ ወሰን ገላ፣ ውቃቢ፣ አርሜት፣ ደማሜት፣ ራሔሎ፣ ሐጎስ፣ አመቺሳ፣ ጠቋር እና ለሌሎችም ለዛር የአከባቢ መናፍስት ከጥንቆላና ድግምት ጋር የተያያዘ መናፍስታዊ ግብሮች ሲገብር የቆየ ከሆነ፤ ሁለተኛ፥ በመተት፣ በዓይነጥላ፣ በቡዳ መናፍስት የታሠረ ከሆነ፤ እንደ መስተፋቅር፣ መስተባርር፣ ዕፀ ፋሪስ፣ አረማዊ መፍትሔ ሥራይ እና ሌሎች የመናፍስት የአሠራር ድጋፎች ላይ የቆየ ከሆነ፤ በሕይወቱና በቤቱ ውስጥ ለዘመናት በግብር በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የተገለገለው ሰይጣን ሚቀጥለው የቤተሰቡ የትውልድን ሐረግ ለመሻገር የቀደመው የኃጢአት ተግባርና ጊዜ ድልድይ ስለሚሆነው ገና በጽንስ ላይ ያለ ልጅን ለመያዝ ምንም አያግደውም። አሁን በዚህ ሁኔታ ተወራርሰው አብረው በሚወለዱ መናፍስት 95% የሚሆነው የትውልዳችን ክፍል በመናፍስት አገዛዝና ተጽዕኖ ኑሮውን ከባላጋራ ጋር ይመራል።መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዓለም የመጣው ይህንን የመናፍስት ውጤት የሆነውን የዘር ውድቀት ሊሽርልን ነበረ። " የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ፥ እንደ ሰዶም በሆንነ እንደ ገሞራም በመሰልነ ነበር። " (ትንቢተ ኢሳይያስ 1፥9) የትውልድ እርግማን የሚጠፋው ትውልድን በመቀደስ ውስጥ በመሆኑ የአብርሃምን ትውልድ አስቀርቶ ቀድሶ ወገናችን ከምትሆን ከእመቤታችን ድንግል ማርያም እግዚአብሔር አምላክ ተወለደ። በመወለድ አስጀምሮ ሲቀድስን በድንግል ማርያም ላይ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ይዞ መጣ። " መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት። መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፥ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል።" (የሉቃስ ወንጌል 1፥35) በዘር ውስጥ እየተወራረሰ በኃጢአት ማደሪያነት በኩል ሲያልፍ የነበረው የዲያብሎስ ሠራዊት ወደ ድንግል ማርያም የተቀደሰ ትውልድ መዝለቅ አልቻለም። " መሠረቶቹ በተቀደሱ ተራሮች ናቸው፤" (መዝሙረ ዳዊት 87፥1)

ከአንቺ የሚወለደው ከሚለው ቃል አስቀድሞ የቀደመው፤ የልዑል ኃይል ይጸልልሻል የሚለው ነው። መንፈስ ቅዱስ በእርሷ ሆኖ እንደ መጋረጃ የከደናት፤ ቃል ሥጋ የመሆኑ ሚስጢር ከፍጡራን ሁሉ ይደበቅ ዘንድ ነው። ሚስጥረ ሥጋዌ መባሉ ይህን ልዩ የእግዚአብሔር ጥበብ በፍጡራን ልዕልና ለመመርመር ባለመቻሉ ሲሆን፤ ስለዚህ በእመቤታችን ውስጥ የጸለለው መንፈስ ቅዱስ፤ የቃልን መወለድ ሚስጥር ሲያደርገው፤ ሰይጣን በድንግል ማርያም ማኅፀን የተገኘው የአብ ልጅ ስለ መሆኑ ምንም መረጃ አጣ። ዛሬ ሕፃናት ሲወለዱ መንፈሱ ስለተወለደው ልጅ መረጃ ስላለው አብሮት ይወለዳል። ታዲያ ገና ከማለዳው ጀምሮም ይቀራኘዋል።

ታዲያ እሺ ከመንፈሳዊ በረከትና ጥበቃ ርቀው፤ በዲያቢሎስ የመረጃ ቅርበት ሥር የተወለዱ ልጆቻችን ምን ሆኑ? ብለን ስንመለከታቸው መፍዘዝ፣ መደንገዝ፣ ብዥ ማለት፣ ግራ መጋባት፣ መጨነቅ፣ እንቅልፍ ማጣት ወይም

በአንፃሩ አብዝቶ መተኛት፣ ደንታ ቢስ መሆን፣ በትንሹ ነገር ውኃ ቀጠኑ እያሉ መበሳጨት፣ መጫጫን፣ መልፈስፈስ የማይለያቸው ድንብዥ ያሉ ልጆች ተወለዱ። ቁጭ በሉ ሲባሉ የሚነሡ፣ ተነሡ ሲባሉ የሚሄዱ፣ ሂዱ ሲባሉ የሚቀመጡ፣ ማስተዋልና የቤተሰብ ፍቅር የራቃቸው፣ ለመንፈሳዊ እውቀትና እውነት ምንም ፍላጎት የሌላቸው በሥጋ ብቻ የተወለዱ ልጆችን ይዘው የሚሰቃዩ እናት አባት በየሰፈሩና በየቤቱ ብዙ ናቸው። ሕፃናቱ ሲወለዱ የሚታዩን ለሥጋ ዓይኖቻችን ብቻ እየመሰሉን፤ በስውር የሕይወታችን ዘመን ውስጥ ሥር ሰደው የቆዩት መናፍስትም እንደሚያዩቸው እየዘነጋን የወለድናቸው ልጆች ሱሰኛ፣ አመፀኛ፣ ነውረኛ፣ ተሳዳቢ፣ ደም አፍሳሽ እየሆኑ ስናይ ነገሩ አይገባንም።

ጌታችን ግን ከመወለዱ አስቀድሞ ወደ ወላጁ ድንግል ማርያም ምን መጥቶ አድሯል? መንፈስ ቅዱስ መጥቶአል አያችሁ። መንፈስ ቅዱስ ባንቺ ላይ ይመጣል አለ ቅዱስ ገብርኤል። ዛሬ ቃልቻ ጋር ሄደን፣ ጠንቋይ ጋር ሄደን፣ መተተኛው ጋር ሄደን ንስሐ ሳንገባና ቅዱስ ቁርባን ሳንቀበል የወለድናቸው ልጆች የጠንቋዩ፣ የቃልቻው፣ የመተተኛው መንፈስ አብሮአቸው ተወለደ። ሲያድጉም አብሮ እንደባሕሪይና ጠባያቸው ራሱን እየለዋወጠ፤ ምክር የማይወዱ፣ የቤተክርስቲያንና የእምነት ጉዞ የሚጠሉ፣ እንደ ራሳቸው በመናፍስት ከተጠመዱት ጋር የሚገጥሙ፣ ጸጋና ሞገስ የሸሻቸው፣ ትምህርት የሚከብዳቸው፣ ሥራ መሥራት የሚያቅታቸው እየሆኑ የእርግማን ፍሬ የሚያፈሩ ሲሆኑ ለምንድነው ብለን አስበን ስላልጠየቅን ችግሩ አይገባንም። ልጆች ሲወለዱ መንፈስ ቅዱስ አብሯቸው እንዲኖር እናቶች አስቀድመው በጽንሰት ጊዜ በተደጋጋሚ ቅዱስ ቁርባን መውሰድ ይኖርባቸዋል። መንፈስ ቅዱስ በጸለለባት እናቱ የተወለደው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰይጣን መረጃ ርቀ በተወለደ ግዜ የመወለዱን ነገር ሲሰማ ዲያቢሎስ በሄሮድስ ልቦና ሆኖ ነበረ የደነገጠው። እስኪ የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ሁለትን ከመጀመሪያው ጀምሮ አንብቡት። መረጃ ያጣው ንጉሥና የጭካኔ መንፈሱ በቤተልሔም የተወለደው ሕፃን ማንነት ተደብቀባቸው ግራ ሲጋቡ ትመለከታላችሁ። ስለ ክርስቶስ ተወልዶ ስለመምጣቱ አስቀድሞ ዲያቢሎስ ያውቃልና 'እርሱ ነው? አይደለም?' ብሎ ሰብአ ሰገልን እንዲያጣሩለት ላካቸው። እነርሱም ወድቀው የአምልኮት ከሰገዱ በኋላ በሕልመ ራእይ የሄሮድስን በውስጥ መንፈስ ፈቃድ የሚመራ ፍላጎቱን መለየት ስለቻሉ በሌላ መንገድ ወደ አገራቸው ተመለሱ። የጠበቀውን መረጃ ያጣው ርኩስ መንፈስ በግምት ክርስቶስን ሊያስገድል ያን ሁሉ የቤተልሔም ሕፃናት ፈጀ። ይሄ መረጃ ማጣቱ ሲያስጨንቀው ከውጪ ሆኖ እየተከተለው፤ በካህናቱ በኩል ሕግ አስጠባቂ ሆኖ መጣበት። ክርስቶስ እያየው እንደሆነ ግን በፍጹም አልተገነዘበም። ጌታ ለፈሪሳውያን ከአባታችሁ ዲያቢሎስ ናችሁ ብሎ ከዘራቸው ውስጥ የቀየ አጋንንት ሲከተለው እንዳየ ነግሯቸዋል። "እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ።" (የዮሐንስ ወንጌል 8፥44)

እኛም ያለ ቅዱስ ቁርባን የተወልድን ዘሮች ስንሆን ከአባታችን ከዲያቢሎስ ስለመሆናችን ሕይወታችን ማረጋገጫ የማያስፈለገው መታያ ይሆናል። ሁላችንም በሥጋ የአኗኗር ውጥረት መካከል በጠበበ የማስተዋል መስመር ላይ ወድቀን፤ የቅርብ ቅርቡን ብቻ እያየን፤ ጊዜያችንን በትምህርትና በሥራ ብቻ አጥረን ይዘነው፤ ውስጣችን መቼ እንደታመመ እንኳ መረጃውን አጥተን ቀስ በቀስ በመጀመሪያ ከውስጥ ቀጥሎም በውጪ ገጽታችንም እየተበላን መጣን። እየተበላን መጣንና አሁንም ወደ ኋላችን ዞረን የመጣንበትን አቅጣጫ ቀመን የምናስተውልበትን አእምሮና ጊዜ አጥተነው ከባሰ ወደ ባሰ፣ ከጨነቀ ወደ ጨነቀ፣ ግራ ከተጋባ ወደ ተሰፋ ወደ ቀረጠ የሕይወት እርከን እየተሸጋገርን ዕለቶቻችን ለማሳለፍ ብቻ የምንኖር ጥቂቶች አይደለንም። በየቀኑ እየሠራን አቅማችንን አሟጠን እየለፋን የምናጠራቅመው ገንዘባችን አለን ስንለው እየከዳ ተያዘ ስንለው እያመለጠ፤ በተሰነካከለ ጎዳና የቱን ርቀት ያህል ሳናውቀው ወሰደን? መቼ ሰላም ማጣት ጀመርን? ከመቼ ጀምሮ ነው መቃዠት የጀመርነው? መቼ ነው ፍቅርና ሞገሳችን የተገፈፈብን? መቼ ነው የየግል ችግሮቻችንንና መጣሰናቸውን ተመሳስለው እንደሕብረተሰብም ጎልብተው እንደ አገር አድገው መውጫ መግቢያው እስኪጠፋን በተናጠልም በጋራም ግራ ግብት ያለን?

የችግሮቻችንን ጥያቄዎች ለማንሣትና ለመፈተሽ መጣርን ረጅም አድካሚ ጉዞ አድርገን ስለወሰድነው እንዲሁ ፈዘን መቀመጥ መርጠናል። መደንግዞቻችን ከምናስበው በላይ በራሳችን ላይ ሰልጥነው ቅርባችን ያለ ሰው

ካልተጎዳ በቀር መባነን እያቃተን፤ በርቀት ብዙዎች በአመፃ፣ በግፍ፣ በጥላቻ፣ በዘረኝነት ጎጥ፣ በትዕቢት፣ በራስ መውደድ እጆች ተጨቁነው የፈሰሰ የደማቸውን ጥሪ መስማት ተስኖን፤ የሌላው ችግር ችግራችን መሆን እያቃተው፣ የሌላው ቁስል ሳይጠዘጥዘን፣ የሌላው ስቃይ ሳይሰማን፤ ዓለምን በውድድር መድረክ ቀርጸናት ጥሎ ለማለፍ በፊናችን ከኑሮ ጋራ እንሯሯጣለን።

ከሁሉ ችግራችን ሐበሾች ማስመላችን ነው ትልቁ በሽታ። ምንም ደህና የቅድስና ሕይወት ሳይኖረን፤ አንድም የበጎነት ልምምድ በኑሮአችን ሳይመዘገብ፤ ፍቅርና ትኅትና ከሰውነታችን ከጠባያችን ውስጤ ሳይገለጡ፤ ዝም ብለን እንደሆነልን ሁሉ እናስመስላለን። በመንፈስ ቅዱስ የሚታይ ኑሮአችን ሲፈተሽ ግን ገመናችን ባዶ ነው። ባዶ ከዜሮ በታች። "ማኔ ቴቄል ፋሬስ" የሚለው ቃል በእውነት እኮ ውስጣችን ነው ቤቱን የሠራው። የቀለለ ኑሮ። የቀለለ ዘመን። የቀለለ ትውልድ። እግዚአብሔር ይማረን።

ይሄ የአገራችን ትውልድ ችግር ከዘመን ዘመን ተባብሶ ዛሬ ላይ እንዲህ ባለ ገጽታ በጋራ የመዘበራረቃችን ምክንያቱ ምንድነው? ወደሚለው ስንመጣ አንደኛው ምክንያቱ ከማኅፀን ጀምሮ በቅዱስ ቁርባን ተቀድሰን ብዙዎቻችን ስላልተወለድን ነው። እኛም እንዲሁ የምንወልዳቸውን ያለ ቅዱስ ቁርባን አስገኝተን የመከራውን ዘመን አፈጠንነው በቃ።

## የክርስቶስ ሥጋና ደም በምንወስድበት ግዜ በምን አይነት ሁኔታ ውስጥ ነው የተባረከ ፍሬ የምናገኘው ?

የተባረከ ፍሬ በተከፈተ ሰማይ በኩል ሊመጣ የሚችል መቀ'ደስ ነው። ይህ መንፈሳዊ ኃይል በዘለዓለም ሕይወት በኩል ተባርኮ የልዑል እግዚአብሔር አምላክ ሞገስ ያለበት መንፈሳዊ ተስፋ እንዲኖረው ለማድረግ ከሚያስችለን ዘዴ ዋነኛው ቅዱስ ቁርባን ነው። የተባረከ ትውልድ ለማግኘት የክርስቶስ ሥጋና ደም ያስፈልግሃል።

አንድ ልጅ ከተጸነሰ በኋላ ደጋግሞ ደጋግሞ ቅዱስ ቁርባን መወሰድ አለበት። ርኩስ ጠላት አብሮት እንዳይወለድ። የዘር መንፈስ እንዳይዘው። የዛሬይቱ አገልጋዮች ግን ከተረገዘ በኋላ ቅዱስ ቁርባን እንዳይወስዱ ደብተራው፣ ቄሱም፣ መነኩሴውም ይከለክላል። በጣም አሳዛኝ ውድቀት ነው። ለምንድን ነው? ለምን ይከለክላሉ? ቅዱስ ቁርባን እንዳይወስዱ እርጉዞችን ይከለከላሉ። ለምን? ዓይነጥላው እንዲይዘው፣ ቡዳው እንዲይዘው፣ ልክፍቱ እንዲይዘው፣ መተቱ እንዲጋባበት፣ የአስማተኞች ሥራ ተግባራዊ እንዲሆን? ለምንድነው የምንከለክለው?

እናቶች ለመሆን የሚፈልጉ ሁሉ የተባረከ ፍሬ እንዲሰጣቸው፤ እመቤታችን ድንግል ማርያም ከመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንደተቀበለቺው፤ መጀመርያ እየጸለዩ ሰማይ እንዲከፈት ኃይል እንዲቀበሉ ቁርባን ይወስዳሉ። ከጸነሱም በኋላ ይወስዳሉ። ዓይነጥላው አብሮት እንዳይወለድ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ አብሮት እንዲወለድ፤ መንፈሳዊ ጥበቃ እንዳይላላ፤ የተባረከ ፍሬ ለማግኘት የክርስቶስ ሥጋና ደም የግድ ያስፈልጋል። እዚህ ላይ አንድ ወቅት ላይ እንዲህ ነው ያለው << የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ አባቶቻችሁ መና በልተው እንደሞቱ አይነት አይደለም። >>፤ የዮሐንስ ወንጌል 6፥53 ላይ ደግሞ እንዲህ ይላል "ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የወልደ እጓለ ምህያው ክርስቶስን ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም።" የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ምንም ሕይወት የላችሁም ነው። አሁን ሕይወት አለን ወይ? አለን ያላችሁ ሁሉ፤ በሕይወት ተወልደዋል ያላችሁ ሁሉ አልተወለደም።

የተወለደው የሥጋ ልጅ ብቻ ነው። የሥጋ መልክ ፎቶግራፍ ነው። መንፈስ ቅዱስ የለውም። ሕይወቱ በእግዚአብሔር ኃይልና ጥበቃ በኩል መዝገብ የለውም። ጌታችን "ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ" አለ። በሥጋዬ በደሜ በኩል የሚመጣው ሁሉ ሕይወት አለው ይለናል። ስሙ ለዘላለም የተመሰገነ ይሁን። ስለዚህ ጥያቄውን ልናስተውለው ይገባል። ሕይወት አለን ወይ? የወለድናቸውስ ልጆቻችን ሕይወት አላቸው?

<< ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ። ሕያው አብ እንደ ላከኝ እኔም ከአብ የተነሣ ሕያው እንደምሆን፥ እንዲሁ የሚበላኝ ደግሞ ከእኔ የተነሣ ሕያው ይሆናል። ከሰማይ የወረደ እንጀራ ይህ ነው፤ አባቶቻችሁ መና በልተው እንደ ሞቱ አይደለም፤ ይህን እንጀራ የሚበላ ለዘላለም ይኖራል። በቅፍርናሆም ሲያስተምር ይህን በምኵራብ አለ። >> ይላል የዮሐንስ ወንጌል። ከደቀ መዛሙርቱም ብዙዎች በሰሙ ጊዜ "ይህ የሚያስጨንቅ ንግግር ነው፤ ማን ሊሰማው ይችላል?" አሉ። ዛሬም የክርስቶስ ሥጋና ደም የሚያስጨንቃቸው ብዙ ናቸው። የሚያስጨንቅ ንግግር ነው አሉ። ዓይነጥላቸው ከውስጣቸው ስላልወጣ፣ የዘመኑ መንፈስ ስላልራቀ፣ የሚሰሙት ባዕድ ስለሆነባቸው ተጨነቁና ይህ የሚያስጨንቅ ንግግር ነው አሉ። << ስለዚህ እንዳንጕራጕሩ በልቡ አውቆ አላቸው። ይህ ያሰናክላችኋልን? እንግዲህ የሰው ልጅ አስቀድሞ ወደ ነበረበት ሲወጣ ብታዩ እንዴት ይሆናል? ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው፤ ሥጋ ምንም አይጠቅምም፤ እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው !ሕይወትም ነው። ነገር ግን ከእናንተ የማያምኑ አሉ። ኢየሱስ የማያምኑት እነማን እንደ ሆኑ አሳልፎ የሚሰጠውም ማን እንደ ሆነ ከመጀመሪያ ያውቅ ነበርና። ደግሞ፤ ስለዚህ አልኋችሁ፥ ከአብ የተሰጠው ካልሆነ ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም አለ። >>

ተመልከቱ እኛ አሁን ተሰናከልን። ዛሬ በሕይወታችን በአብዛኛው በክርስቶስ ሥጋና ደም ተሰነካክለን ሕይወት አልባ ሆነን ስለምንኖር የተባረከ የትውልድ ፍሬ እጥረት ገጥሞናል።

ስለዚህ ለተባረከ ትውልድ ፍሬ የሚያስፈልገን የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው። አንዲት እናት ጸንሳ ካለች የክርስቶስን ሥጋና ደም ከወሰደች እስከ መውለጃዋ ግዜ ድረስ በሳምንት አንድ ግዜ፤ ከሰኞ እስከ አርብ ግዜ ድረስ ያለዉን ሁኔታ ከጸሎቷ ጋራ፤ ከአምልኮትዋ ጋራ፤ ትቀይና እሁድ ሲመጣ ትቀደሳለች። እሁድ እንግዲህ የመቀደሻ ግዜ ነው። ስትቀደስ ልጅም አብሮ ከውስጥ ይቀደሳል። መንፈስ ቅዱስ ከማኅጸን ጀምሮ ይባርከዋል። መንፈስ ቅዱስን የተቀበለቺው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወደ ኤልሳቤጥ ቤት ስትሄድ በጽንስ ውስጥ የነበረ የስድስት ወር ልጅ ዘለለ ነው የሚለው። ደስታ አሳየ ማለት ነው። በፊት ስሙ ደስታ እንደሚባል ከቅዱስ ገብርኤል ተነግሮዋል። በተጨማሪ ተተንብዮለታል። ደስታ ማለት ዮሐንስ ማለት ነው። የጸጋ ደስታ ማለት ነው። ከማኅጸን ጀምሮ በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ጸጋ የተባረከው ዮሐንስ በዘመኑ ሁሉ ቅዱስ ሆኖ፤ የጌታ መንገድ ጠራጊ ሆኖ፤ ለሐዲስ ኪዳን የመጀመር ምዕራፍ በር መሆን የቻለ ታላቅ ሰው እንደሆነ በዘመኑ ሁሉ እናያለን።

ደስታ ያለው ልጅ የሚወለደው ከክርስቶስ ሥጋና ደም ጋር ያለህ ኅብረት ሲጨምር ነው። የሚጦርህ ልጅ የሚወለደው ከክርስቶስ ጋር ስትሆን ነው። የሚያጠፋህ ልጅ የሚወለደው ደግሞ ከክርስቶስ ስትርቅ ነው። የሚባርክ ልጅ የሚወለደው ከክርስቶስ ጋር ሆነህ ሲጸነስ ነው። የሚረግምህ ልጅ የሚወለደው ከክርስቶስ መንፈሳዊ ተሰፋ ስትርቅ ነው።

ስለዚህ የሚያስጨንቅ ንግግር እንዳሉት ደቀ መዛሙርቱ ዛሬም የሚያስጨንቅ ንግግር አባቶቻችንና አገልጋዮቻችን ይናገራሉ። አንድ እናት ከጸነሰች በኋላ ከቅዱስ ቁርባኑ እንድትርቅ የሚናገሩ አባቶች ካሉ እጅግ በጣም ትልቁ ስሕተት ነው። ለምን እንደዚህ ይላሉ? የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከማኅጸን ጀምሮ እንዳይባርከው? የዲያብሎስን ክፉ መንፈሳዊ አገዛዝና አኗኗር የሚያግዝ ጠባይና ባሕሪይ ላይ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ልምድ አላቸው ማለት ነው። ይሄ ግራ መጋባት የሚስጢረ መለኮት ትምህርት ያጠራቸውና በዘፈቀደ ሕይወታቸውን በመንፈሳዊ ስፍራ ላይ የጀመሩ ሰዎች የፈጠሩት ትልቅ ውድመት ነው። የተባረከ ትውልድ ለማግኘት በቃ የግድ ነው የክርስቶስ ሥጋና ደም ያስፈልጋል።

ከጽንስ ጀምሮ እናት ሆን ብላ የተባረከ ልጅ እንዲሆንላት እየጸለየች ከውስጥ ክርስቶስን እየተቀበለች፤ ከውጭ በጸሎቱ፣ በቅብዓ ቅዱሱ፣ በእምነቱ፣ በቤተ እግዚአብሔር አምልኮቱ እየዳበሰች ስትቀይ፤ እንዲህ ከሆነ ከውስጥም ከውጪም ኃይል ያለው ልጅ ይወለዳል። ይሄ ኃይሉ እግዚአብሔር ይሆናል። ይሄንን ትተን የወለድናቸውን ደግሞ

ይኸው እኮ ትውልዱን በመንፈሳዊ እይታ በኩል ስንፈትሽ ሁሉ ገብ ውደቀቱን ለማገናዘብ አትቸገርም። ኑሮአችንን ይኸው እኮ ማየት ነው።

ሐናን ተመልከቱ። በመጽሐፈ ሳሙኤል ከምዕራፍ አንድ ጀምሮ ያለውን ተመልከቱ። ቤተ መቅደስ ሄዳ እየጸለየች የወለደቺው ልጅ እስከ መጨረሻው ድረስ የእግዚአብሔርን ቅባትና ዘይት ይዞ የሚመላለስ ታላቅ ነቢይና አገልጋይ፣ ሐዋርያና ትልቅ ደቀ መዝሙር ሆኖ ዘመኑን ጨርሶዋል። እርሷ ከውስጥም ከውጪም የባረከቺው ልጅዋ የተባረከ ሆኖ ስለተገኘ ነው። በቅድስናው ስፍራ ላይ የበላችውና በዛ በመስዋዕቱ ቦታና ግዜ ላይ የቆየችበት ፍሬ ሳሙኤልን አስገኘ። ሳሙኤል እግዚአብሔር ሰማኝ ማለት ነው። እግዚአብሔር የሚሰማው ኑሮ፣ ጊዜ፣ ገንዘብ፣ በረከትና ትዳር ከልጅ ፍሬ ጋር እንዲሰጣችሁ ሥጋወ ደሙን ተቀበሉ።

## ክፍል - 5

## ኤፍታህ

## ስንቱ ነገሮች ተዘጉብን ?

ኤ-ፍ-ታ-ህ የሚለው ቃል በምዕራፈ ሰባት የማርቀስ ወንጌለ ቁጥር ሠላሳ አራት ላይ የተገኘ ኃይለ ቃል ነው። ቃሉን ስንመለከተው እንዲህ ሲል እናነበዋለን። " ወደ ሰማይም አሻቅቦ አይቶ ቃተተና። ኤፍታህ አለው፥ እርሱም ተከፈት ማለት ነው።"

አሁን እዚህ ኤፍታህ ምን ማለት ነው አለ? ተከፈት ማለት ነው ይላል። እንደዚህ የሚለው መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

ተከፈት ነው የሚለው የኛ ጌታ። ተዘጋ አይደለም። እንዴት ነው እኛ ምን ምን ነገሮች ተዘግተው አስከፈትን? በክርስትና የሕይወት ጉዞ ሂደት ውስጥ ከሚያስፈልጉን ኃይለ ትዕዛዛት መካከል አንደኛው << ተከፈት! >> የሚለው ቃል ነው። የሚያስፈልገንን የማናውቀው እኛ በኑሮአችን መንገድ ላይ ከተከፈቱ ይልቅ የተዘጉብን ነገሮች ይበዛሉ። ለምሳሌ በረከታችንን እንመልከት። ብዙዎቻችን ጠዋት ማታ ያለማቋረጥ እንሠራለን። የዕለት ጉርስና የተመቻቸ የኑሮ አቋም ለማግኘትም በአቅማችን ልክ በየቀኑ ወጥተን እንገባለን። ግን የበረከት ኑሮ በምንሠራውና በምንለፋው ልክ ስሌለን ብዙ ዘርተን ትንሽ እናጭዳለን። ይሄ ለምን ይሆናል? ምክንያቱም የበረከት መንገድ ተዘግቷል። የበረከት ዕድል ተቋርጧል። የበረከት ጠላት በረከታችንን አቀጭጮታል። በመሆኑም በመናፍስት ተጽዕኖ እና አገዛዝ ሥር የወደቀው የሕይወታችን ገጽታ ካለበት አረንቋ መላቀቅ ያቃተው፣ ለፍቶ መና የሆነ፣ ገንብቶ ማፍረስ የሚስተዋልበት የኑሮ ቅርጽን ለመያዝ ይገደዳል። አገራችን ብዙ የተፈጥሮ ሐብት፣ ምቹ የአየር ንብረትና መልክአ ምድር እንዲሁም በቂ የሰው ኃይል እያላት ስለምን ከአገራት የኢኮኖሚ መደብ ውስጥ የጭራነቱን ስፍራ ለመያዝ ተገደደች? ሰው ጠፍቶ ነው? ሥራ ጠፍቶ ነው? ድሃ እንድንሆን ተረግመን ነው? በመሠረቱ እኮ የእግዚአብሔር ህዝብ እየሰጠ የሚሄድ እንጂ፤ እያጣ እየደኸየ የሚሄድ አይደለም። እኛ ግን እያጣን እየደኸየን መጣን። ውስጣችን መጀመርያ እግዚአብሔርን አጣ። ከዛ በኋላ በዓለም ላይ ባለው ነገር ላይ ምንም ባለቤትነት አጣን። ለምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? "ኤ-ፍ-ታ-ህን" ስለማናውቅ ነው። ይዘጋ እንጂ ይከፈትን አላወቀበትም ማኅበረሰባችን።

ባለፈውም የትውልድ ዘመን ውስጥም ድምፃችን ሲል የተደመጠው ይውደም ነው። ይገንባ አይደለም። ሽማግሌዎቻችንም፣ አሮጊቶቻችንም፣ ሠራተኛውም፣ ተማሪውም፣ ገበሬዎችም ተሰበሰቡና ጮኹ በቃ። ይወድም ተባለ። የአፋችንን ፍሬ ተከተለውና በመኖር የሕልውና ሂደት ውስጥ ከግዜ ወደ ግዜ በሚንከባለል የእርግማን ምሪትና የአመፃ ራእዮች በኩል ቀጣዩ ትውልዳችን በሚያወድሙት መናፍስት ሲቀደም ከግዜ የሚብስ፣ ከኑሮ የሚብስ፣ ከገንዘብ የሚብስ፣ ከእውቀት የሚብስ፣ ከዕድል የሚብስ አኗኗር ላይ እንድንደርስ ወደፊት እየቀደመ ሲሮጥ

እየገሰገሰ ሲቸኩል፤ የመኖራችን አካሄድ በብዙ መንገድና አቅጣጫ በኩል ጥልቅ ፈተና ውስጥ እንዲወድቅ፤ አባቶች በእውነተኛ ሰማያዊ ሞገስና ጸጋ ያቆዩትን ቃልኪዳን፣ በፍጹም መሰዋትነትና ተጋድሎ ያስረከቡትን ስጦታ፣ አክብረውና ጠብቀው ያቆዩት የተሰፋና የራእይ በረከት፣ ክፉን በአንድ ኅብረት ተቃውመውና አውግዘው መልካሙን ያቆዩበት አቅማቸው፣ አንዱ ለአንዱ የድክመቱ ኃይል በሆነበት ላይ ለድጋፍና ለመተባበር የተከፈተው ሰብእናቸውን፣ አንደበታቸውንና ምግባራቸውን ከመንፈሳዊ ጉድለትና ሙላት አንፃር እየመዘኑ የእግዚአብሔር የምሕረትና የረድኤት እጆችን የያዙበትን ዘመናቸውን፤ እኛ ተሰበሰብንና እንዲህ በሚል ቃል ንቀን አፈረስነው። "ይውደም።"

ከዚህ የማርኪሲቱና የፍልስፍናው አምባ የተነሣው አፍራሽነታችን፤ ይህንን አጥፊነቱን በቀጥታ ለቀጣዩ ትውልድ በሚያስተላልፍበት ግዜ፤ ይውደም ያልንበት የቃል እርግማን በእያንዳንዳችን ልብና ቤት ውስጥ ዘልቆ ሲገባ፤ በመጀመሪያው ውድመት አንድ ሲል ውስጣችንን ነው ያወደመው። ውስጣችን በሚወድምበት ግዜ፤ ባሕሪያቶቻችን ከኛ ጋር ተስማምተውና ተግባብተው መቀየት ስለሚያቅታቸው አሁን በቃ የሚከተሉት ሁኔታዎች መከሰት ይጀምራሉ። አንደኛው፤ ከአመላችን፣ ከጠባያቶቻችን፣ ከልብና ሕሊናችን፣ ከእውቀታችን፣ ከገንዘባችን፣ ከእቅዳችንና ከዕድሚያችን አጋጣሚዎች ጋር ሁሉ እንጣላለን። ሁለተኛ፤ የወላጆች የእርግማን ፍሬ፣ የአከባቢና የቀዬ የዘልማድ ርኩሰት፣ በሕይወት መስመር ላይ ከሚኖሩ ግራ ሁኔታዎች፣ ከትምህርት ቤትና ከሥራ ቦታ ውስጥ ካለ የተሰወረ ጥልፍልፍ የሴራ ጥቃት የተነሣ እኛነታችንን በማጣት ማንነታችን በብዙ የተመሳከሩ ፍልስፍናዎችና የተበሳጠሩ መረጃዎች የተገነባ እንዲሆን አመጣጣችንም ስለሚያስገድደው፤ ወደ ውስጣችን ለማየትና የነፍሳችንን ፍቃድ ለማድመጥ የምንችልበት ማስተዋሉ፣ አቅሙ፣ ግዜውና መረጃው ያጥረናል። ሦስተኛ፥ የግዜና የሁኔታ ሰዎች ለመሆን እንገደዳለን። እንደዚህ ስንሆን ጊዜና ሁኔታ በተገለባበጡበት ልክ እኛም እንገለባበጣለን። ሁኔታዎች ሲረበሹ እንረበሻለን፤ ሁኔታዎች ዝም ሲሉ ዝም እንላለን፤ ግዜዎች ሲሰደዱ እንሰደዳለን፤ ግዜዎች ሲደናገሩ እኛም እንደናገራለን፤ ሁኔታዎች ሲፈጥኑ እንሮጣለን፤ ሁኔታዎች ሲቆሙ ግራ እንጋባለን። ይህ እንግዲህ ውስጣዊ አለመግባባት ከሚያመጣቸው የሕይወት አካሄድ ውጪያዊ ጥገኝነት አንዱ ውጤት የሆነ ክፍል ነው። አራተኛ፤ ራእይና ተስፋ ከሕይወታችንና ከእንጀራችን ይሸሻል። የውስጥ ውድመት በሚከሰትበት ኑሮ የእምነት መደበዘዝና በሃይማኖት ላይ የመተኛት ግዴየለሽነት እየጨመረ ሄዶ አልከፈት ባለው ሰማይ ምክንያት መንፈሳዊ ምሪት ከነራእዩ ስለሚጠፋ፤ በቀን ስንጨነቅበት የዋልነው የዕለት ጉዳይ ማታ ደግሞ በሕልም ሊያስጨንቀን በሕሊናችን ውስጥ ተቀርፆ ይዞታም አግኝቶ ይጠብቀናል። ከዛ በኋላ በቃ ተኝተህ መሄድ ትጀምራለህ። ተኝተህ መጮህ ትጀምራለህ። ተኝተህ መባተትና መጨነቅ የሌሊቱ ግዜህ ይሆናል። ትውልዳችን ብሎ ጮኾ የነበረው ይወድም ሲል ነዋ። ይበልጽግ አይደለም ያለው። ይለምልም አይደለም ያለው። ይገንባ አይደለም ያለው። ስለዚህ ይወደም ብለን ለጮኽንለት ዘመን የድምፃችን ፍሬ ችግር ፈጣሪ፣ መከራ ሳቢ፣ ሰቀቃ ጠሪ ሲሆን መፍትሔ የሚመስለንን ነገር ሁሉ ሞከርን። አንዱም ሳይሳካ ይኸው በምንገኘው ትውልድ ውስጥ የየግል ችግሮችን እንደጋራም እያስተናገድን በተናጠል እንደመጣን፤ በተመጣን እንሸኛለን። እግዚአብሔር ምሕረቱን ያብዛልን።

እግዚአብሔር አምላክ ሰው ሆኖ ወደ ምድር ሲመጣ ያሰማን አንደኛው የኑሮ መርህ "ኤፍታህ" የሚለው ድንቅ የቸርነቱን ቃል ነው። በቃ ሌላ ነገር የለም ኤፍታህ ነው የምትለው። በምንድነው ኤፍታህ የምትለው እሺ? እኛ እንደ ጌታችን ኤፍታህ የምንለው እንዴት አድርገን ነው?

የተዘጋውን የምንከፍተው በሥጋና ደሙ መቀደስን ይዘን ነው። "ተከፈት" ብሎ ጠላት የያዘውን የሚያስለቅቅ ሰማያዊ ድምፅ ባለቤት የሆነውን ጌታ ወደ ውስጣችን ስንቀበል እኛም እንደርሱ ተከፈት ስንል የታሰረው፣ የተዘጋው፣ የተቆለፈው ሁሉ ይከፈታል። እየከፈተ የሚሄድ አምላክ ነው የሰማይ አባታችን።

የክርስቶስ ሥጋና ደም በተዘጋብን ነገር ላይ የምንወስደው መክፈቻ ቁልፋችን ነው። ትምህርቱ ሲዘጋ፣ ሥራው ሲዘጋ፣ ዕድሉ ሲዘጋ፣ ሰላምና ጤናው ሲታሰር፣ በረከትና ረድኤቱ ሲቆለፍ ያን ጊዜ የጌታችንን ሥጋና ደምን

ስለተዘጋው ነገር በርዕስ እንወስድበታለን። "እኛን መርጠህ ወደኛ የመጣህ የሰማይ አባታችን ሆይ፥ ሥራው ተዘጋብኝ። የትምህርት ዕድሌ ተዘጋብኝ። ሕይወቴ ውስጥ ያለው ጠላት መንገዶቼን ዘግቶብኛል። አቤቱ የተዘጋው በር ሁሉ መክፈቻ ያለህ ቅዱስ አምላክ ሆይ፤ የተዘጋብኝን ክፈተው፣ ዕድሌ ላይ የተኛውን ጠላት አስወግድልኝ፣ እንጀራዬን ከበረከት ያራቀውን ጠላት ከመንገዴ ላይ አንሣው፤ ትዳሬ አደጋ ላይ ሆነ አድነው ጌታ ሆይ፤ ሰዎች ሸሹኝ ብቸኝነት ወረሰኝ ከኔ ጋር ሁን አባት ሆይ፤ ጸጋና ሞገስ የጠፋበት ኑሮዬን አስተካክልለው አምላክ ሆይ፤ ብርሃንህን አብራልኝ ንጉሥ ሆይ" ብለን ቅዱስ ቁርባንን ስንቀበል የተቀለፈብን ሁሉ ወለል ብሎ ይከፈታል። ደሞ ሲከፈት ተጨማሪ የዕድልና የበረከት መንገዶችን ይዞ ነው የሚከፈተው። በቃ ይሄ ግሩም ቸርነቱ እኮ ነው። የሚዘጋ የሚከፍት አምላክ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ። " እርሱም ይከፍታል የሚዘጋም የለም እርሱም ይዘጋል የሚከፍትም የለም።" (ትንቢተ ኢሳይያስ 22፥22)

በዘመናችን እኛ የተዘጋውን ለመክፈት አሊያም የተከፈተውን ለመዝጋት የራሳችንን ሥጋዊ ጥበቦችና አካሄዶች ብቻ ተጠቅመን ልናስተካክል ብንወጣ ብንወርድም፤ የተዘጋው ይበልጥ እየተቀለፈብን፤ የተከፈተው ይበልጥ እየሰፋብን፤ ችግር ላይ ችግር እየደረብን የተነሣንበትን መነሻ ችግር የረሳን ብዙዎች ነን። የተዘጉት ነገሮችን መክፈቻው ቁልፍ ሥጋና ደሙ ነውና፤ ከመቀ'ደስ ሕይወት በራቅንበት ርቀት ልክ፤ የመፍትሔ ቁልፉም እየራቀን እየሸሸን ስለመጣ፤ አሁን የተገኘንባቸው መንገዶች በብዛት የተዘጉ ናቸው። ስለዚህ መዘጋት፣ መቀለፍ፣ ማጣት፣ መታሰር እጣ ፋንታዎቻችን ሆነው ይታያሉ። ኢየሱስ ክርስቶስ በድንግል ማርያም በኩል ወደኛ ሲመጣ እነዚህን ነገሮች ከሕይወታችን ሊያወስግድልንና ሰማያዊ ሕይወት ሊያካፍለን ነበረ የመጣው። ድምፆቹም "ተከፈት፣ ፈትታችሁ አምጡልኝ፣ ተነሳና አልጋህን ተሸክመህ ተመላለስ፣ በሰላም ሂጂ፣ ወደ እኔ ጥሩት፣ ሽክማችሁን አምጡ" የሚሉ ናቸው። እጆቹም 'የሚባርኩ፣ የሚቀድሱ፣ የሚያነሡ፣ የሚደግፉ፣ የጠፉ ዓይኖችን የሚያበሩ፣ የተዘጉ ጆሮዎችን የሚከፍቱ፣ የሚያበሉና የሚያጠጡ' ናቸው። እግሮቹም 'ወደ ታሰሩት የሚሄዱ፣ ከድሃው ጋር አብረው የሚዞሩ፣ ወደ ብርሃን ምሪት የሚወስዱ፣ ለጸሎት የሚቆሙ' ናቸው። ይሄ ጌታችን ማነው? ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እናቱም እናታችን ድንግል ማርያም፤ መልአኩም ቅዱስ ሚካኤል ነው። የብሥራት ባለቤቱም ቅዱስ ገብርኤል የኛ ነው። እኛ ግን ምንም ልናውቅበት አልቻልንም። በቃ እንዲሁ ዝም ብለን በየልብስ መሸጫው ላይ የሚንጠለጠሉትን ሰው መሳይ አሻንጉሊቶች ሆነን፤ እየኖርን እየመሰለን ሳንኖር እንሞታለን።

እንደው እስኪ እባካችሁ አትሸወዱ! ሥጋና ደሙን መቀበል ስትጀምሩ ነው ሰላምና በረከት የሚመጣው። የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ሃያ አንድን ተመልከቱት። ሂዱ ወደ ፊታችሁ መንደርና የታሰረቺውን ውርንጫ ፈትታችሁ አምጡልኝ የሚል ቃል ታገኛላችሁ። "ፍቱና አምጡልኝ" የሚለው ጌታ ወደ ኑሮህ ካልመጣ፤ እሰሩና አስቀምጡት የሚሉ የዲያቢሎስ ድምፆችን ሕይወትህ ለመስማት ይገደዳል። ይኸው እኮ ታስረን ታስረን። እውቀት ያሰረው አለ። ሥራ ያሰረው አለ። ሥልጣን ያሰረው አለ። ችግር ያሰረው አለ። እፎይታ ያጣ ትዳር ያሰረው አለ። ዝሙት ያሰረው አለ። ሱስ ያሰረው አለ። ፊልምና ሙዚቃ ያሰረው አለ። በሽታ ያሰረው አለ። ጭንቀት ያሰረው አለ። ሰው ያሰረው አለ። ዛሬ ይኸው ይሄ የመታሰር ገጽታ ብሶ ብሶ ሲገኝ፤ በየቤታችን እንድንታሰር የሚያስገድድ ዘመንና ግዜ ወደ ሕይወታችን መጣ። ግዜ ደሞ አሰረን ማለት ነው። አየኸው እግዚአብሔር የሌለበት ዓመታትና ዘመን? እንደዚሁ ይሆናሉ።

"አማኑኤል" ማለት እግዚአብሔር ከኛ ጋር ሆነ ማለት ነው ብለናል ክርስቲያኖች። ታዲያ የታለ አማኑኤል እኛ ጋራ የሆነው? የአንድነቱ ማሰሪያ አሪቡት ቅዱስ ሥጋና ደሙ የታለ በሕይወታችን ውስጥ? የዮሐንስ ወንጌል 6፥56'ን የሚለው " ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ።" ነው የሚለው። አማኑኤልነትን የፈረመ የሰጦታው ቃል ነው። በእኔ ምን ይላል? በእኔ ይኖራል አለ። እኔም በእርሱ ምን እላለሁ? እኔ በእርሱ እኖራለሁ አለ። ታዲያ ይሄ አንድነቱ እኛ ውስጥ የታለ? እርሱ በእኛ፥ እኛ በእርሱ በማለት አማኑኤልነቱን የሰጠበት ሰማያዊ እውነታችን የታለን? የእግዚአብሔር ቤት ቤተመቅደስ እንሆን ዘንድ በውስጣችን እንዲኖር ወደራሱ የሳበን በቅዱስ ቁርባኑ በኩል ነው። ጌታችን ወደ ምድር መጥቶ ሲሄድ፥ ሰጥቶን ከሄደው ታላቁ

ሰጦታው አንደኛውና ኃያሉ፤ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙ ነው። ሁሌ ከኛ ይሆን ዘንድ ይህንን ትቶልን ሄደ። በእኛ ይኖር ዘንድ ትቶልን ሄደ። በእርሱ ውስጥ እንኖር ዘንድ ትቶልን ሄደ። የክርስቶስ የአማኑኤል ስሙ አንድነት የሚጸናው በሥጋና ደሙ እንደሆነ የሚያስተውል ሰው ጠፋ በቃ። በመሆኑም በአንደበታችን አማኑኤል አማኑኤል እንላለን፣ እንዘምራለን ግን አንድነቱን በኑሮ ፋይዳና ትርጉም ውስጥ ባለ እጣ ስንፈትሸው የለም።

" ጌታም። ይህ ሕዝብ በአፉ ወደ እኔ ይቀርባልና፥ በከንፈሩቹም ያከብረኛልና፥ ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነውና፥ በሰዎች ሥርዓትና ትምህርት ብቻ ይፈራኛልና " (ትንቢተ ኢሳይያስ 29፥13)

ጥያቄ መጠየቅ አለባችሁ። ስንቱ መንገድና ዕድል ተዘግቶብን እስከመቼ? እስከመቼ ነው እስቲ? ኤፍታህ የምንለው መቼ ነው? ተከፈትን ማለት የምንለምደው መቼ ነው?

ወደ ሥጋና ደሙ ተመለሱ። በየትኛውም ዕድሜ ክልል ሁኑ ዛሬ ነገ ሳትሉ ንስሐ ግቡና ቅዱስ ቁርባን መውሰድ ጀምሩ። መቀ'ደስ ጀምሩ። ከዛ በኋላ ኤፍታህ የሚለው የክርስቶስ ቃል በኑሮአችሁ ውስጥ በተዘጋው ነገር ላይ ሲናገር ትሰሙታላችሁ።

(የማርቆስ ወንጌል ምዕ. 7)

34፤ ወደ ሰማይም አሻቅቦ አይቶ ቃተተና። ኤፍታህ አለው፥ እርሱም ተከፈት ማለት ነው።

35፤ ወዲያውም ጆሮቹ ተከፈቱ የመላሱም እስራት ተፈታ አጥርቶም ተናገረ።

## ክፍል - 6

### ሰማያዊ ዜግነት

### ቅዱስ ቁርባንን ከወሰድን በኋላ ፍጹም መሆን አለብን?

ሰማያዊ ዜግነት ምን ማለት ነው? እንዴትስ ሰማያዊ ዜጋ መሆን እንችላለን? እስኪ የሚከተለውን ቃል እንመልከት። 1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች ምዕ. 15'ን ስትነቡ የምታገኙት ቃል እንዲህ ይላል።

48፤ መሬታዊው እንደ ሆነ መሬታውያን የሆኑት ደግሞ እንዲሁ ናቸው፥ ሰማያዊው እንደ ሆነ ሰማያውያን የሆኑት ደግሞ እንዲሁ ናቸው።

49፤ የዚያንም የመሬታዊውን መልክ እንደ ለበስን የሰማያዊውን መልክ ደግሞ እንለብሳለን።

50፤ ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ይህን እላለሁ። ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርሱ አይችሉም፥ የሚበሰብሰውም የማይበሰብሰውን አይወርስም።

የመሬታዊውን መልክ እንደለበስን የሰማያዊውን መልክ ደግሞ ምን እንላለን? እንለብሳለን። ሰማያዊ መልክ እንለብሳለን ነው የሚለው። ክርስቲያን ተብለን በ40 እና በ80 ቀን ተጠምቀን፤ በመንፈስ ቅዱስ እሳት የሥላሴ ልጅነትን አግኝተን፤ ወልደ ኢየሱስ፣ ወልደ ማርያም፣ ገብረ ማርያም፣ ክንፈ ገብርኤል፣ ወለተ ሥላሴ፣ ሰይፈ ሚካኤል ተብለን ተጠርተን እኛ ግን ሰማያዊ መልክ የለንም። ያለን የሚዳሰስ፣ የሚጨበጥ፣ የሚታይ መሬታዊ መልክ ብቻ ነው። ዘወትር የምንታጠበው፣ የምናለብሰው፣ የምናበላው የምናጠጣው ምድራዊ ሥጋን ብቻ ነው የያዝነው። ሰማያዊ መልክ የታለን? እኔ ሰማያዊ መልክ አለኝ የሚል ማነው እስቲ በዚህ ዘመን? ሁላችን ሰማያዊ

የሰውነት ክፍል እንዲኖረን ተጠምቀን እና ማኅተብ አሰረን ብንባረክም፤ ከአፈር ብቻ እንደተፈጠርንና ነፍስ እንደሌላቸው እንስሳት ከውስጣችን ያለውን ሰማያዊ ኃይልና እውነት በውጪያዊ የሥጋ ፍላጎቶችና የአኗኗር ሂደቶች አፍነን በቅዱስ መንፈስ በኩል ለመ"ጎብኘት የሚቻልበትን የየዕለት መንፈሳዊ አጋጣሚዎችንና ዕድሎችን ስንዘጋበት፤ በቃ ያው እንስሳቱን ሆንን። በሥጋዊ ገጽታዎችና የአካሄድ መንገዶች ብቻ የተገነባው ኑሮአችን ከመብላት፣ ከመጠጣት፣ ከመተኛት፣ ከመልበስ፣ ከመዋብ፣ ከመማር፣ ከመሥራት፣ ከመዝናናት እና ትዳር ከመመሥረት ያለፈ መንፈሳዊ ሕይወት ላይ ጊዜና ቦታ ለመስጠት አቅሙ አጠረን። አቅሙ ሲያጥረን በዛው ፍቅርም አጠረን። ሰላም አጠረን። በረከት አጠረን። ምንድነው እስኪ እንዴት ነው ነገሩ? ብለን በመንፈሳዊ አቅጣጫ በኩል የታመመ ኑሮአችንን ለማከም ምንም አይነት ፍላጎትና መረጋጋት ከባሕሪያችን አልገኝ ስላለ፤ ጠዋት ወጥተን ቀኑን ሙሉ ስንዳክርና ስንለፋ ውለን ማታ መውደቂያችን ላይ ጫማችንን እንኳ ለማውለቅ እስኪሣነን ደክመን ገብተን እንተኛለን። ነገና ከነገ ወዲያም እንዲሁ በተመሳሳይ የኑሮ አዙሪት ላይ ውደቀን፤ ዓመታትን ለትምህርትና ለሥራ ብቻ የምቾት ግብ ላይ ለመድረስ ስንታትር ስንታትር ብንቀይ፤ ኑሮው በራሱ የተሰወሩ ጠላቶችንና ክፋቶችን የያዘ የምቀኝነት፣ የአመፃ፣ የግፍ፣ የአረማዊነት፣ የትዕቢት፣ የተንኮል፣ የሴራ ቀናትን ተሸክሞ አምጥቶ እየጣለብን፤ ትግላችን ረጅም ጊዜ የሚወስድና መጨረሻውም አልታይ የሚል አሰልቺ ሕይወትን ለመምራት እንድንገደድ ጊዜዎችና ሁኔታዎች አንድ ላይ ከቁጥጥር ወጥተው እየተባበሩ አስጨነቁን። መሬታዊ መልክ ብቻ ያለው ሕይወትና ዘመን ስትይዝ እንደዚሁ ነው። ሰማያዊ መልክ የለህም። መንፈሳዊ ማንነት የለህም። መለኮታዊ ጥበቃና በረከት የለህም። ስለዚህ እሾህና አሜኬላ ታበቅልብሃለች ተብላ የተረገመቺው የመሬት መልክ ብቻ ሲኖርክ በእውነት ኑሮህና ጊዜህም ላይ እሾህና አሜኬላ ቢበቅል ምንም የሚያስገርም አይሆንም።

ቃሉ የሚለንን በድጋሚ እስቲ በማስተዋል እናስበው። "የዚያንም የመሬታዊውን መልክ እንደ ለበስን የሰማያዊውን መልክ ደግሞ እንለብሳለን።" ለምንድነው እኛ ሰማያዊ መልክ መልበስ ያቃተን? ሰማያዊ ዜግነት ለምን ከሕይወታችን ተለየ?

ዜግነታችን በተወለድንበት አገርና መሬት ሥር ብቻ ሲያሜና መገለጫ አግኝቶ የምንገኝ ከሆነ፤ እንደ መሬት ፍጡራን ብቻ ለመኖርም እንገደዳለን። መሬታዊ ዜግነታችንን በሕግና በመወለድ በኩል አጽድቀን፤ ሰማያዊ ዜግነታችንን በፍቅርና በመ'ቀደስ ለሐዲስ ኪዳን ዜጎች ሲሰጠን ልንቀበል በጣም ያስፈልገን ነበረ። እኛ ግን መቀበል የምንፈልገው ሹመት ነው። ማዕረግ ነው። ዝናና ሥልጣን ነው። ከፍተኛ ደመወዝና ቁሳቁስ ነው። እርሱንም በሰማያዊ ዜግነታችን በኩል መቀበልና በበረከቱ ጎዳና በኩል መሰለፍ ስንችል፤ የማናስቀድመውን ስለማናውቅ በረከት ሸሸቶን፣ ረድኤት እየራቀን፣ የእጆቻችንም ፍሬዎች እየደረቁብን ሕይወት ውስጥ በተሰወሩ ጠላቶች ሕልውናችን አደጋ ላይ ወድቆ፤ በቀኝም በግራም በኩል ፈተና ውስጥ ገብተን፤ የውስጥም የውጪም ችግሮቻችን ለዘመናት እንዲቀይ ምክንያቱ ራሳችን ሆነን አበሳችንን እናያለን።

ሰማያዊ ዜግነት ከኑሮ፣ ከቤተሰብ እና ከቤት በሚለይበት ጊዜ፤ በዓለም ፖሊሲና ሕግጋት የሚመራ ሕይወትን ለመያዝ ስለምንገደድ ሁሉንም ነገር ከሥጋዊ ሚዛንና እውቀት በኩል ብቻ እየፈተሸን በአንድ ጎን የተንሻፈፈ ጊዜንና ዘመንን ስለምንመራ ወደፊትም ወደኋላም ያለውን የኑሮአችንን አካሄድና አመጣጥ ቦታና ትንፋሽ ሰጥተን ለማገናዘብ እንቸገራለን። ሁሉም እንደሚኖረው እየኖርን ስለሚመስለን፤ መከራና አልፈታ ያሉ ቤተሰባዊና ውስጣዊ ችግሮቻችን የጋራ እውነታዎች ብቻ እንደሆኑ አድርገን እንቀበላለን። በዚህ አይነት አስተሳሰቦች እና የርዮተ ዓለም ፍልስፍናዎች የተሞላው ዘመናችን፤ አንዱ የአንዱን ችግር የማይሰማው እየሆነ፤ የአንዱን ስቃይና ብልሽት ለመካፈል የሚችልበትን መስመሮች የሚሸሸ እየሆነ፤ ቤተሰብ ቤተሰቡንም መርዳት የሚያቅተው እየሆነ፤ የግል የግል ስሜቶችን ለውሰጥ ባሕሪያትና ጊዜያቶች ብቻ አሸክመናቸው፤ መሄጃውና መምጫው የተሰወረብን የነፍስና የሥጋ ዳተኞች ጥቂት አይደለንም።

የዚያንም የመሬታዊውን መልክ እንደ ለበስን የሰማያዊው መልክ ደግሞ እንለብሳለን ይላል የእግዚአብሔር መልእክት በመጽሐፍ ቅዱስ። ሰማያዊውን መልክ ደግሞ እንለብሳለን። ወደ ሮሜ ሰዎች 13፥14 ላይ " ነገር ግን ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት፤ ምኞቱንም እንዲፈጽም ለሥጋ አታስቡ። " ይላል። ሰማያዊ መልክ የምንለብሰው መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ስንለብሰው ነው። እኛ አሁን ምንድነው እስኪ የምንለብሰው? ፋሽን ብቻ ነው። ክርስቶስን መልበስ ሲያቅተን፤ በፋንታው የጨለማው ገዢ እኛን ለብሶን የጥፋት ስልቶችንና አካሄዶችን አስልቶ በስውር ተቀራኝቶን በግልጽ ሲወጋን ምን እንደሚያጠቃን እንኳን ለመገንዘብ መረጃውን አጥተን የብርሃን ዘመን ውስጥ ጽልመት ውጦን እንገኛለን።

<< ክርስቶስን ልበሱት >> ይላል ቃሉ። እንዴት ነው ክርስቶስን መልበስ የምንችለው? የሰማዩን አምላክ እንዴት ነው ልንለብሰው የምንችለው? ቅዱስ ሥጋው ከሥጋችን ክቡር ደሙን ከደማችን ስናዋሕድ ነው የሰማዩን አባት ለብሰን ሰማያዊ መልክን እናገኝ ዘንድ የሚቻለን። አሁን ዮሐንስ ወንጌልን ስታዩ ጌታችን በቅፍርናሆም ምኩራብ ሲያስተምር እንዲህ አላቸው ለአይሁዳውያንና ለደቀመዛሙርቱ።

(የዮሐንስ ወንጌል ምዕ. 6)

56፤ ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ።

ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣው ምን ይሆናል? በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ አላቸው። አይሁድ በዚህ ጊዜ ግራ ተጋቡ። እንዴት ነው ሥጋውን እንበላ ዘንድ የሚሰጠን እያሉ ተከራከሩ። ሥጋና ደሙን በባረከው ስንዴና በቀደሰው ወይን በኩል ለሁላችን ሰጠን።

(የማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 26)

26፤ ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና። እንካችሁ፥ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ።

27፤ ጽዋንም አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው እንዲህም አለ። ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፤

28፤ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።

ሥጋውን በባረከው እንጀራ ደሙን በቀደሰው ወይን በኩል ሰጣቸውና እንዲህ አለ። "ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።"

ዛሬ በደም መሠረቱ ታንፃ በስሙ የቀመቺው ቤተክርስቲያንም ሕብስተ ሥጋውን እና ሕብስተ ደሙን ቀድሳ ሥጋ መለኮትና ሥጋ ደም አድርጋ ፊትታ "ኑ የኃጢአት ማስተሠሪያ ሥጋውን ብሉ ደሙን ጠጡ" እያለች ዘወትር ብትጠራም ወደዚያ የሚሄዱ እግሮች የሉም። ለምንድነው የሚሆነው ይኼ? ለምንድነው ወደ ክቡር ሥጋውና ወደ ቅዱስ ደሙ የማንጠጋው? ኸረ ሰማያዊ ቃሉ እንዲህ ነው የሚለው ይኸውላችሁ።

" ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም።" (የዮሐንስ ወንጌል 6፥53)

## ቅዱስ ቁርባንን ከወሰድን በኋላ ፍጹም መሆን አለብን?

ብዙ ክርስቲያኖች በዚህ ዘመን ከቅዱስ ሥጋና ደሙ የሚርቁበት አንደኛው ምክንያት "ከቆረብን በኋላ እንደ መነኮሳት፣ እንደ ጻድቃን፣ እንደ ቅዱሳን" መኖር አለብን ብለው የሚያስቡት የተዛባ አስተምህሮ ያለበት ትምህርት

በመኖሩ ነው። ማነው እንደዚህ ያለው? ማነው ከተቀረበ በኋላ ሁሉም የሕይወት መስመር ካልተቀደሰ አይቻልም ያለው? እንዲህ ያለው ትምህርት ዲያቢሎስን የሚያግዝ ቋንቋና ጠባይ የያዘ በመሆኑ ርኩሳን መናፍስት በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ የሚኖራቸውን ሥውር የአገዛዝ ዕድሜ የሚያራዝም ሲሆን ክፋትን የሚደብቅ ለመቀደስና ለበረከት ዘመን መዘግየት የድርሻውን የሚወጣ መናፍስታዊ እሳቤ ያለበት የክርስትና ጉዞ ላይ አረንቋ የሚሆን መሰናክል ነው።

እስኪ የቅዱስ ጴጥሮስን ታሪክ ተመልከቱ። አንተ ዓለት ነህ ብሎት ነበረ በዚህ በማቴዎስ 16 ላይ። ከጌታም ጋር ሲወርድ ሲወጣ የከረመው ጴጥሮስ በመጨረሻውም ወቅት ላይ ከጌታ እጅ ላይ ቀረበ። ሊቀ ካህኑ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ባርኮ የሰጠውን ሥጋውን ቀድሶ ያቀረበለት ደሙን ከጓደኞቹ ሐዋሪያት ጋር ሆኖ እንደበላ እንደጠጣ በማቴዎስ 26፥26 ላይ ታገኙታላችሁ። ሥጋና ደሙን የተቀበለው ጴጥሮስ በክርስቶስ ተባርኮ ውስጣዊ ሕይወቱም ተቀድሶ ጌታውን ከኋላ ኋላ እየተከተለ ሲመጣ አይሁዶች "አንተም ከእርሱ ጋር ነህ!" ሲሉት ከአንድም ሦስት ጊዜ "የምትሉትን ሰው አላውቀውም!" አለና ሸመጠጠ። የሚገርም ነው አያችሁ። በእጁ ሥጋውን በልቶ? በእጁ ደሙን ጠጥቶ አላውቀውም? እንዴት ነው ነገሩ? ጴጥሮስ ቀርቦ ካደ።

የሰው ልጅ ከቀረበ በኋላ ፍጹም ሕይወትን ሊመራ እንደማይችልና ወደነበረበት ኃጢአት ሊመለስ እንደሚችል ያው እዚህ ጴጥሮስና ሐዋሪያቱ አስተማሩ። አስቀድመው ሲያቀፉት፣ ሲከተሉት፣ ድንቅ ሥራውን ሲያዩ፣ ቃሉን በአንክሮ ሲሰሙ የቆዩት ሥጋና ደሙን ከተቀበሉ በኋላ ከባዱ ጊዜ ሲመጣ ሸሹ። ወደነበሩበት ዓለም ሊመለሱ ወደኋላ ሸሹ።

ዛሬ የንስሐ አባቶች፣ ካህናትና የእግዚአብሔር አገልጋይ ነን የሚሉ ሰዎች ወጣቱን ከሥጋና ደሙ ያርቁታል። "ተው ታጠፋለህ፣ ታርከሰዋለህ፣ ትቀሰፋለህ" እያሉ ትውልዱን ከሥጋና ደሙ አራቁት። እስኪ ልቁረብ ሲል ማነው "ቆይ፤ ገና ነህ፤ ትሰናከላለህ" የሚል መልስ ከሰዎች የማይሰጠው? ጫት ሲበላ ተው የሚል የለም። መጠጥ ሲጠጣ ተው የሚል የለም። ሥጋና ደሙን ልውሰድ ሲል ግን ብዙዎች ያንጎራጉራሉ። ለምን? ለምን ከሥጋና ደሙን ርቀን ሌሎችንም እናርቃለን?

ጴጥሮስ ቀርቦ ሦስቴ ቢክድም የዶሮዋ ጩኸት አነቃው። ወደ ጌታም ቢመለከት ጊዜ፤ ዓይኖቹ ውስጥ በቀል የለም። ቁጣ የለም። ብስጭት የለም። ይልቁኑ በፍቅር መልሶ ያየዋል። ያኔ ጴጥሮስ ውስጡ ቢናወጥበት ግዜ፤ ትሕትናው ከአቅሙ በላይ ሲሆንበት ጊዜ፤ የዋህነቱ መሸከም ከሚችለው በላይ ሲሆንበት ጊዜ፤ ራሱን አሳለፈና ሰጠው። ተሸሽጎ አለቀሰና "አባት ሆይ ይቅርታ አድርግልኝ!" ሲል ምሕረትን ለመነ። ንስሐ ገባ ማለት ነው በቃ። ከዚያ ጴጥሮስ ምን ሆነ? የዮሐንስ ወንጌል ምዕ.21 ላይ የሚከተለውን ቃል ታገኛላችሁ።

15፤ ምሳ ከበሉ በኋላም ኢየሱስ ስምዖን ጴጥሮስን። የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን? አለው። አዎን ጌታ ሆይ፥ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው። ግልገሎቼን አሰማራ አለው።

16፤ ደግሞ ሁለተኛ። የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ትወደኛለህን? አለው። አዎን ጌታ ሆይ፥ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው።

17፤ ጠቦቶቼን ጠብቅ አለው። ሦስተኛ ጊዜ። የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ትወደኛለህን? አለው። ሦስተኛ። ትወደኛለህን? ስላለው ጴጥሮስ አዘነና። ጌታ ሆይ፥ አንተ ሁሉን ታውቃለህ፤ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው። ኢየሱስም። በጎቼን አሰማራ።

ከአንድም በሁለትም በሦስተኛውም አስቀድሞ ደጋግሞ ከድቶ የነበረውን ቅዱስ ጴጥሮስ፤ ቂም የማያውቀው ጌታ "ትወደኛለህን?" አለው። ከዚህ በፊት በአስቸጋሪው ወቅት አላውቀውም ሲል የነበረው አገልጋይ፤ እዚህ ከንስሐ

በኋላ ቋንቋው ተቀየረና "እንድወድህ አንተ ታውቃለህ" ይለው ጀመረ። ፍቅሩንም ሕይወቱንም አሳልፎ ሰጠው። በቃ "አንተ ታውቃለህ አባት ሆይ" አለው። ሁለተኛም ጊዜ ትወደኛለህን? ሲለው እንድወድህ ታውቃለህ እያለ ፍቅሩን እያረጋገጠ መመለስ ጀመረ። ሦስተኛው ላይ "ትወደኛለህን?" ቢለው፤ የተጠራጠረው መሰለውና አዝኖ "ጌታ አንተ ሁሉን ታውቃለህ፤ ፍቅሬንም ታውቀዋለህ" አለው። ሁሉን የሚያውቅ ብሎ አዶናይነቱን እዚህ መሰከረ። በቀያፋ ግቢ ሦስት ጊዜ "አላውቀውም!" ሲል የቀየው ሐዋሪያ አሁን ሦስት ጊዜ "እንድወድህ ታውቃለህ" ማለት ጀመረ።

ቀርበንም ብንከዳው በይቅርታ እጁ የሚሰብ አምላክ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ። ቀርቦ የካደው ጴጥሮስ ዳግም በንስሐ ተመልሶ "እንድወድህ ታውቃለህ" ላለው ጌታ እውን እስከ ነፍሱ መጨረሻ ታምኖ ስለ ስሙ ተንገላቶ፤ ስለ ስሙ መከራን ተቀብሎ፤ ስለ ስሙ ወጥቶ ወርዶ፤ አእላፎችን በስሙ አጥምቆ፤ በአንድ ቀን ሰብከት ሦስት ሺህ ሰዎችን መልሶ፤ አእላፍ ደቀመዛሙርትን አፍርቶ፤ ስለ ስሙ ተገድሎ እውነትም የቤተክርስቲያን የዓለት መሠረት ሆኖ ርዕሰ ሐዋሪያት ቅዱስ ሆኖ አለፈ።

ስለዚህ የክርስቶስ ሥጋና ደም ኃጢአትን የሚያስተሠርይ ነው እንጂ ፍጹም የሚያደርግ አይደለም። አስተውሉ!

## ክፍል - 7

## ዘላለማዊነት

## ተፈጥሮ ይግዛን ወይስ እኛ እንግዛው?

በዚህ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 6 ላይ ከመጀመሪያው ጀምሮ ያለውን ስንመለከት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እየተመላለሰ፤ በመለኮቱ እየባረከ መድሃኒት የሆነ ድምፁን እያሰማ፣ መድሃኒት በሆነ መዳፉ እየዳበሰ፣ መድሃኒት በሆኑ ዓይኖቹ እየተመለከተ በሽተኞችን ሁሉ እየፈወሰ ሲሄድ ብዙዎች እንደተከተሉት መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። አሁን ክርስቶስ እርሱ የሚያደርገውን እንደ ተአምር እያደነቁ ብቻ የሚከተሉት ሕዝቦች መማር ያለባቸው ጊዜ ሲደርስና ለምን ወገንነትን ተካፍሎ ሥጋችንን ወስዶ መለኮቱን ሰጥቶ ዘመዳችን እንደሆነ አስረግጦ የሚነግርበት ወቅትና ሰዓት ሲመጣ ወደ ምኩራብ ገብቶ በምዕራፍ 6፥54 ላይ እንዲህ ተናገረ። " ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።"

ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው አለ የዘላለም ጌታ። የዘላለም ጊዜ፣ የዘላለም ሰላም፣ የዘላለም እውነት አለ አየህ።

እኛ ለዘላለም ተፈጥረን ለቅጽበቶች እየኖርን በደረስንባቸው የኑሮ ሁኔታዎችና ቀይታዎች ላይ የሚያጋጥሙን ነገሮች ሁሉ የቅጽበቶች ሆኑ። ከደስታም ቅጽበት፣ ከእፎይታም ቅጽበት፣ ከእረፍቱም ቅጽበት፣ ከተስፋውም ቅጽበት፤ ከጸጋና በረከቱም ቅጽበት፣ ከሞገስና ማስተዋሉም ቅጽበት፣ ከጥበቡና ችሎታውም ቅጽበት። ለምን እንደዚህ አይነት ኑሮ እንመራለን ወገኖቼ? ለምን ከቅጽበት የአጭር የቆይታ ጊዜ ክልል ተሻግሮ ሊቆይ የሚችለውን ማግኘት አልቻልንም? ለምን ሁሉም ነገር ለተወሰኑ ጊዜያትና ሁኔታዎች ብቻ እየተገኙ ሊጸና የሚችለው እየጠፋብን ተቸገርን? በአንፃሩ ልክ የሚጠፉብን፣ የሚበተኑብን፣ የምንቸገርባቸው፣ የምንማቅቅባቸው፣ ለብቻችን የምንሰቃይባቸው፣ የምንባትትባቸው ነገሮችና የሕይወት ኩነቶች ለምን ዘለዓለም እንደሚቀዩ ያህል ጸኑብን?

ብዙዎቻችን ዘላለማዊነት የለንም። የዘላለም ሰው የምንሆንበትን መንገድ አናውቀውም። ስለዚህ ዝም ብለን እንዲሁ በቃ ጊዜው እንዳደረገን ሆነን እየኖርን፤ የጊዜ ሰው ሆነን ስንገለባበጥ ስንገለባበጥ እየኖርን ያለን በጣም ብዙዎች ነን። እስቲ ቃሉን መለስ ብለን እንመልከተው። ምን እንደሚል እናስታውስ እስኪ። "ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው"

የዘመናችን ዓለም በቲዎሪ አስተንትኖቷና በእውቀቷ ሚዛን በኩል ሰፍራ፤ የሕይወትን መርህ ደንግጋ፤ ስታበቃ "ሥጋዬ የተቀበለ ደሜን የተቀበለ ዘላለማዊ ነው" ያለውን ጌታ ሰማያዊ ድምፅ በቅጽበቶች የርዮተ ዓለምና የፍልስፍና ቃላቶች ለውጣ፤ ዜጎቿን በዲያቢሎሳዊ መሠረት በኩል ለረጅም ዘመናት ስለሰበከች፤ የኛ ትውልድ በተለይ ዘላለማዊነት የሚባለውን የሕያውነት አካል ሊኖረው ቀርቶ ትርጉሙ ምን እንደሆነ አይገባውም።

ታዲያ ዘላለማዊነትን ከትምህርት ሰነዶቿና ፍኖተ ካርታዎቿ፣ ከሥራ መዋቅሯና የመሥሪያ ደንቦቿ፣ ከዜጎች የዘወትር የሕይወት አቅጣጫና ጎዳና፣ ከቴክኖሎጂና ሳይንሳዊ ግኝቶቿ አርቃ ያወጣቺው ዓለም ዘላለማዊነት ሲለያት ምን ሆነች? የሚለውን ስንመለከት የዘለዓለም ሕይወት ከውስጥና ከዘመን ሕልውና ሲወጣ፤ የሚጠብቀን ነገር ቢኖር እንዲሁ ትርኪ ሚርኪ የሆነ በብልጭታ ሁነቶችና በአጋጣሚዎች አካሄድ የተመሠረተ የመንደር ኑሮ ነው። በወረትና ቅጽበቶች የላመ የሚለዋወጥ ኑሮ የዛሬዋ ዓለም አገራት ሁሉ የሚጋሩት የአንድነት ገጽታቸው ነው። ዛሬ ዛሬ የምንመራው የብልጭታ ኑሮ፣ የጊዜ ኑሮ፣ የሰዓት ኑሮ ሆነ በቃ። ዘላለማዊነት ከባሕሪያቶችህና ከሕይወት መንገድህ መካከል አልገኝ ሲል፤ የግዜ ሰው ለመሆን ትገደዳለህ። ግዜዎች ሲወድቁ አብረህ ትወድቃለህ፤ ግዜዎች ሲጠፉ አብረህ ትጠፋለህ፤ ግዜዎች ሲያርፉ አብረህ ታርፋለህ፤ ግዜዎች ሲሰደዱ አብረህ ትሰደዳለህ።

የሰው ልጆች ስንፈጠር ጊዜዎችና ሁኔታዎች ወደ ሕይወታችን የሚያመጧቸውን ወደ ራሳችን የመኖር ውኅደትና የመስመር ስምምነት ከማምጣታችን በፊት ምን መጣ? የሚለውን ለማጥለል እንድንችል፤ ከመጣው ጉዳይ አሊያ አጋጣሚ መካከል ክፋትን ለይተን፤ መልካሙን አስቀርተን፤ አንጥረን እንጠቀም ዘንድ አእምሮ ከግራ ቀኝ የማጤኛ ልቦና ታድለን ሳለ፤ ሰዎች ዛሬ ከተሰጣቸው በታች የሚኖሩ ሲሆን፤ ጊዜ እንዳመጣው የሚመጡ፣ ጊዜ እንደሚወስደው የሚሄዱ እየሆኑ ወደ ዓለም በጊዜ እንደመጡ ከዓለምም ተለይተው በጊዜያቸው ይሄዳሉ። አየህ የዘላለም ሕይወት ሲጠፋብህ? ጊዜው ጀምሮ፤ ጊዜው እንዳደረገው አድርጎ፤ ጊዜው ይጨርስሃል። በጊዜዎች መካከል የአንተን ማንነትና ጸጋ ሳትፈልገውና አግኝተህ ሳትጠቀምበት፤ ጊዜው ላንተ የሚስማማህን ብቻ እንዲያቀይልህ የማይጠቅምህን እንዲወስድልህ ሳትቆጣጠረው፤ ሳትሞት ከውስጥ በጊዜዎች ውስጥ ሞተህ ደግሞ እንደገና በአካልም የምትሞትበት ጊዜ ሲደርስ ወደ መቃብር ትወርዳለህ።

ክርስቲያኖች የዘላለም ሕይወትን አጥተው የጊዜዎች ሕይወትን ይመሩ ዘንድ እንዳይገደዱ ኢየሱስ ክርስቶስ ወገናችን ሆኖ የዘላለም ቃሉን አሰማን። ምንድነው ያለን? "ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው" ነው ያለን። የሰው ልጆች በሰማይ አምላክ ዘንድ ባለ በዘለ-ዓለማዊ ሕይወት መያዝ አለባቸው። ለዚህ ደግሞ ስለ ዘለዓለማዊ ሕይወት ቅዱስ ቁርባን ይወስዳል ማለት ነው።

የክርስቶስን ሥጋና ደም መውሰድ ስትጀምር የአንተና የዓለም ጊዜዎች ቅርጻቸውን ወደ ዘላለማዊነት እየቀየሩ ይመጣሉ። የዕድሜ ሰዓቶችህና የዘመን ሰዓቶች ቅጽበታዊ የኑሮ ሁነታቸውን እየለቀቁ ሊቀይ የሚችለውን ሊጸና የሚችለውን ለማምጣት መሄድ ይጀምራሉ። የጌታችንን ሥጋና ደሙን መቀበል ስንጀምር ዘላለማዊነትን መኖር የምንጀምረው በሚከተሉት ሁለት ውስጣዊና ውጪያዊ መንገዶች ነው። በአንደኛው፤ እግዚአብሔር አምላክ ከምድር አፈር አበጅቶን ሰው ሊያደረገን ሕያዊነት አካለ እስትንፋሱን ነፍስ አድርጎ በውስጣችን ሲያኖራት፤ ከውጪ የምንቀበለው የእግዚአብሔር አምላክ ሕያው ሥጋውና ሕያው ደሙ ለነፍሳችን ምግብና መጠጥ

ይሆንላታል። ስለዚህ ቅዱስ ቁርባን የሕይወትህ ክፍል በሚሆንበት ጊዜ ዘላለማዊነት ከነፍስህ ውስጥ ስለሚጀምርና እየገዘፈም ስለሚመጣ ውስጣዊ ሕይወትህ ዝም ይላል።

ዝምታው የሐዘን፣ የመቆዘም፣ የመባዘንና የመቀራመድ ሳይሆን የመረጋጋት ዝምታ ነው የሚሆነው። የእፎይታ ዝምታ ከውስጥ ይሰማሃል። ቢሆንም ባይሆንም ላንተ ምንም የማይሞቅ የማይበርድ አይነት የሚንሳፈፍ ማዕበል ቢመታው የማይናወጽ እንደሐይቅ ጠለል በዝግታ የሚንሸዋሸው ዝምታ ከውስጥ ይሰማሃል። ከውስጥህ ያለው በሥጋና ደሙ መቅ'ደስ በኩል የመጣው የሰላም ዝምታ፤ ብትታመም የማይደነግጥ፣ ብታጣ የማይሰጋ፣ ብትራብ የማይጨነቅ፣ ቢሞላልህ የማይፈነጥዝ፣ ቢተረፈረፍህ የማይኮፍስ፣ ብትጠግብ የማይወጣጠር ሰው አድርጎ ይቀርጽሃል። ቢመችህም ባይመችህም ዘወትር የውስጥ መረጋጋትና የማይሸበር እፎይታ ያለው ሰው ትሆናለህ። ሁለተኛው፤ ሥጋና ደሙን በተደጋጋሚ በመቀበል የሕይወት ልምድ ውስጥ ሕይወትህን ስትቀድሰው ተፈጥሮ ወዳንተ እያዘነበለ፤ ላንተ እየታዘዘ፣ አንተን እያገዘ፣ የምትለውን እየሰማህ የምትኖርበትን ዘላለማዊነት ከውጪ ባለው ገጽታ በሚታይ እውነት ውስጥ ይሰጥሃል።

## ተፈጥሮን እንግዛው ወይስ ይግዛን ?

እግዚአብሔር አምላክ ተፈጥሮን አንጾና አስተካክሎ ከፍጥረታት ጋር ሲያኖራት፤ የሰው ልጆችን እንደ አባትነቱ ይሆን ዘንድ በፍጹም ፍቅሩ ለይቶ ሲፈጥር በእስትንፋሱ ሥልጣንነት በኩል እግዚአብሔርነት አካፍሎናልና ተፈጥሮ እንድታገለግለን ፍጥረታትን እንድንገዛ አክብሮ ቀረጸን። ተመልከቱ እስኪ በኦሪት ዘፍጥረት 2፥19 ላይ ምን እንደሚል። "እግዚአብሔር አምላክም የምድር አራዊትንና የሰማይ ወፎችን ሁሉ ከመሬት አደረገ፤ በምን ስም እንደሚጠራቸውም ያይ ዘንድ ወደ አዳም አመጣቸው፤ አዳምም ሕያው ነፍስ ላለው ሁሉ በስሙ እንደ ጠራው ስሙ ያው ሆነ።"

ይሄ ድንቅ ገርነቱ ነው። የምድር ፍጥረታትን ሁሉ በየወገን ወገናቸውና በየነገድ ነገዳቸው ካበጃቸው በኋላ ስም የማውጣት ኃላፊነትን ለአዳም ሰጠው። በል እንደምትፈልግ ሰይማቸው ላንተም ይሁኑልህ ብሎ ሰጠው። ፈጥሮ የሚሰጥ ጌታ አያችሁ? እንካ እንጂ አምጣ የማያውቅ አባት አያችሁ? አዳምም ለእንስሳትና ፍጡራት ሁሉ ስም ሲሰጣቸው፤ ስማቸውም ጸድቀላቸው እንዲታዘዙት በዙሪያው ሆኑ። ከፍጥረታቱም ደግሞ አሻገረና የፈጠራት ተፈጥሮን አዳም እንዳሻው እንዲያበጃትና እንዲጠብቃት ሰጠው። "እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በዔድን ገነት አኖረው።" (ኦሪት ዘፍጥረት 2፥15)

ዛሬ ይሄ እውነት ከሰብአዊነት ማዕከላችን ርቆን፤ እንኳንስ ተፈጥሮን ልናበጃትና ልንጠብቃት ይቅርና የራሳችንንም ሕይወትና ዘመን ማስተካከልና መጠበቅ ተስኖን ከተፈጠርንበት ሞገስና ጸጋ ሸሽተን የምንኖር ድኩማኖች ሆነን ሰንገላወድ ሰንገላወድ እንዲሁ እየኖርን ስንቶቻችን የተፈጥሮና የመኖር ሚስጢርና ጣዕም ተደብቀብን ቀረን? በእውነት ማስተዋል ይሰጠን ወገኖቼ።

ስንጀምረው ተፈጥሮ ለኛም ትሠራ ዘንድ ነበረ የተፈጠረቺው። መጽሐፈ ኢያሱ ምዕራፍ 10'ን ስታዩ፤ ኢያሱ በእግዚአብሔር ፊት ፀሐይን በገባዖን ምድር አቁሟታል። ጨረቃንም አዘግይቷታል። እኛ አሁን እግዚአብሔር ፊት መቆም ስላቃተን ለተፈጥሮ ብቻ ለመሥራት ተገድደናል። አልፎም ተርፎ አንዳንዴ ተፈጥሮ ስትከዳን ለመኖራችን አደጋም ጭምር ታመጣብናለች። የእግዚአብሔር ሕዝቦች ባሕር ከፍለው ተሻገሩ የሚለውን ታሪክ ክርስቲያኖች በመጽሐፍ ቅዱሳቸው ይዘው፤ ዛሬ ከአገር ሊወጡ ሲሹለከለኩ፣ እንደ ዕቃ ሲጫኑ ሲወርዱ፤ ባሕር ደርምሷቸው ስንቶች የዓሳ እራት ሆነው እንደቀሩ ቤቱ ይቁጠረው። በተፈጥሮ አደጋ ምክንያት ስንቶች አለቁ? መሬት ሲንሸራተት የስንት ሰዎች ሕይወት አብሮ ተንሸራተተ? የጎርፍ ውኃ ስንቶችን እያላተመ ወሰደ? የእሳት ሰደድ የስንቶችን ሕይወትና ኑሮ አነደደ? የአውሎ ነፋስ ወጀብ ስንቶችን ለሥርዓተ ቀብር አስክሬናቸው እንኳ እንዳይገኝ አርቆ ቀበራቸው? አየህ እግዚአብሔር የሌለው የሰው ልጅ? በተፈጥሮ ሥር ነው። አሁን በዚህ በየምዕራባውያኑ

እና ሩቅ ምሥራቃዊያኑ ውስጥ ያሉ አገሮች ኗሪ ዜጎች ከአሁን አሁን መሬት ከዳችን እያሉ ከሚመጣው አደጋና ሰቀቃ ለመትረፍ ቤት ሲሠሩ፣ መንገድ ሲገነቡ፣ ኢንደስትሪ ሲተክሉ የተፈጥሮ አደጋን መቋቋም እንዲችል አድርገው ነው። ለዘመናትም በዚህ የተፈጥሮ ግብ ግብ መካከል የኖሩ ዜጎችም ተፈጥሮን እየፈሩ፣ ተፈጥሮን ባለማመን እየጠበቁ፣ ተፈጥሮን አጨንቁረው እያዩ ይኖራሉ።

ተፈጥሮ እንድታገለግለን ነፍሳችን በእግዚአብሔር አምላክ በኩል ተቀድሳና ተባርካ ስትገኝ፤ በዘመነ ፍዳ የዲያቢሎስ ክንድና አገዛዙ ሰልጥኖ፤ ከሕግ በታች አድርጎ፤ የሰው ልጆችን በዘር ጉዳትና ውድቀት ውስጥ አስሮ፤ ስጦታችንን ሲፋለም የኖረበትን ዘመን ወደ ምሕረት ሊለውጠው እግዚአብሔር ቃል ፍቅር ይዞት ሥጋ ሆኖ፤ ጸጋንና እውነትን ተመልቶ ወደጊዜና ሕይወታችን መጣ። ሲመጣ ከሰጠን ታላቁ ሰማያዊ የመለኮቱ በረከቶች መካከል አንደኛው ሥጋና ደሙ ነው። ሥጋና ደሙን ስንወስድ፤ እርሱን መውሰድ ማለት  እንደሆነ በቃሉ አረጋግጦ ነገረን በዮሐንስ ወንጌል ላይ። " ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ።"

እስኪ እንደው ሞኝ አትሁኑ እንደው። ክቡር ሥጋውን ቅዱስ ደሙን ስትቀበሉ ተፈጥሮን ማገልገላችሁ ይቀርና ተፈጥሮ እኛን ለማገልገል ወደ ኑሮአችን ትታዘዛለች። እነሆ፥ ተፈጥሮ ላንተ እንድትስማማ የክርስቶስ ሥጋና ደም ያስፈልግሃል። "የሰማይ አባታችን ሆይ፥ ለአዳም የሰጠኸውን ጸጋና ሞገስ እንዲሁ በኔ ሕይወትም ስጠኝ። ጊዜና ዘመን እንዳይገዛኝ የሕይወቴን መግቢያ መውጫ ተቆጣጠረው። የመኖርን ሚስጢር ከሰማያዊ ስጦታዎችህ ጋር ግለጥልኝ።" ብለህ ቅዱስ ቁርባን ስትወስድ ያን ጊዜ የተፈጥሮ ባለቤት መሆን ትጀምራለህ። ጊዜ አንተ ስለለፋህ ብቻ ሳይሆን ጊዜው አንተን ሊያግዝህ የማያቋርጡ ዕድሎችን እየያዘ ወዳንተ ይመጣል። ሁኔታዎች አንተ ስለተጨነቅላቸው ሳይሆን ሁኔታዎች ላንተ ሊጨነቁልህ ወዳንተ ይገሰግሳሉ። በረከት አንተ ስለደከምክለት ብቻ ሳይሆን፤ ስለወጣህ ስለወረድክለት ሳይሆን፤ በረከት ካንተ ጋር ለመሆን ወዳንተ ይመጣል። የሚደግፉህና የሚያበረቱህ ልበ ቀና ሰዎች ሳትጠራቸው ወዳንተ ይመጣሉ። የሚያስፈልግህን ሁሉ በጊዜ ጊዜው እንድትሰጥህ ተፈጥሮ ከሰማይ አምላካችን ትእዛዝ ትቀበላለች። በቃ ከዛ በኋላ ዓለምና ዲያቢሎስ የቱንም ደረጃ ያህል ቢሮጡ አይቀድሙህም። ክፉዎች የዘጉት በር ሁሉ እየተከፈተ የከፈቱትም ሁሉ እየተዘጋ፤ የበረከትና የሰላም ገባር ወንዞች ወዳንተ የሕይወት ወንዝ ያለማቋረጥ እየመጡ ይቀላለቀሉ። እግዚአብሔር ስሙ የተመሰገነ ይሁን።

ይሄ የሚሆነው ግን በመጀመሪያው አቋም ሲኖረን ነው። በተሰበረ ልብና የእውነት ፍቅር ወደ እግዚአብሔር የመጠጋት ቁርጠኝነት ሲኖረን ነው። በቅዱስ ቁርባኑ በመቀ'ደስ ከውስጥም ከውጪም የዘላለማዊነትን ቅርጽና ገጽታ መያዝ ስትጀምር ተፈጥሮ ለአዳም እንደታዘዘቿውና እንዲጠብቃትም እንደተሰጠቺው ወዳንተ እርዳታዎችንም ልታደርግልህ ትመጣለች። የዛሬው ትውልድ ተፈጥሮ የሸሸቺው ትውልድ ነው። ዓለም ሲደነግጥ አብሮ የሚደነግጥ፣ ዓለም ሲፈራ አብሮ የሚፈራ፣ ዓለም ሲሸወድ አብሮ የሚሸወድ ትውልድ ነው በአብዛኛው ያለው። ስለዚህ የሕይወት ምሪቱንና የራእይ መረጃዎቹን ከቴሌቪዥን፣ ከኢንተርኔት፣ ከጋዜጣና የመገናኛ አውታሮች ብቻ የሚጠብቅ እየሆነ፤ ዜናዎች ሲጨክኑ እየተሳቀቀ፣ ዜናዎች ሲያበስሩ እየፈነጠዘ፣ ዜናዎች ሲወሳሰቡ ግራ እየተገባ የሚኖር እየሆነ ይገኛል።

## ክፍል - 8

### ሰማያዊ መልስ

የሰው ልጅ የሕይወት ዕድሜ ዘመን አኗኗር ጉዞ መካከል ላይ ያሉ፣ የሚመጡ እና እንዲሁ ያለፉ የዕለት ዕለት ኑሮ ክስተቶች ውስጥ የሚፈጠሩ ጥያቄዎች አሊያ መጥራት የሚፈልጉ ውዥንብር ገጠመኞች በአብዛኞቻችን ልብና ሕሊና ውስጥ ይኖራሉ። አሁን ታዲያ እነዚህ የሕይወት ጥያቄዎችን እና የዘመን እንቅቅልሾችን አስረግጠን

መመለስ እና ማጥራት ካቃተን፤ የዕድሜያችን የቀይታ ርዝመቱ መውጪያ መግቢያው ላይ አንዳንዴ ዙሪያው ሁሉ የጥያቄ ጉርምርምታ ውስጥ እየገባ ልቦናችንንና አእምሮአችንን ያስጨንቀናል።

ዛሬ ዛሬ ላይ በተለይም ሕይወት በራሱ ጥያቄ ውስጥ ገብቷል። ኑሮው ራሱ የተሸከመው ጥያቄ አለ፣ ትዳራችንም ውስጥ ጥያቄ  አለ፣ የቤተሰባችንም ሕይወት ውስጥ ጥያቄ አለ፣ እውቀታችንም ውስጥ ጥያቄ አለ፣ ንብረታችንም ውስጥ ጥያቄ አለ፣ ዕድላችንም ውስጥ ጥያቄ አለ። እሺ እንግዲህ ለነዚህ ጥያቄዎች ማን መልስ ይስጥ? ማንስ ከውዥንብር እንቀቅልሾቻችን ያሳርፈን? የገነባናቸው ትላልቅ የትምህርትና የምርምር ተቋማት ለምን እስከ ወዲያኛው የሚያሳርፍ መልስ አይሰጡንም? በሳይንሱና በግኝቱ ዘርፍ ያመረትናቸው የቴክሎኖጂ ውጤቶች ለምን የውስጣችንን ጥያቄ በተገባ መመለስ አልቻሉም? በመንግሥትም ሆነ በሕዝባዊ መዋቅር ግንባታ ውስጥ ያቋቋምናቸው የተለያዩ ማኀበራት መልሳቸው ለምን የምንፈለግው ጥያቄ ላይ አጥጋቢ ምላሽ አላስገኘልንም?

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የጌታችን ቃል " ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ፥ ይከፈትላችሁማል።" ይላል ማቴዎስ 7፥7 ላይ። ቁጥር 11 ላይ ደግሞ እንደዚህ ይላል። " እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠትን ካወቃችሁ፥ በሰማያት ያለው አባታችሁ ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መልካም ነገርን ይሰጣቸው?" ይላል። ይህንን ሰማያዊ ቃሉ ለደቀመዛሙርቱ አሰማቸው ሲል ጻፈ ቅዱስ ማቴዎስ።

ከዚህ የተሰፋ አምላክ የተሰፋ የእውነት ቃል ላይ እምነታችንን ማቀም ያቃተን እኛ የሕይወትና የኑሮ ጥያቄዎቻችንን ወደ ሰማያዊው አባት መውሰድ የምንችለበት መንገድ ስለማናውቅ፤ የመልሶቻችን ምንጭና አድራሻ ከምድራዊ የቴክሎኖጂው መረብ አሊያ የመገናኛው አውታረ ዓለም ውስጥ ብቻ እየፈለግን እየፈለግን ዓመታትን ከመወለድ ጀምሮ ሰንባዝን ለጊዜው የሚያስታግስ የሚመስል ምላሽን ብናገኝም ሊቀይ የሚችለውን መልስ ከማግኘት ይልቅ ወደሌላ ጥያቄ እየተሸጋገርን፤ ወደ ሌላ አጀንዳና ርዕስ እየዘለቅን፤ ተረጋግቶ ለመኖር የሚፈቅድልንን የውስጥ ሕይወት የሰላምና የእፎይታ አንድነት ተነፍገን፤ የነበረውንም፣ ያለውንም ሆነ የሚመጣውን በአብዛኛው 'መሰለኝ' እያልን በሚመስል ሕይወትና በሚመስል መርህ ውስጥ ብዙ ቀይተን ስናበቃ፤ አሁን ሁሉም ነገር የሚመስል እየሆነብን የእርግጠኝነት ኃይልና ድጋፍ ተለይቶን በግምት ብዙዎቻችን እንኖራለን። "እንዲህ ይመስለኛል፣ እንዲህ ሊሆን ይችላል፣ እንዲሁ የሚቀጥል ይሆናል፣ ምናልባት እንዲህ ቢሆንስ" ብለን ውሉ ያልረገጠ መልስ የሰጠንባቸው ወይንም መልስ የተቀበልንባቸው ነገሮችን መለስ ብለን ስንመለከታቸው፤ ከመላ ምቱ አካሄድ ያፈነገጡ፣ በምንጠብቀው መስመር ላይ ያልሄዱ፣ ካሰብነው በተቃራኒው አቅጣጫ የሚጓዙ ሲሆኑብን አሊያም በጠበቅነው ፍፃሜ ሥር ተሳክተው ቢገኙ እንኳ ሌላ የማንጠብቃቸው ጅማሮዎችን እያስነሡ የሕይወታችንን ገሚሱ ክፍል በእጅጉ የተፈታተኑ ሆነው ለረጅም ዘመናት ሕልውናችንን መፋለማቸውን ለማስተዋል አቅቶን፤ የመኖር ትርጉም እስኪደበዝዝብን ድረስ ለብቻችን ሆነን ከልባችን ጋር በተወያየን ቁጥር በሕሊናችንም በነፍሳችንም እንጨነቃለን።

የእግዚአብሔር አምላክ ሰማያዊ መልስና የራእይ ምሪቶች ከጊዜያችንና ከሕይወታችን ውስጥ ለመገኘት የሚችሉበት ዕድሉን ሲያጡ፤ በምትኩ የአኗኗራችን ገጽታ ለመላበስ የሚገደደው አካኋን ምን አይነት ይሆናል? የሚለውን ስንመለከት፤ አንደኛው ላይ በእኛችን ላይ አልጠራ ብሎ የሚያፋትገንን ጥያቄና የሕይወት ግርግር መፍታት አቅቶን ግራ ስንጋባ፤ ሁለተኛው ላይ የሚመጣውን ለማወቅ የምንችልበት ምንም መንፈሳዊ ኃይል በአምልኮት ሕይወት ውስጥ ያልያዝን በመሆኑ የቅርቡ የቅርቡን ብቻ ለመከተል እንገደዳለን። እስኪ አሁን ቀስ በሉና ኑሮአችሁ የመጣበትን መንገድ ተመልከቱት። በአጠገባችን ቁመት ልክ ከአፍንጫችን ሥር ያሉት ክንውኖችን እያየ አብዛኛው የኑሮአችን መሠረት ስለተሠራ፤ የአኗኗራችን መስመር በጣም በፍጥነት ቅርጽና ይዘት የሚለዋወጥ እየሆነ ውስጣዊ ማስተዋላችን ከአቅማችን ጋር እስከደከመበት ርቀት ድረስ እየተለዋወጥን ስንኖር

ስንኖር የከርምን በመሆናችን፤ ልምድ እንጂ የነፍስ ፈቃድ አይገዛንም። ስሜት እንጂ ሰማያዊ እውነት አይኖረንም። ፍላጎት እንጂ የተጨበጠ ውሳኔ አንይዝም።

ለነባራዊውም ሆነ ለሚመጣው ሕይወት የሚሆን የሰማይ አምላክ ብርሃን ከጥበቃው ኃይል ጋር በዘመናችን ውስጥ ካልተገለጠ፤ የመንገዳችን ጉዞ በጨለማ የተዋጠ ስለሚሆን ዓለም ባበራቸው ጠፊ ብርሃን በኩል ለመታገዝ ስንሞክር፤ ደሞ ጉልበት ያላቸው አመፀኞች የግል ብርሃናችንን እየነጠቁ፣ ክፉዎች ሲሆኑ በአጥፊነት ኃይል እየቀደሙ፣ ተንኮለኞች ሲሆኑ የኛን አታለው ሲወስዱ፤ ምቀኞች ሲሆኑ የኛን ብርሃን ለማጥፋት በስውር ሲታገሉ፤ የሃይማኖት ጉዞ የማይገባቸው ሲሆኑ በጨለማ ተውጠው ጽልመትን እንድንለምደው ሲያግባቡን፤ ቀድመን ነቅተን ስላልገባን በራሳችን የኑሮ ሰፋት ልክ ውስጥ ባለው አቅምና ጉልበት ተመርኩዘን ብርሃን ውስጥ ለመቆየት ያደረገነው ዘመቻ ብዙ ቦታ ላይ ገንዘብና ሕልውናችንን አድክሞት ተስፋ ቆርጠን የተቀመጥን ዓይናማ እውራኖችን የመሆናችን ምክንያቱ ሌላ ምንም አይደለም። ሰማያዊ ብርሃንና የሕይወት መልስ እንደሚያስፈልገን ገና ለማመን የተዘጋጀን ስላልሆንን ተጨማሪ የመከራና የፍዳ ዘመናትን አሳልፈን ዙሪያ ገባው ሁሉ ከመፍትሔ አማራጮች በሙሉ ተሟጦ እስኪያልቅ ድረስ እየተሰቃየን እንቀያለን።

ለሕይወታችን፣ ለኑሮአችን፣ ለሕውልናችን የሚሆነው ጥያቄ ላይ ሰማያዊ መልስ ሊሆን እግዚአብሔር ሲናገር እንድንሰማው አንደኛ፤ "እግዚአብሔር ሆይ፥ አንተ ተናገር" ማለትን በሕይወታችን አኗኗር ውስጥ ከባሕሪያችንና የሥጋ ፈቃዳችን ትግል ጋር በተግባር እያለፍን መንፈሳዊ ግንዛቤያችንን መተርጎም አለብን። እኛ የምንናገረውን መጨረስና የእርሱን ለማዳመጥ ዝግጁ መሆን አለብን። አንዳንዶቻችን እግዚአብሔር ለሕይወትና ውስጣዊ ሕልውናችን ውስጥ ለሚመላለሱ ጥያቄዎቻችን መልስ እንዲሰጥ የራሳችንን ጉዞ ጨርሰን የእርሱን እንዲጀምር ቦታ አልሰጠነውም። ታዲያ እንዴት ይሆናል? ሥራውን እንዲሠራ መንገዱን ካለቀቅንለት እንዴት ይሁን?

ሁለተኛ፤ ራሳችንን ለእግዚአብሔር ቃልና ለቃልኪዳኑ ተስፋ በታመነ ሕሊና ውስጥ ፈቃደኛ ሆነን መስጠት አለብን። እነዚህንም ስናደርግ እግዚአብሔር ሲናገር ለመስማት፤ እግዚአብሔር ለሕይወታችን ጥያቄ መልስ ሲሰጥ ለመስማት፤ እግዚአብሔር የሚመጣውን ሁኔታ ከወዲሁ በሚያስፈልገን ልክ ሲያስተውቀን ለመስማት ዕድሉን እናገኛለን። እንግዲህ ከዚህ መንፈሳዊ እውነታና ኃይል ርቀን እግዚአብሔር ሲናገር ማድመጥ ካቃተን ዓለም ስትናገር መስማት ግዴታችን ይሆናል። ሰዉ ይናገራል። ርኩስ መንፈስ ከሰው ትከሻ እየተከለለ ይናገራል። ዘመንና ጊዜ የራሳቸውን ይናገራሉ።

## እግዚአብሔር እንዲመልስልን እንዴት እናድርግ?

በብዙ የዓውደ ምሕረት የስብከትና የመንፈሳዊ ትምህርት ድምፆች ውስጥ "ሰው አምላክ ሆነ፤ አምላክ ሰው ሆነ" የሚለውን ቃል ስንል አሊያ ስንሰማ እንገኛለን። አምላክ ሰው በመሆኑ ሚስጢር ውስጥ፤ ሰው በመሆኑ ጥበብ ውስጥ፤ ለኛ ያለው ፋንታ ምንድነው? የጽድቁና የበረከቱ ስጦታ ምንድነው? የሚለው ጉዳይ ላይ ትኩረት መስጠት ያስፈልገናል።

ቃል የመለኮት ባሕሪይ ሆኖ ሳለ የሰው ልጅነትን ለመዛመድ ሥጋ ሲሆን፤ አንደኛው የፍቅሩ ኃይል የተገለጠው እኛን የሆነበትን ሥጋውንና ደሙን መልሶ ለኛው መስጠቱ ነው። በማቴዎስ ወንጌል የመጨረሻው ምዕራፍ የመጨረሻው ንባብ ላይም "እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእናንተ ጋር ነኝ" የሚለው የሕያውነት የተስፋ ቃልኪዳን በልባችንና በሕይወታችን ተተርጉሞ የሚጸድቅበት ቦታ ላይ መንገዱ በእውነት ስለጠፋን፤ እስከ ሕይወታችን ፍጻሜ አብሮን ምን እንደሚዘልቅ በውል አናውቅም። ኑሮአችንን በራሳችን መንገድና አሳብ በኩል ጀምረነው ማብቂያው ላይ የምናዝን ከሆነ እንደገና መልስ ብለን እስከ ፍጻሜ ድረስ አብሮን ሊሆን የሚችለውን ኃይል መፈለግ ይኖርብናል።

እግዚአብሔር ሰማያዊ መልሱንና የራእዩን ኃይል ይገልጥልን ዘንድ በመጀመሪያው #አብሮን_መሆን_አለበት። ይኸውም በዕለት ዕለት አምልኮትና በጸሎት በሚገኝ መንፈሳዊ ግንኙነት ውስጥ ሊመጣ የሚችል ኃይል ሲሆን፤ የአንድነቱ ማጽደቂያ ማኅተሙ ደግሞ ሥጋውና ደሙ ይሆናል። << ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ። >> ነው ያለን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ።

ቅዱስ ቁርባን የሚወሰደው ሰማያዊ መልስ እንዲኖር፤ አገር፣ አከባቢ፣ ጎረቤት፣ በሁሉም መንገድ ጥያቄ ውስጥ ሲገባ፤ ጭንቀ ወይም ጦርነት አሊያም አልጠራ ብሎ በደበዘዘ ጉዳይ መካከል ላይ አስፈሪ ነው በምንለው ነገር ላይ ቅዱስ ቁርባን እንወስዳለን። መልስ ጠፍቶኛል፣ የሚመራኝ ጠፍቶኛል፣ ግራ ገብቶኛል፣ ሚስጢሩና እውነቱ ተደብቀብኛል፣ ውስጡና ፈለጉን መከተል አቅቶኛል፣ ሕይወት እንቆቅልሽ ሆኖብኛል፤ አስጨናቂና የማይፈታ ውስብስብ ሆኖብኛል፤ በምንለው ነገር ላይ ምን እንወስዳለን? ቅዱስ ቁርባን እንወስዳለን። ቅዱስ ቁርባን ስንወስድ በሕይወት ጥያቄአችን ውስጥ የተደበቁትን፤ ስለሚመጣው የኑሮአችን መስመር አቅጣጫ የአካሄድ መረጃ ስንፈልግ፤ በምድር ላይ ያሉትን ከኛ እውቀና ውጪ የራቁትን ምናምንቴ ነገሮች ሁሉ፤ በዙሪያችን አድፍጠው በረከትና ሰላማችንን የሚዋጉትን ጠላቶች ሁሉ ከነባሕርያቸው እግዚአብሔር ያስታውቀናል። ከዛ በኋላ ከምናምንቴ ጋር ምናምንቴ አንሆንም፤ ከሚታመሰው ጋር አንታመስም፤ መሄጃ አጥቶ ነገር ግን መድረሻውን አዋቂ መስሎ ከሚደናበረው ጋር አንደናበርም። በተሳሳተ አቅጣጫና የተሰናከለ ጎዳና ከሚነጉደው ጋር አንነጉድም። እንዴት? ለምን የእግዚአብሔርን ሰማያዊ እጅ የበረከት እጅ ይዘን በዚህ ስለዚህ በጠላቶቻችንና በዓለም ፊት የምንወድቅ ሳይሆን የምንቆም ስለምንሆን ነው።

የዘመኑ ትውልዳችን ቅዱስ ቁርባንን ከመቀበል የበሽታ መቅሠፍትን መቀበል፤ ጊዜና የእርግማን ፍሬ የሚያመጣውን መዓት መቀበል፤ ሰማያዊ መልስና ብርሃን በተለየው በእውር ድንብር መንገድ ላይ መጓዝ የቀለለው እስኪመስል ድረስ ሥጋና ደሙ የቋጥኝ ያህል ሲከብደው፤ የሚታየው ሁሉ በሃይማኖት አንገት ላይ የቀመ አኗኗር እየሆነ በመናፍስት ወጥመድ ተከርችሞ፤ መግባቱም መውጣቱም ያልተለየ ኑሮን የሚመራ ትውልድ ብንመለከት አይደንቅም። ዓለም በርኩሳን መናፍስት የሴራ አገዛዝ ሥልጣን በኩል ምድራዊ ኃይልን እያሰፋችና እያረቀቀች ወደፊት ወደ መጨረሻው ስትፈጥን፤ እኛ የራሳችንን ትተን የሌላውን ለማምጣት በምንታገልበት ውጣ ውረድ ውስጥ፤ ኑሮው የራሱን አዚምና ድካም እየለቀቀብን ሲያመሰቃቅለን፤ መከራንና ድካምን ደግሞ እንደገና ለምደነው እንደዚሁ ለየዕለት ዕለት ግኝት ብቻ በዝግታ እንተንቀሳቀስን በተልፈዘፈዘ ሕሊናና አካሄድ ለዘመናት መጥተን ዛሬን የተገኘነበት የመንፈሳዊ ኃይል ጸጋና ራእይ የተጋድሎ መስመሩ ላይ ቀጥኖ ሲላላብን፤ ምን ያህል ሁለ ገብ ክሥረት እንዳስተናገድን ይኸው በሕይወታችን ውስጥ እንደ ግልም እንደአገርም ተገልጦ ሲነበብ፤ ለሌሎች አገራት የታሪክ ሐብታሞች ብቻ ሆነን ለዛሬ ከውድቀት መማሪያ ሲያደርጉን፤ ታዲያ ምን ይሻላል እስኪ? እርሱ "እናንተ ሸክማችሁ የከበደ ሁላችሁ ወደኔ ኑ" ነው ያለው። ወደ ክርስቶስ ለመሄድ እንቢ ስንል ኑሮአችን የነፍስ ሕይወት አጣ። የሥጋ ሕይወት ብቻ ያለው የነፍስ ሕይወት ያጣ ማለት የነፍስ በድን ነው ማለት ነው። በድን የሆነ ግዜ፣ በድን የሆነ ዓመት፣ በድን የሆነ ኑሮ፣ በድን የሆነ በረከት፣ በድን የሆነ ቤት፣ በድን የሆነ ሐብት ይዘን ቆይተን በመጨረሻው ራሳችንም በሥጋ በድን እንሆናለን። የሕይወትን ትርጉም ያጣ ሰው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ከባሕሪው ውስጥ ያልተገኘለት ሰው፤ መንፈሳዊ ኃይል ከጊዜና ዘመኑ የተለየበት ያ ሰው ሕይወት የለውም በቃ። በሕይወት አለን፤ እየኖርን ነው፤ ለማለት መተንፈስ ብቻውን ሙሉ መዝገቡን አያሟላም። ዝም ብሎ መተንፈስንማ ዛፎቹም ይተነፍሳሉ። ሊያውም ከኛ በተሻለ ንጹሕ አየርን ነው ወደ ውጪ የሚተነፍሱት። መርዛማውን አስገብተው፥ ንጹሑን አየር ያሰወጣሉ። እኛ በተፈጥሮም ስንተነፍስ ንጹሑን ወስደን መርዛማውን እናስወጣለን። ኑሮአችን ደግሞ ከነክፋቱ፣ በዛው የነፍስ ሕይወት ባጣበት፣ የርኃርኄና የፍቅር ኃይል እንደተለየው ሲተነፍስ ደሞ ይባሱን፥ መርዛማውን አስገብቶ መርዛማውን ያስወጣል። እንደዚህ በሚሆንበት ግዜ አንዱ ለሌላኛው መርዝነቱን እያስተላለፈ፤ ሕይወት የሚሆንን ቃል፣ ሕይወት የሚሆን ደግነት፣ ሕይወት የሚሆን በረከት ከዘመኑና ከትውልዱ ውስጥ ጠፍቶ፤ የሞት ሽታዎች የሚሰራጩበት ሕይወት አልባ ጊዜ የኛም ጊዜ ይሆናል።

"ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም።" (የዮሐንስ ወንጌል 6፥53)

## ክፍል - 9

## ክርስቶስ ከኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል ?

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጻፉ ታላላቅ የእምነት ኃይሎችን ከሚገልጹ ቃላት መካከል አንደኛው ወደ ሮሜ ሰዎች 8፥31 ላይ ያለው፤ " እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል?" የሚለው ግሩም ቃል ነው። ጥያቄ ነው የሚጠይቀው እንግዲህ። ማን ይቃወመናል? የሚል የእምነት ድጋፍና ኃይል ያለው ጥያቄ ይጠይቃል። የእኛስ ኑሮ እንዴት ነው ይሄ በጠላቶች ግርማ ፊት መቆም የሚችል፤ የክፋትን ወጥመድ ጥሶ ማለፍ የሚያስችል፤ መልሱን የጨረሰ ጥያቄ አያስፈልገውም? ማን ይቃወመናል የሚለው የምርኩዝነት መታመኛ ለኛ አያስፈለገንም?

ክርስቲያኖች << ክርስቶስ ከኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል? >> የሚለውን የተሰፋ ቃል ከልብና ከሕይወታቸው ውስጥ ሲያጡት፤ በሄዱበት በደረሱበት ቦታ ላይ ሁሉ የተቃውሞ ኃይል፣ የፍርሃት ኃይል፣ የጭንቀት ኃይል የሚያገኛቸው እየሆኑ እየተሳቀቁ እንዲኖሩ በአጥፊ መናፍስት የውስጥም የውጪም ግፊት በኩል ይገደዳሉ።እውነትም ሲታይ ታዲያ ዛሬ ዛሬ በፍርሃትና በጭንቀት ጦርነት መካከል የምንመላለስ ሰዎች ጥቂቶች አይደለንም። "እግዚአብሔር ከኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል?" የሚለው ጥያቄ ውስጥ፤ የቀደመው "እግዚአብሔር ከኛ ጋር ከሆነ" የሚለው የሰውና የአምላክ አንድነት ማረጋገጫ የሆነው ቃል ነው። ብዙዎቻችን እግዚአብሔር ከኛ ጋር እንዲሆን የኑሮአችንን ቦታ መክፈት ስላቃተን፤ ከየአቅጣጫው የሚቃወመን በዝቶ መውጫ መግቢያችን ሁሉ በራሱ ያለ ምክንያት የሚያስፈራራ እየሆነ የፍርሃት ኑሮ እንኖራለን። ብዙ ነገር ነው የሚያስፈራን። ባለንበት የቴክኖሎጂና የሳይንስ ዘመን ጭንቀትና ፍርሃት በፍጥነት እየተዛመቱና ሥር እየሰደዱ የመጡ የግለሰቦች የውስጥ በሽታ ሆነዋል። አንዳንዶቻችን ቁጭ እንዳልን ማንም ሳይነካንና ሳያናግረን እንበረግጋለን። አንዳንዶቻችን ሥራ እየሠራንና ትምህርት እየተማርን ያለምክንያት እንጨነቃለን። አንዳንዶቻችን ደሞ ወደ ውስጣችን አስበን ስለነገው የነፍሳችን መድረሻና ሁኔታ በጥልቀት ስንመረምር ፍርሃት ይውጠናል። አንዳንዶቻችን ተኝተን እንፈራለን። በህልም ውስጥ እንፈራለን። በቃ ብዙ ነገር ነው የምንፈራው። ምድር በከፍተኛ ሁኔታ የፍርሃት የእስር ኃይል መግለጫ ከሆነችባቸው ጊዜያትና ዘመናት ውስጥ ይኸው የኛው የምንገኝበት ትውልድ ውስጥ ያለው ዘመን ነው። የፍርሃት ጉዞ እንጓዛለን። ታክሲ ውስጥ ገብተን እየፈራን እንሄዳለን። በእግርም እየተጓዝን እንፈራለን። በአውሮፕላንም ብንጓዝ ፍርሃትን መግታት ያቅተናል። በየዕለቱም የምንሰማቸው አደጋዎችም ቤታችን ቁጭ ብለን እንድንፈራ ያደርጉናል። ዲያቢሎስ በውስጥ ፍርሃት ብቻ የሚፈትንበት አሠራርና አካሄድ ብሶ በሥጋ ፍርሃታችንም ውስጥ እጁን አስረዝሟል። የምንሰማቸውና የምንመለከታቸው ሰበር የዜና መግለጫዎች በአብዛኛው ፍርሃትንና ጭንቀትን የሚነዙ ሆነው እናገኛቸዋለን። አሁን አሁንማ እንደአገርም እንደ ዓለም ዜጎችም በጋራ መፍራት የጀመርንበት ጊዜ ላይ እንገኛለን። በሽታ ያሰጋናል። ጦርነት ያሰጋናል። ችግር ያሰጋናል። አሸባሪውም ያሰጋናል። መበታተን ያሰጋናል። እንደዜጋ መተያየት አለመቻላችን ያሰጋናል። አንዱ ኢትዮጵያዊ ለሌላው ኢትዮጵያዊ አሰፈሪ የሆነበት ዘመን መጣ ይኸውላችሁ።

ቃሉ የሚለው ምን ነበረ? እግዚአብሔር ከኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል ነው የሚለው። ይህን የሐዲስ ኪዳኑን ቃል በአንድ ወቅት ላይ መዝሙረኛው ዳዊት ተናግሮት ነበረ። በመዝሙረ ዳዊት 23፥4 ላይ "በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም፤" ሲል እንሰማዋለን። አልፈራም ነው ያለው። እፈራለሁ አይደለም የሚለው። አልፈራም ሲል የመለኮትን ጥበቃንና የከለላ ኃይል የተገነዘበ ቃል ነው። አልፈራም ሲል

የማመንና በእምነትም ውስጥ ጉልበትን የማግኘቱ የማረጋገጫው ድምፅ ነው። አልፈራም ሲል ሰማያዊ ጋሻነትንንና የእግዚአብሔርን ክንድ መመሸጉን የሚመሰክር ቋንቋ ነው። አልፈራም ነው በቃ።

አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም ለሚለው ቃል አንፃራዊ በተቃራኒው ሊገኝ የሚችለው ቃል፤ 'አንተ ከእኔ ጋር የለህምና ክፉው ያስፈራኛል" የሚለው ይሆናል። ዛሬ በኛ ትውልድና ዘመን ውስጥ እግዚአብሔር ከኛ ጋር አልኖር ሲል፤ የፍቅሩና የሞገሱ ኃይል በሕይወታችን ውስጥ ስፍራ ሲያጣ፤ በመለኮታዊ ባሕሪያቶቹ ሰብአዊ ባሕሪያቶቻችንን እንዲያንጽና እንዲያፀና የሚፈቅድ የሕሊና ፈቃድ አሳልፈን ለመስጠት እንቢ ስንል፤ ፍርሃት ተከተለን። ጭንቀት ተከተለን። ከእግዚአብሔር ጋር ለመተባበር ያስቸገረ ትውልድና ዘመን፣ የመንፈስ ቅዱስ የፍቅር ጠባያቶችና የበጎነት በረከቶችን የጠላ ኑሮና የአኗኗር ጊዜ፤ የልዑል አምላክን የረድኤት ከለላንና የሰላምን መንፈስ ያልፈለገ እውቀትና ገንዘብ ምን መጣበት? ስንል በዓይናችን የምናየው፣ በጆሮአችን የምንሰማው፣ በኑሮአችን የምናረጋግጠው የክፋትና የእርግማን ፍሬን ያፈሩ ብዙ መተረማመሶች፣ ብዙ መጨነቆች፣ ብዙ ዋይታዎች፣ ብዙ ሽብሮች፣ ብዙ ግፎች፣ ብዙ ስቃዮች፣ ብዙ ሕልፈቶች፣ ብዙ በሽታዎች፣ ብዙ አመፃዎች፣ ብዙ ርኩሰቶች፣ ብዙ ግራ መጋባቶች፣ ብዙ መፍትሔ ማጣቶችን ለማስተናገድ የምንገደድበት የክፋለ ዘመን ጊዜና ወቅት ላይ መድረሳችን ምን መጣበት? ለሚለው ጥያቄ ግልፅ ውጤቱ ሆኖ ይታያል።

የዳዊት ቃል የሚለው አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራውም ነው። መፍራት ያለበትንም አውቆታል። ክፉን ነው ያለው። ምናልባት አንዳንዶቻችን የምንፈራውና የምንሸሸው የቀድስና የጽድቅ ሕይወትን ይሆናል። የእግዚአብሔርን በጎ ነገራትን መፍራትና መሸሽ በዛሬ ዘመናዊ ትውልድ ውስጥ አንዱ እጣ ፋንታችን ሲሆን ጊዜ ክፉው ከባሕሪያችን ክፍል እንደ አንዱ ሆኖ፤ ለዘመናት በቀየ የመናፍስት መደበቅ ውስጥም ክፋትን ለምደነው፤ የክፋት ውጤት ተገልጦ #መፍትሔ_አልባ_በሆነ_ሁኔታ በቤታችን እስኪመዘገብ ድረስ፤ ብዙዎቻችን ችግርን ለመገንዘብ አደጋ የምንጠብቅ እንሆናለን። የዲያቢሎስ አሠራርና አካሄድ ከዘመኑ ጋር አብሮ በተሳሰረና በተሰወረ መልኩ ብዙ ውድመቶች ብዙ ጥፋቶች በትውልዳችን ውስጥ ተስተውለው ስናይ ቅድሚያ ልንጠነቀቅባቸው የሚገባን እውነታዎች ቢኖሩንም ዛሬም መንፈሳዊ ጉዳዮችን አምኖ ለመቀበል መከራ እስኪመጣ የሚጠብቁ ሰዎች ጥቂቶች አይደሉም።

የተነሣንበት የሮሜውን ቃል እናስታውስ። "እግዚአብሔር ከኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል?" ይላል። ማን ይቃወመናል ብለን በዓለምና በጠላቶቻችን ፊት በድፍረት ከመቆማችን በፊት፤ እግዚአብሔር ከኛ ጋር ከሆነ የሚለው ጉዳይ ላይ ትኩረት መስጠት ያስፈልገናል። አሁን እንዴት ነው ታዲያ እግዚአብሔር ከኛ ጋር የሚሆነው? የሚለውን አስፈላጊና ቀዳሚ ጥያቄ ስንመልስ፤ እግዚአብሔር ከኛ ጋር ከሆነ የምንለው በቅዱስ ልጁ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም በኩል ነው። አማኑኤል በሚል ኃያል ስሙ ከራሱ ጋር አንድ ያደረገን ጌታ፤ በሕይወታችን፣ በባሕሪያችን፣ በጊዜያችንና በዕድላችን ውስጥ እንዲገባ ቦታ የምንሰጠው በቅዱስ ቁርባን የመቀ'ደስን ቦታ ስንሰጠው ነው።

የሰማዩ አባታችን የሰጠው የሚስጥረ መለኮት ስጦታችን በሆነው፤ በተባረከ ሥጋና በተቀደሰው ደሙ በኩል የሚመጣው የእግዚአብሔር መንፈስ ጸጋና በረከት ከሰው ልጆች ኑሮ በሚርቅበት ጊዜ፤ የሰው ልጆች ሕይወት አጠቃላይ ውድቀትን ለማፋጠን በአጥፊ መናፍስት መሪነት በኑሮ ክፍተቶች መካከል በዘመን አመጣሽ ችግሮች ምክንያት የሰብእና ቀውስን በማስተናገድ ፍዳን መቁጠር ያለ አማራጭ የሚኖር ክስተት ይሆናል። እግዚአብሔር ከኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል? ሲል እንግዲያው "እግዚአብሔር ከኛ ጋር ካልሆነ ደግሞ ማን የማይቃወመን አለ?" የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ሕይወታችንን እንደ አገራዊ ምንነት ያለበት ደረጃን ስንፈትሸው ታዲያ ከትውልድ ትውልድ አሻግረን በስተፊት በሄድን ቁጥር እግዚአብሔርን አንድ የታሪክ ምዕራፍ ላይ ትተነው ስለመጣን፤ ሁለገብ ፈተናዎቻችን በፍጥነትና በግፊት እየጨመሩ፤ እንደ ማኅበረሰብም የነበረን የእምነት ታሪካዊ ጉዞ እና የዜግነት ሕይወት አንድነት እየፈዘዘ እየደበዘዘ ለመጥፋት ሲቃረብ፤ የዕለት ተዕለት የኑሮ እክል ተግዳሮቶች

በየጊዜው በፍቅራችን፣ በሰላማችን፣ በቤተሰባችን፣ በእውቀታችን፣ በገንዘባችን፣ በዕድላችን ላይ ሁሉ ሲቃወሙ ማስቀም አቅቶን፤ ከክርስቶስም ሥጋና ደም ረጅም ዘመናትን ርቀን የመጣንባቸውን መንገዶች በጠላት ጉዞ ተቀድመንባቸው ዛሬ እየተሰደድንም በየሄድንበት ሁሉ ብንለፋ ብንለፋ ምንም ጠብ የሚል ነገር እያጣን፤ የእፎይታ ትንፋሽ እስኪናፍቀን ድረስ የምንጨነቅ በጣም ብዙዎች ነን። ተመልከቱ! ነብዩ ዳዊት ያለው አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም ነው። እኛ 'አንተ ከእኔ ጋር ነህና' የምንልበት የሥጋና ደሙ አንድነት ላይ መንፈሳዊ ግንዛቤና የእምነት ትርጉም በሚገባ ሰጥተን ስለማናውቅ ችግራችን በተቃዋሚዎች በኩል እየበለጸገና ሌሎች ችግሮችን ወደ ሕይወታችን እየጠራ ዕድሚያችንን አስቸገረው። ጌታችን በአባቱ አምላክ በእናቱ ሰው ሆኖ፤ ሰማያዊነትን ከምድራዊነት አስማምቶ አማኑኤል ሲባል በትርጓሜው "እግዚአብሔር ከኛ ጋር ሆነ" ማለት ነው'ን ብዙ ጊዜ ብለናል። በእርግጥም የሐዲስ ኪዳኑ ተስፋ ይኼኛው ነበረ። ልዑል አምላክ ከኛ ጋር የሆነበት፤ ሰማያዊ ክብሩና ጥበቃው በሕይወታችን ውስጥ የሚገለጥበት፤ ኃይሉና ሞገሱ በኑሮአችን የሚታይበት ጊዜ ነበረ ዓመተ ምሕረት። ግን ከአንደበት በቀር እግዚአብሔርን ወደ ውስጡ ማኖር ያልቻለው ሕይወታችን፤ የአማኑኤል መለኮታዊ ስጦታ የሆነ አንድነታችንን መጠበቅና ማስጠበቅ አላውቅበትም ብሎ በተደበቁና በተገለጡ መናፍስት እንዲሁም ክፉ ሰዎች ተቃውሞ ዕድሜውና የዕድሜው ጉዞ ቅርጹን ስቶ ወደ ችግር ብቻ የሚመራው መንገድ ላይ እየደጋገመ ቢወድቅ በእውነት ምኑ ይገርመናል?

አሁንም አስተውሉ! ማን ይቃወመናል ከሚለው ከሐዋሪያው ቃል በፊት "እግዚአብሔር ከኛ ጋር ከሆነ" የሚለው ይቀድማል። አማኑኤል ይቀድማል ማለት ነው። የእግዚአብሔር አንድነት ይቀድማል ማለት ነው። የምናስቀድመውን ማወቅ ያልቻልንበት እኛ በዲያቢሎስ ሠራዊቶች የኑሮ ባለቤትነትን እስክንነጠቅ ድረስ በተናጠልም በጋራም በከፍተኛ ስቃይ ተፈትነን እየተሰቃየን ነው። ስለዚህ እንደ አገርም ያለው ታሪካዊው ጥያቄ ዛሬም ድረስ ሳይመለስ በጥርጣሬና በውዝግብ እይታ መካከል ተገኝቶ፤ እንደወረደ በቀዳነውና በኮረጅነው የምዕራባውያን ሥልጣኔ ውስጥ ልንመልሰው ብንጥርም አልተሳካልንም። ከሥጋና ደሙ ተለይተን፤ የእግዚአብሔርን አንድነት አጥተን፤ ዓመታትን ነጉደን የመጣንባቸው የኋልዮሽ ሂደቶቻችን ዛሬ ላይ ለምንገኝበት የተቃውሞ ጊዜ በተገባ አድርሰውናል። የዲያቢሎስ ሠራዊት በዚህ ተቃውሞ በኩል ሰፊውን ድርሻ ተጫውቶ፤ እንደ አገር ሊኖረን የሚገባን እድገት ላይ ድንቃራ ሆኖ ከፍታችንን በአጭር ቀጭቶ ሲያስቀረን አሁንም ገና ምኑም ያልገባን እንኖራለን። እግዚአብሔር ምሕረቱን ይላክልን።

አንድ ወቅት ላይ ኢያሱ ሕዝቡን ሲመራ፤ በመጽሐፈ ኢያሱ ምዕራፍ አንድ ላይ አንድ ታላቅ ድምፅ እንሰማለን እንዲህ ሲል "በሕይወትህ ዘመን ሁሉ ማንም አይቋቋምህም እኔ ከአንተ ጋር ነኝ።" በቃ በሕይወትህ ዘመን ሁሉ ማንም አይቋቋምህም እኔ ከአንተ ጋር ነኝ የሚለውን ድምፅ የሰማው ማን ነው? ኢያሱ ነው። የእስራኤልን ሕዝብ ወደ ምድረ ርስት ለመውሰድ በሚያደርገው ጉዞ ውስጥ፤ የርስት ባለቤቶች እንዲሆኑ ለማድረግ ባደረገው ጉዞ ውስጥ፤ ማንም አይቋቋምህም የሚለውን ድምፅ በሕይወቱ ውስጥ እግዚአብሔር ሰጠው። ማንም አይቋቋምህም የሚለው መለኮታዊ ፊርማ ደግሞ የጸደቀው እኔ ካንተ ጋር ነኝ በሚለው የእግዚአብሔር ፍቅርና የቃልኪዳን ተስፋ በተገለጠበት ድምፁ በኩል ነው።

እንደ ኢያሱ << እኔ ከእናንተ ጋር ነኝና >> የሚለውን የእግዚአብሔርን ድምፅ የሰሙ አባቶቻችን ታላቅነትን ከተባረከው ትውልድ የቃልኪዳን ሽግግር ውስጥ ተረክበው፤ በልባቸው አኑረው፤ በሰውነታቸው ይዘው ሲቀዩ፤ በዓለም ፊት ሞገሳቸውን አስነብበው ከእግዚአብሔር ጋር በአንድነት የቀየው ጊዜያቸውና ኑሮአቸው ማን ይቃወመናል የሚለውን ድምፅ እያሰማ በእውነታነት የሚታይና ሉዓላዊነቱ በማይደፈር ጥበብ ደርጅተው የቆየበት ዘመን ምስክራቸው ሆኖ ለዛሬ የኛ ትውልድ የጀግንነት ምዕራፍ ሊሆን ተቀምጧል።

የእኛስ ትውልድ? የአባቶቹን ታላቅነት እነርሱ በሄዱበት ጉዞ በኩል ሳይጓዝና የከፈሉትን የተጋድሎ መስዋትነት ሳይሰዋ እንዴት አድርጎ ታላቅነትን ሊመልስ ይቻለዋል? ታላቅነት እንዴት ያለ ነው? ከተማዎቻችን ከፍታ ባላቸው

ቤቶችና ባማሩ አስፓልቶች ቢያሸበርቁም፤ ሰው ቤቱን ያጣበት አሊያም ቤቶች ሁነኛ ሰው ያጡበት ኑሮ እየኖርን እድገታችንን በሙሉ በምዕራባውያን ቁና የተሰፈረ እየሆነ የኛ የምንለው ነገር አጥተን ሌሎችን በመምሰል ውድድር ውስጥ ቀለጥን፤ የእግዚአብሔርን አንድነት ረሳን። ስለዚህ ይቋቋሙን ዘንድ ብቀላ የተቀላቀለበት ግፊትና ሴራ ይዘው የተንሰራፉብን የመናፍስት ሠራዊት ከውስጥም ከውጪውም ድብቅ ክፉ ኃይሎች ጋር እየተጋገዙ የመኖር ሕልውናችንን ብዙ ቦታ ላይ አጨንግፈውት በታሪክ ያለፈ፤ ነገር ግን በታሪክ የማያልፍ ትውልድ እንዲገኝ ስላደረጉን ለቀጣዩ ትውልድ አረማዊነትን ከዘመናዊነት ጋር ደባልቀን እንድናቀይላቸው ተገደን ቁጭ ብለናል። በኛ ዘመን እና በኃያላን ቀደምት የአባቶቻችን ዘመን መካከል የገባው የታሪክ፣ የዘውግ፣ የሕልውና፣ የአንድነት፣ የሰላምና የእድገት ነፋስ የዲያቢሎስ ሠራዊት የተሸሸገ መናፍስታዊ አካሄድና አሠራር ነው። ይህንን አምነን ለመቀበል ሁላችን ስንጀምር፤ ፊታችንን ወደ እግዚአብሔር በማዞር የትልቅነታችንን መንገድ ጠቋሚ አቅጣጫ ማግኘት እንደምንችል ቃሉ ያስገዝበናል። እግዚአብሔር ከኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል? ነው የሚለው።

## ክፍል - 10

### ማጠቃለያ

### ያለ ሥጋወ ደሙ ክርስትና የለም!

በመጽሐፍ ቅዱስ 1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 3፥16 ላይ ያለውን "የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን?" የሚለውን ቃል ስንመለከት፤ የሰው ልጆች የእግዚአብሔር መንፈስ ማደሪያነትን በሥጋ አዳራሽ መቅደስነትና በነፍስ ጽላት ታቦትነት ቤተ መቅደስ እንድንሆን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም የደም ዋጋ ከፍሎ በመሥዋዕትነት ፍቅሩ በኩል በበረከትና በጽድቅ ኃይሉ እየተመራን እንኖር ዘንድ ሰውነትን ወስዶ አምላክነቱን ሰጠን። የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ ነው የሚለው። እዚህኛው የውስጣዊ መቅደስ መለኮታዊ ማደሪያነት ላይ መንፈሳዊ ትርጉምና ጊዜ ሳንሰጠው ስንቀር፤ ሰውነታችን ቤተ መቅደስ መሆኑ ይቀርና ቤተ ርኩሰት ሆኖ የአጥፊ መናፍስት መጋዘን መሆናችን የማይቀረው ጉዳይ ነው። ምክንያቱም ገለልተኛው ቦታ ላይ ድርሻ የምንወስድበት ዓለም ላይ አይደለም የምንኖረው። ቤተ መቅደስ መሆን ካላወቅን ቤተ ርኩስ፤ መባረክ ካልሆነልን መረገም፤ ወደ ብርሃን ለመድረስ ካልቻልን ወደ ጨለማው፤ ወደ ሰላሙ መቆየት ከተሳነን ወደ አመፃው ለመገኘት የተፈጥሮ ሕግ ጭምር ያስገድደናል። ቀኙም ላይ ግራውም ላይ ተስማምቶ ለመኖር በፍጹም አንችልም። "ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው?" (2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 6፥14)

እንግዲህ አንድ ክርስቲያን ቤተ መቅደስነቱን ያጸና ዘንድ እንዲቻለው የክርስቶስ ሥጋ ደም ያስፈልገዋል። ለዚህ ምክንያቱ ምንድነው? ምክንያቱም የቤተክርስቲያን ቤተ መቅደስ መሠረት የክርስቶስ ቅዱስ ደሙ ሲሆን፤ የኛ ቤተ መቅደስነት ስለ መቅደስነቱ ማረጋገጫው ደሞ የክርስቶስ ሥጋና ደሙ ነው። አምላክ ሰው ሆነ፤ ሰው አምላክ ሆነ በሚለው የፍቅር ትስስር ውስጥ እግዚአብሔር በባሕሪይ አምላክነቱ ሳለ ከሥጋችን ሥጋ ከነፍሳችን ነፍስ ነስቶ ሰው በመሆን ከአምላክነቱ ባሕሪይ ሊያካፍለን ሥጋችንን ከሥጋው ደማችንን ከደሙ ያዋሓደው በቅዱስ ቁርባን በኩል ነው። ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሕይወታችን ሲገባ ጊዜ የቤተ መቅደስነትን ኃይል ከውስጥ በኩል በሚኖር የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የምንካፈል ይሆናል። ያለ ክርስቶስ ሥጋና ደም << ክርስቲያን ነን! >> ብለን በድፍረትም መናገር አንችልም። ክርስቲያን ከሆንን እኛ ጋር ክርስቶስ የታለ? ክርስቲያን ከሆንን ሰማያዊ ሥጋና ደሙ በኛ

ምድራዊ ሕይወት ውስጥ መቼ ተገኘ? ክርስቲያን ከሆንን የአማኑኤል ስመ ኃይል አንድነት በኛ ውስጥ በምን መሠረት ተገነባ? ቤተ መቅደስ መሆን ያልቻለ ቤት እንደምን የክርስቶስ ቤት ነው ይባላል?

ዛሬ ላይ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ጥሩ ነው የምንለው ክርስቲያን ከውጪ ቤተክርስቲያን እየሄደ፣ እያስቀደሰ፣ ዝክር እየዘከረ፣ ጽዋ እየጠጣ፣ ታቦት እየተሳለመ፣ አጽዋማት እየጾመ በውስጡ ግን ጌታውን ማግኘትና መያዝ አቃተው። ለምን? ለምን ማግኘት አቃተው? እስኪ ለምን እንጨነቃለን? ለምን በየጊዜው ችግሮች ያስቸግሩናል? ለምን በሕይወታችን ውስጥ የምንለፋውን ያህል በረከት አናገኝም? ለምን የዓለም ሚስጢር ከጉያችን ሥር የተገኘውም እንኳ ይደበቅብናል? እውነት ጌታችን ያለበት ኑሮ ነው ኑሯችን?

ክርስቲያኖች ሁላችን ክርስቲያን ተብለን የተጠራነው በሥጋና ደሙ በኩል ነው። መስቀል ማሰር ብቻውን የክርስትና መስፈርት አይደለም። የግራውን ወንበዴ መስቀል የሚያስሩ ብዙ ሺዎች አሉ። ነገር ግን ክርስቶሳውያን እንድሆን በአንዱ ክርስቶስ ሥጋና ደም ነው የታተምነው። ሁላችን ወንድማማቾችና እህትማማቾች የሆንነው በሥጋና ደሙ ነው። ቃሉን ተመልከቱ በ1ኛ ወደ ቆሮ. ሰዎች ምዕ. 10፥17 ላይ ያለውን። << አንድ እንጀራ ስለ ሆነ፥ እኛ ብዙዎች ስንሆን አንድ ሥጋ ነን፤ ሁላችን ያን አንዱን እንጀራ እንካፈላለንና። >> ይላል ስናነበው። እኛ ብዙዎች ስንሆን ነገር ግን ምንድን ነን አለ? አንድ ሥጋ ነን አለ። አንድ ሥጋ ያደረገን ደግሞ ምንድን ነው አለ? ያ አንዱን እንጀራ መካፈላችን ነው አለ በቃ። አስቀድሞ << ከሰማይ የወረደ እንጀራ ይህ ነው፤ አባቶቻችሁ መና በልተው እንደ ሞቱ አይደለም፤ ይህን እንጀራ የሚበላ ለዘላለም ይኖራል። >> የሚለውን ቃል በቅፍርናሆም ምኩራብ ስለ ሰሙ፤ የክርስቶስን ሥጋና ደም እንጀራ ብለው ለመጥራት አልተቸገሩም። እኛ ይሄ ሰማያዊ እንጀራ ከሕይወታችን ስለጠፋን፤ ብዙዎቻችን ዛሬ የዕለት ተዕለት እንጀራችን እስከ ክፋቱ ገዝቶናል። እንግዲህ እንደምናውቀው በተለይ በዚህ ዘመን ኢትዮጵያውያንን እንደ ጉድ እያተረማመሰን ያለው ጉዳይ የእንጀራ ጉዳይ ነው። እንጀራ ውስጥ ሐብት አለ። ዝና አለ። ፍላጎትን እስከ ቅንጦት ደረጃ ሟሟላት አለ። በዚህኛው እንጀራ ውስጥ ታዲያ ግን ሰማያዊ ፍቅርና የወንድማማችነት አንድነት ስለሌለው ይኸው በየሰበብ አስባቡ ስንጋጭበት ውለን ስንጋጭበት እናድራለን። ለምን? አንድነቱ ያለው ሰማያዊው እንጀራ ላይ ነዋ። በቃ አንድ ሥጋ ነን ነው ያለው። እንኪያስ፥ ክርስቲያን ተብለን በአንድ ሥጋ ወንድማማችነት እና እህትማማችነት ክርስቲያን ለመሆን የአባታችን ክርስቶስ ሥጋና ደም ያስፈልገናል። ከዚህ ውጪ ከሆንን በግልጽ ቋንቋም ከክርስትናም ውጪ ነን።

በዚህ ዘመን ቅዱስ ቁርባን መውሰድ አስቸጋሪ ሆኗል። በዓለማዊው በኩል የርዮተ ዓለም ዳፍንት የተጠናወተን፤ በፍልስፍና ንድፈ ሐሳቦች የናወዘን፤ በቀለም ትምህርት ላይ ዕድሜ የጨረስን፤ የምዕራባውያንን ሥልጣኔ በኢኮኖሚ ጫናና የሥጋ ተገዢነት በኩል እስከ አተላው የተቀበልን፤ የእምነት ፍቅርና መሻቱ የራቀን ስለሆንን የኛ ባሕሪያችን በራሱ ለሥጋና ደሙ ክብር በቀላሉ የተመቸ አይደለም። በመንፈሳዊውም በኩል የዛሬ ጊዜ ንስሐ አባቶች፣ መምህራንና አገልጋዮች ምዕመኑን ወደ ቅዱስ ቁርባን ማስጠጋት ተስኗቸው፤ አልፎም "ገና ናችሁ አትንኩ፣ ትቀሠፋላችሁ፣ ዕድሜያችሁ አይፈቅድም፣ ከቁርባን በኋላ ፍጹም መሆን አለባችሁ፣ ከቁርባን በኋላ ኃጢአት ብትሠሩ ቁጣ ትጠራላችሁ፣ ቅዱስ ቁርባን ለበቁ ሰዎች ነው!" የሚል የሚሰጥረ መለኮት ሰጦታን የሚያሸሽ፤ በአንፃሩ በሰዎች ሕይወት ውስጥ እሰራት የሚሆነውን የዲያቢሎስን ባላጋራነት የሚያቀርብ ቋንቋና መረጃ እያሰሙ አብዛኛው የማኅበረሰብ ክፍል የሆነው ወጣቱን ከእግዚአብሔር አንድነት የቃልኪዳኑ ኃይል ሰላራቁት፤ የእነዚህ ሁሉ ውጤቶች በአንድ ምዕራፍ ሲጠቀለል ኢትዮጵያውያን ብዙ ቦታ ላይ የማይከናወንልን መከራ ቀጣሪዎች ሆነን በትንሽ ነገር ብዙ እየተደሰትን፤ ነገር ግን ትልቁ እንደሰማይ የራቀን፤ ሰማያዊ ተስፋና ራእይ ከአኗኗራችን ውስጥ ተለይቶ የእርግማን መግለጫ ዘመን ላይ የተገኘን የነፍስም የሥጋም ቁስለኞች በመሆን በየግልም በየጋራም ስቃይ ውስጥ ተዘፍቀን፤ ደግሞ ተሰብስበንም እንደ ተናጠል ችግርንና እንደ አገር ያለብንንም ሁለ ገብ ቀውስ ለምደነው፤ መፍትሔ በአንደበት ቀርቦን በተግባር ሲርቀን፤ ሁሉም ወቃሽ፣ ክስ አቅራቢና አብጠልጣይ ሆኖ፤ እንደ ሃይማኖትም፣ እንደ ዜግነትም፣ እንደ አገር ሉዓላዊነትም፣ እንደ ማኅበረሰብ ፍቅርም በዝግታ ስንፈርስም እያየን ችግርና መከራ

አስጨንቆ ካልተከተለን በቀር አንዳንዶቻችን ብዙም አይገባንም፤ አንዳንዶቻችን አያስጨንቀንም፤ ለአንዳንዶቻችን ከነአካቴው ምናችንም አይደለምም።

ይሄንን ቃል በአንክሮ አስምሩበት። ያለ ሥጋና ደሙ ክርስትና የለም። ምክንያቱም ሥጋና ደሙ የለንም ማለት፤ በቀጥታ ክርስቶስ የለንም ማለት ነው። ዮሐንስ 6፥56'ን አንብቡ። ይኸውላችሁ፤ ጸሎት ክርስቶስን ማነጋገሪያ ነው። ስግደት ስለ ክርስቶስ ፍቅር ራስን ማስገዢያ፣ ኃይሉን መልበሻ፣ ቃልኪዳኑን ማጽደቂያ እና አምልኮት ማቅረቢያ ነው። ጾም በሥጋ ድካም በኩል መንፈሳዊነትን ማበርቻ ነው። ቅዱስ ቁርባን ግን ክርስቶስን ማኖሪያ ነው። በጸሎት፣ በስግደትና በጾም ጌታን ከውጪ ነው የምንቀበለው። ሥጋና ደሙን ስንወስድ ግን ወደ ውስጥ እንድንቀበለው ነው ሕብስተ ስንዴ እና ሕብስተ ወይን ሆኖ የተዘጋጀው። ሥጋና ደሙን ከላይ እንደ ቅባዕ ቅዱስ የምንቀባው፣ እንደ ጸበል የምንረጨው፣ እንደ ጸሎት መጽሐፍ የምናነበው አይደለም። ከውስጣችን መሠረት የምናኖረው መለኮታዊ ስጦታው ነው። ቤተክርስቲያን ያለ ክርስቶስ ደም መሠረት ቤተ መቅደስ እንደማትሆነው፤ እኛም ያለ ሥጋና ደሙ የውስጥ መቅ'ደስ ክርስትናችን ቤተ መቅደስነትን አይይዝም።

ዛሬ ላይ ብዙ ወገኖቻችን ሃይማኖት አለኝና ርኩሳን መናፍስት በኔ ላይ ሥልጣን የላቸውም የሚል የአንደበት ፉከራን እያሰሙ መናፍስት የበለጠ በጠባያቸውና በሕይወታቸው ውስጥ ሥር እንዲሰዱ የሚደበቁበትን ምሽግ ያበለጽጉላቸዋል። ዛሬም ድረስ በመናፍስት ተይዘናል ለማለት ጸበል ላይ የሚጮኹ፣ በቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ የሚታሠሩ፣ በየገዳማቱ የሚታሠሩ ሰዎችን ብቻ መስፈርት አድርገን፤ እኛ ከመናፍስት ስውር አገዛዝ ነፃ እንደሆንን በዘመናዊነታችንና ትንሽም ብቅ ጥልቅ በምናደርጋት ክርስትናችን ተማምነን የተቀመጠን እጅግ ብዙዎች ነን። ይሄ በጣም አስቸጋሪው ነገር ነው በእውነት። ግን እዛ ጸበል ቦታ ተገልጦ የጮኸውን ጩኸት እኛም እያንዳንዳችን በየግል በየግላችን እንጮኸዋለን። ጩኸት ሁለት መልክ ይኖረዋል። አንደኛው ድምፅ እያወጣን የምናሰማው ዋይታ ሲሆን፤ ሁለተኛው ድምፅ አልባ << ኡኡታ >> እናሰማለን። የብዙዎቻችን ጩኸቶች ድምፅ አልባ ናቸው። ሕሊናችን ይጮኻል፣ አስተሳሰባችን ይጮኻል፣ ማስተዋላችን ይጮኻል፣ እቅዳችን ይጮኻል፣ እውቀታችን ይጮኻል። ሕሊናችን ሲጮህ፥ ከውስጣችን ጋር የማይግባባ ክፉ አሳቦችን እያመላለሰ ወደ ውጪም ይኸው ክፋት በተገለጠ ጊዜ ለምንም የማይበጅ፣ የበጎነትን ኃይልና አቅም የሚቃወም፣ በሌሎች ላይ ክፉ ክፉውን በምቀኝነትና በተንኮል ገልጦ የሚያሳይ ይሆናል። አስተሳሰባችን ሲጮህ፥ ለመልካም አሳብ ምግባር ውጤት መሆን የሚችልን እንቅስቃሴ ለመፍጠር የሚታገል እየሆነ፤ ለሥጋዊ አመለካከት የምቾት እይታ ብቻ ሚዛኑ ያጋደለ እየሆነ፣ መስሎ በመኖር ጋጋታ ውስጥ የራስን ጸጋና የኑሮ ዕድል አሳልፎ የሚሰጥ ይሆናል። ማስተዋላችን ሲጮህ፥ ለነፍስና ለሥጋችን የሚጠቅመውን ለመለየት የምንችልበት አመዛዛኝነትን እያጣን፤ በሕይወታችን ውስጥ የተበላሹትንና እየወደቁ ስለሚመጡት ነገር ጊዜ ሰጥተን መንስኤያቸውን ለማውጠንጠን ፋታና እርጋታ እያጣን፤ መንፈሳዊ ሚስጢራትንና የልዑል አምላክን ስውር ስጦታ ለማገናዘብ አቅም እያጣን በታይታ ሃይማኖት ተቸግረናል። እቅዳችን ሲጮህ፥ ራእይና ሰማያዊ ተስፋ ከልብና ከኑሮአችን እየተጠነቀ በምድራዊ መረጃዎችና የፖሊሲ ፍልስፍናዎች ብቻ የመኖራችን መሠረት ሲገነባ፤ የሚመጣውን የርኩሰት ዘመንና የጥፋት ኃይሎችን ወጥመድ ለመከላከል የማይችል ሆኖ የምንመራበት የኑሮ መርህና መድንግግ የሌላውን ችግርና ስቃይ ለመካፈል ትንሽ እንኳ ዘንበል ያላለ ራስ ወዳድነትን ብቻ የሚንጸባርቅ ይሆናል። እውቀታችን ሲጮህ፥ የምናውቀው መረጃ ሁሉ በአንዳች ጥፋት የተመረዘ፤ የምንማረው ሁሉ ፍሬያማና ውጤት ላይ ለመድረስ ያቃተው፣ የምንናገረው የአገርን ሞገስና ታሪካዊ ዳራ ያናናቀ የሆነ፣ የምንቀበለው ከፈረንጁ ዓለም 'የቲዎሪ' ጫና እና ተጽዕኖ ያልተላቀቀ ሆነና ዕድሜያችን በቃላት አልባ ሰቀቃዎች በየጊዜው ታጥሮ የመገኘታችን ዕጣ በእውነትም ከየት የመጣ ነው? አየህ በቃ የምንጮኸው ጩኸት ውስጣዊ ነዋ። እርሱን ለመገንዘብ እዛጋ ፍቃድና ጊዜ አልሰጠንም። ስለዚህ የማንጮኽ የምንመስል ጩኸተኞች በዘመኑ ላይ በዝተን በዝተን የሕይወት ወይን ሲለየን ጊዜ፤ እውነት ሐሰት፣ ሐሰቱ ደግሞ እውነት፤ ፍቅር ጥላቻ፣ ጥላቻው ደግሞ ፍቅር፤ ርኅራኄ ሞኝነት፣ ተንኮል ብልጠት፣ ምቀኝነትና አስመሳይነት የጋራ

ጠባያችን ሆኖ፤ ዛሬ ላይ የምንሰማቸውን አሰቃቂ ዜናዎች፣ ሽብሮች፣ መተረማመሶች፣ አለመግባባቶች ለማስተናገድ ተገደናል። እግዚአብሔር ይማረን!

አሁንም በአጽንዖት ያዙ! ያለ ሥጋና ደሙ ክርስቲያን መሆን የማይቻል ነው። ክርስቶስ የሌለበት ሃይማኖት እንደምን የክርስቲያን ነው ሊባል ይቻለዋል?

ሥጋና ደሙን እንደ መጨረሻ የበቃ የክርስትና ደረጃ አድርገው በዘልማድ የቀዩ ሰዎች የሚነዙት የዘልማድ ትምህርት እኛንም የ-ዘልማዶች ሲያደርገን፤ ሁሉንም ነገር በቃ በልማድ፣ በስሜት፣ በመሰለኝ እየከወንን፤ ያዝነው ስንል እየሸሸ፣ ሸሸን ስንል እየያዘን፤ ኑሮዬ ሊያልፍለት ነው ስንል እኛን በጭንቀት እያሳለፈ፤ በበረከት ቀምን ስንል እንደገና እየተንሸራተትን፣ ሆነ ስንል አልሆን እያለ ሕይወት ካሰብናት ውጪ በምትፈልገው ጎዳና ላይ ስታሽከረክረን እኛም ስንሽከረከርላት፤ የዚህ ሁሉ መዘውር መሪ የሆነው ጠላታችን በኑሮአችን ደስ ብሎት ዝም ያለ ስቃይ እያሰቃየን በመጨረሻውም የግራውን ጎተራ ሊሞላ ሲጣደፍ ታዲያ እንዴት ነው የሚሻለን እስኪ?

የክርስቶስን ሥጋና ደም ለመውሰድ ምንም አይነት የዕድሜ መስፈርት፣ የኑሮ ደረጃ እና ፆታ አይለይም። በፍጹም የነፍስ፣ የልቦናና የምግባር ፍቅር በንስሐ ወደ እግዚአብሔር መመለስ ነው የቅዱስ ቁርባን መስፈርት። በዘመናችን ሲሆን የምናየው ግን ምንድነው ሕፃናት እና አዛውንታን እንጂወሰዱት የታዘዘ እስኪመስል ወጣቶችና ጎልማሶች ወደ ቁርባን አይጠጉም። ሲገርማችሁ ደግሞ ይልቁኑ ሥጋና ደም ለማን በጣም ያስፈልጋል ስንል ለወጣቱና ጎልማሳው ነው። ምክንያቱም ስሜታዊነት የሚወጣበት፣ አቅምና ጉልበት የሚጸናበት፣ ብዙ ሥራ የሚሠራበት፣ ትዳር የሚመሠረትበትና እንደ አገርም አምራች ዜጋ የሚኮንበት የዕድሜ ክልል በአብዛኛው ስለሆነ፤ በዚህ ጊዜ ነው ይልቁኑ እግዚአብሔር አብሮን መገኘት ያለበት። ስሜታዊነትን ወደ መንፈሳዊ ኃይል እንዲቀይረው፤ አቅምና ጉልበታችን በመናፍስት እንዳይደክም አሊያ ለክፋት እንዳይውል፤ ሥራችን እንዲባረክ፤ ትዳራችን እንዲሰምር፤ የአገር ፍቅር ከታሪክ ቁጭት ጋር ያለው የተቀደሰ ዜጋ እንዲኖር ሥጋና ደሙ መቅረብ የነበረበት ለወጣቶች ነበረ። ተገላቢጠና ወጣቶች ከቅዱስ ቁርባን ሲርቁ ይኸው ኑሮአችንም በዘርፈ ብዙ አውታረ አቀጣጫዎች ተገላብጦ ቁጭ አለ። አሁን በቃ ግዴታ እኮ ነው። የመረጥነውን እንድሆን እግዚአብሔር አምላክም ምርጫችንን ያከብራል። "ና ከኔ ጋር ሁን!" ብሎ የሚያስገድድ አባት አይደለም። አስገድዶ የሚይይዝህ አጥፊው ጠላት ነው። ይሄ እውነታ በደንብ እስከሚገባን ድረስ ተጨማሪ የስቃይ፣ የመከራ፣ መፍትሔ የማጣትና የመጨነቅ ሕይወትን በየግል በየግል እንጠብቃለን።

መደምደሚያ ቃሉ እንግዲህ ይሄ ነው። ያለ ሥጋወ ደሙ ክርስትና የለም። ጌታ ያለውማ እንደውም ሕይወት የለም ነው። በራሳችሁ ሕይወት አይኖራችሁም ነው ያለው በዮሐንስ ወንጌል 6፥53 ላይ። ስለዚህ እውቁበት።

ለሥጋወ ደሙ ያብቃችሁ።

<u>አስጀምሮ ላስፈጸመን ልዑል እግዚአብሔር ምስጋና ይግባው!</u>